# ደማቆቹ

## የአንዳንድ ታዋቂ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የሕይወት ውልብታ




D/N Solomon Yohannes
0911860113
0111/271609

የዚህ መጽሐፍ ቅርጽ
ዓላማና ርእይ የሚመራው፣ ወደ ላይ ከፍ እያለና
አተኩሮ የሚያድግ መጪ ትውልድ መናፈቅን
ያመላክታል።

አዲስ አበባ
ሰሙነ ፪ሺ ዓመት ክብረ በዓል
© ሰሎሞን ጥላሁን / ሥምረት ገብረማርያም
email: ethiodemak@gmail.com

www.ethiopianorthodox.org

## ሥነ ጽሑፋዊ አርትዖት

**ፍትሕ አምላክ እንየው**
**ትእግሥት እንዳሻው**

የገጽ አቀማመጥና (Layout) የውብሲ
ሽፋን
**ምናሴ ዘውዴ**

**መብቱ በሕግ የሰሎሞን ጥላሁንና የሥምረት**
**ገብረማርያም ነው**

©፪ሺ. (2000)

## መስክሪዎች

«...አነሰም በዛ በገሎ ተግባርን አሞጋሽ ከተገኘስ ልበርታ» የሚያሰኝ፣ በሚገባ፣ ባማረ አገላለጥ የቀረበ፣ ሰብሰብ ያለ፣ በልብ የሚያድር ወሸኔ ሥራ!!

**ኮሎኔል ሊቁ ዓለሙ – የሕግ አማካሪና ጠበቃ**

ሁሉንም ዐይነት አንባቢ እንዳመጣጡ ያስተናግዳል፤ አስተናግዶም በውበቱ እያዋዛ እያባባና እያዝናና ያስተምራል።

**ደርበው አዱኛ– በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የዘገባ አጻጻፍና ሒሳዊ ንባብ እንዲሁም የሥነ ጽሑፍ መምህር የነበረ**

ትልቅ ሰውነት የሚገኘው ትልቅ ለመሆን በሚደረግ ራስ ወዳድ ተጋድሎ ሳይሆን መለኮት የሰጠንን ችሎታ ለሰው ልጆች ጥቅም ለማዋል በምናደርገው ትጋት መሆኑን ያሳየናል። ኢትዮጵያዊነትን የሚያፋፋ ድንቅና መሳጭ ዘገባ! በይዞታው ብስል ባቀራረቡ ኪን።

**አቶ ንጉሤ ቡልቻ– ቃለ እግዚአብሔር አንባቢያን ማኅበር ዋና ጸሐፊ**

**ደማቆቹ** በርቀትና በድንግዝግዝ እናያቸው የነበሩትን አቅርበን እንድናያቸው፣ በቅርብ ያሉትን ደግሞ በጥልቀትና በስፋት እንድናውቃቸውና የሕይወት ጉዞአቸውን ከነበራቸው ምኞት፣ ተስፋና ተሳትፎ ጋር ገምግመን እንድናደንቃቸው የሚረዳ የታሪክ መስተዋት ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ከዚህ መጽሐፍ በማንበብ የማይጠቀም ይኖራል ብዬ አልገምትም።

**ንጉሤ ተፈራ (ዶ/ር) – ፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር በኢትዮጵያ ዋና ተጠሪ**

ታሪካችንን ታሪክ ባሰኙት ከዋክብት ብርሃን መድመቅን እንጂ በጉድፋቸው መሳለቅን የማናይበት፣ ከካህን እስከ ደራሲ፣ ከጦር ሰው እስከ ሃያሲ፣ ከስፖርተኛ እስከ በጎ አድራጊ እጅግ ብዙ ብዙ የሕይወት ፈርጥ የተላበሱ መኩሪያዎቻችንን ታሪክ በሕያው ብሌንነት ያቀረበ ግሩም ሥራ!

**አቶ ጌታቸው በለጠ – የኢትዮጵያ ደራሲዎች ማኅበር ፕሬዘዳንት**

www.ethiopianorthodox.org

# መክስተ ውልብታ


ቀዳሚ ጕዳዮች
መቅድም
መግቢያ
ደማቆቹ

፩
ኦኒሲሞስ ነሲብ (አባ ገመቹስ)
1842 – 1923
ከባርነት ወደ ላቀ ምሁርነት
ገጽ 21- 40

፪
ከንቲባ ገብሩ ደስታ
1848 – 1942
"የአለቃ ኀባው መዝገብ!"
ገጽ 41 - 56

፫
አለቃ ታዬ ገ/ማርያም
1853 – 1916
የፊዉለማው ብርታት የጎፈነነው ምሁር
ገጽ 57 - 72

፬
አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ
1864 – 1934
የቀለም ቀንድ የቃላት ጕልላት
ገጽ 73 - 88


www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፭

ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ

1878 – 1912

ቀድሞ መጣ ቀድሞ ሔደ

ሩቅ አሰበ ቅርብ ዐደረ

ገጽ 89 - 106

፮

ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ

1907 –

ትንፋሽ ረጅም እግረ ብርቱ

ገጽ 107 - 116

፯

ይድነቃቸው ተሰማ

1914–1979

የአፍሪካ እግር ኳስ አባት

ገጽ 117 - 132

፰

አለ ፈለገሰላም

1915–

ተማጠነ ለበላይ

ሥዕል በኢትዮጵያ እንዲሆን ዘመናይ

ገጽ 133 - 148

፱

እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ

1916–

የሙዚቃ አርቅቆ ምናኔን ተጣብቆ

ገጽ 149 - 162

፲

ተስፋዬ ማህሉ

1916–

የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች

እንደምን አላችሁ ልጆች!

ገጽ 163 - 178

፲፩

ዓለማየሁ አበበ

1916–

በምድር እንደ ጉንዳን ታተረ

በሰማይ እንዳሞራ በረረ

ገጽ 179 - 194

፲፪

ገርማሜ ንዋይ

1916–1953

"ጀመኛው አገረ-ገዥ"

ገጽ 195 - 210

፲፫

ቄስ ጉዲና ቱምሳ

1921– 1971

ፍትሕና እውነትን ለመታደግ የተከፈለ መሥዋዕትነት

ገጽ 211 - 226

፲፬

ሰሎሞን ተሰማ

1926– 1972

ስለ ስፖርት ለፈፈ ሳይደክመው ዐረፈ

ገጽ 227 - 238


www.ethiopianorthodox.org

፲፭
ጸ.ጋዬ ገብረ መድኅን
1929–1998
ማኅደረ ሼክስፒር ትምክሕተ አፍሪካ
ገጽ 239 - 256

፲፮
በዓሉ ግርማ
1931–1975
ሰማዕተ ብርዕ
ገጽ 257 - 270

፲፯
አሸናፊ ከበደ
ውስጥ አዘንባይ ነፍስ አባባይ
1931 –1991
ገጽ 271 - 282

፲፰
ዶ/ር ጀምበር ተፈራ
የዘመን ፍልሚያ በድኻ ጐን
1935 –
ገጽ 283 - 304

፲፱
ደበበ ሰይፉ
ከዘመን ኩርፊያ
1942 – 1992
ገጽ 305 - 316

፳
ደራርቱ ቱሉ
ቀድማ የበራች ኮከብ
1964 –
ገጽ 317 - 336

www.ethiopianorthodox.org

# ቀዳሚ ጉዳዮች

## ምክንያተ ድምቀት

ከየሙያ ዘርፉና ከልዩ ልዩ የሕይወት መስኮች፣ የተረሱትንም ሆነ የታወሱትን አንዳንድ የኢትዮጵያ ታላላቅ ልጆች፣ ሚዛኑን በጠበቀ መሥፈርት፣ እጥር ምጥን ያለ የሕይወታቸውን ውልብታ (Life Profile) አስቀድሞ በተከታታይ ቅጽ በኋላም በአንድ የዳጎሰ ጥራዝ በማስፈር አሁን ላለው ትውልድ ተስፋ ለመጪው ትውልድ ደግሞ ትምህርት የሚሆን መጽሐፍ በማዘጋጀት፣ በአገር ውስጥና በውጪ ያሉትን ኢትዮጵያውን ተስፋ ማለምለምና ማበረታታት የዚህ መጽሐፍ ዐላማ ነው።

## የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ዐበይት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው

ተደራስያን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን ደማቅ ባለ ታሪኮች አጭር የሕይወታቸውን መልክ ወይም ውልብታ ከማንበባቸው የተነሣ፣ ኢትዮጵያን አስመልክቶ ውስጥ አዘንባይነት (ወደ ውጭ ከማየት ወደ ውስጥ የማየት ዝንባሌ) እንዲያዳብሩ በማድረግ ኵነኔ ኢትዮጵያዊነትን ማስወገድ።

የገጸ ባሕርያቱ የሕይወት ውልብታ ያካተታቸውን አኩሪ ታሪክ በመጠቀም በእነዚህ ደማቆች ሕይወት ውስጥ የታዩትን የሕይወት ሥርዐቶች በመጠቀም ጠቃሚ እሴትን መሠረት ያደረገ የአስተሳሰብ ባሕል ለትውልድ በማስተላለፍ ኢትዮጵያዊነት የጅራት ኩራት እንዳይሆን ሥርቶ የመኩራትን ባሕል ማዳበር።

የደማቆቹን ዐበይት ክዋኔዎች በመግለጽ፣ ማን ምን ሠራ የሚለው ጥያቄ ለመጪው ትውልድ መልስ የሌለው ወይም አስቸጋሪ ጥያቄ እንዳይሆን ጥያቄውን ቀድሞ መልስ በማዘጋጀትና ለወደ ፊት አጥኚዎች አማራጭ የሕይወት ታሪክ ማገናዘቢያ በማሰናዳት መጪውን ትውልድ ለብሩህ ተስፋ ማዘጋጀት።

በበጎ ምግባራቸውና ዐቢይ ክዋኔአቸው አንድ ሰሞን ብቅ ብለው ዳግም የተረሱትን በቋሚነት በማስታወስ ተከታታይነት ያለውና በመጪው ትውልድ ሊቀጥል የሚችል የሕይወት ውልብታን ሥራ ማስተላለፍ።



## አበርክቶት

### ለሚመጡ — አበርክቶት ለዐደራ

ጥሎ ማለፍ፣ ወድቆ መታለፍ በመጪና በነባር ትውልድ መካከል በአገራችን የተጣባን ክፉ በሽታ ነው፤ አያሳድግም! አገራችንን ስናስብ ከዛሬ ይልቅ ትናንት ገንኖ መታየት የለበትም፤ ዛሬም ትናንትናን መርገጥ የለበትም ፤ ነገም ድንገት እንደሚመጣ ያልታሰበ ጉዳይ መቆጠር የለበትም። አገራችን ኢትዮጵያ የትናንትናን ታሪክ ሳትጥል፣ የዛሬን ትውልድ እያስተናገደች ነገን በተስፋና በሰላም እቅፏ ውስጥ ልታካትት ይገባታል። ይህ ከማንም ይልቅ የመጪው ትውልድ ዐደራ ነው። እነሆ ይህ መጽሐፍ ለዛሬ ልጆች ለነገ ደማቆች የአደራ አበርክቶት ይሁን!!

**መጥታችሁ ድመቁ**

—//—



www.ethiopianorthodox.org

## ምስጋና

### ለአልፋ ኦሜጋው
ስለ ሰበብ የለሽ ሰበብነቱ

### ለረዳእያን

ገንዘብ የሚያስፈልገውን መንገድእናንተ ባትሄዱልን ኖሮ
መንገት ቀርተን ነበር

### ቅድመ ኅትመት
ሰቶ ብርሃኑ ዓስማየሁ
ሰቶ ዓርአያ የማነ፣ ሰቶ ጥበቡ ጋሹ፣ ሰቶ ሰዝሬ መርሻ
ወ/ሮ ያሬድ ጥላሁን፣ ወ/ሮ ኢትዮጵያ ሰዮስ
ሰቶ ሚሊዮን በስጠ፣ ሰቶ ዓስማየሁ ኅይሉ

### ኅትመት
ሕይወት ብርሃን ቤተ ክርስቲያን
ዶ/ር ፈት ሊካሳ ፣ ወ/ሮ ማሚቱ ተሾመ
ሰቶ ሔኖክ ወንድሙ
ሰቶ ማሙሻ ፈንታ ፣ሰቶ ሙሉቀን ፈንታ
ሰቶ ገረመው ግዛው፣ ዶ/ር ገብረመስቀል ሀብተማርያም

### ድኅረ ኅትመት
ፐፕሊሽን ሚዲያ ሴንተር ሊትዮጵያ

## በጥንቅሩ ሥራ ላይ ለተሰለፉት ግለሰቦች

### ዓይነተኛ ጉልበታችን እናንተ በመሆናችሁ
### ክፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን

ፍቅረ ኢየሱስ ሁንዴሳ፣ ምኒልክ አስፋው
ሰሎሞን ገመቹ፣ ሁሴን ከድር
በኃይሉ ገብረ እግዚአብሔር
ፍቅር ይልቃል፣ነጻነት ሰሎሞን
ቁምላቸው ፋንታሁን
ስሜ ታደሰ
ሔኖክ ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

## መቅድም

ኢትዮጵያ የብዙ ደማቆች አገር መሆንዋ የታወቀ ቢሆንም ታሪካቸው በአግባቡ በወረቀት ላይ ቀልሞ የተመዘገበው የጥቂቶቹ ብቻ ነው:: በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎችና ባገኙአቸው ዕድሎች በአገር ውስጥና በውጭ አገር ዕውቀት ለመቅሰምና የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት የቻሉ አንዳንድ ኢትዮጲያውያን ያገኙትን ዕውቀት ለወገኖቻቸው ለማድረስና አዳዲስ አሠራርንና አስተሳሰብን በሕዝባችን መካከል ለማስረጽ፣ አብዝተው የደከሙና ሕይወታቸውን አሳልፈው እስከ መስጠት የደረሱ ፋና ወጊ ምሁራን እንደ ነበሩ ይታወቃል:: አገራቸውን ከውጭ ወራሪና ጠላት በመከላከል አኩሪ ታሪክ የሠሩ፣ የሕዝባቸውን ደኅንነትና አንድነት እንዲጠበቅ ለማድረግ መሥዋዕትነት የከፈሉና አንፀባራቂ ታሪክ የሠሩ ጥቂቶች አልበሩም:: በደራሲነት፣ በሙዚቃ፣ በሥዕል፣ በስፖርት፣ በታሪክ፣ በሳይንስና በተለያዩ የኪነ ጥበብና የምርምር ሥራዎችም ኢትዮጵያን በዓለም የበለጠ እንድትታወቅ ያደረጉ ትናንትናም ዛሬም ደምቀው የሚታዩ ደማቅ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብዙዎች ናቸው:: የሚያሳዝነው ግን በነዚህ ሰዎቻችን ላይ የተደረጉት ጥናቶችና የተዘጋጁ የታሪክ መጽሐፍት በጣሙን ውስን መሆናቸው ነው:: ታሪካችን በሰፊው አልዘገባቸውም:: ስለሆነም እንኳን በሩቅ የነበሩትን ቀርቶ በቅርብ ያሉትንም ደማቅ ኢትዮጲያውያን አብዛኛው ሕዝብ የሚገባውን ያህል አያውቃቸውም:: እንዲህ የሚረዳበት አጋጣሚ ወይም ዕድል በበቂ ሁኔታ አላገኘም::

ይህ መጽሐፍ የኢትዮጲያዊነት ስሜትን፣ የአገርና የሕዝብ ፍቅርን ተላብሰው በተሰማሩበት መስክ ሁሉ አገራቸው ተገቢውን ዕውቀትና ክብር እንድትላበስ ታሪካዊ ጥረት ያደረጉትን ያስተዋውቀናል::

**ደማቆቹ** ሁኔታዎች እንደ ዛሬው በአብዛኛው ባልተመቻቹበት፣ የመንግሥት ግንዛቤም ሆነ ድጋፍ እምብዛም

በማይታይበትና የሕዝቡም ዕውቀትና ተሳትፎ ጠባብ በነበረበት ዘመን፣ የአገራችንን ሁኔታ ለመለወጥ ፋና ወጊዎቹ የተጓዙበትን ረዥም አድካሚ መንገድና ውጤታቸውን ስናይ የራሳችንን የሕይወት አካሄድና ለአገራችን ዕድገት ያደረግነውን በጎ ጥረት አጥብቀን እንድንጠይቅ እንዲሁም እኛ ዛሬ ከምንገኝበት የተሻለና አመቺ ሁኔታ ጋር እንድናመዛዝን ያደርገናል፡፡

**ደማቆቹ** በርቀትና በድንግዝግዝ እናያቸው የነበሩትን አቅርበን እንድናያቸው፣ በቅርብ ያሉትን ደግሞ በጥልቀትና በስፋት እንድናውቃቸውና የሕይወት ጉዞአቸውን ከነበራቸው ምኞት፣ ተስፋና ተሳትፎ ጋር ገምግመን እንድናደንቃቸው የሚረዳ የታሪክ መስተዋት ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ከዚህ መጽሐፍ በማንበብ የማይጠቀም ይኖራል ብዬ አልገምትም፡፡

**ንጉሤ ተፈራ (ዶ/ር) ፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር በኢትዮጵያ ዋና ተጠሪ**



## መግቢያ

«ጨቡዴ ዳንዴ ሰኞ ተወለደ፤
ማክሰኞ ተጠመቀ፣ ረቡዕ አገባ፤
ሐሙስ ታመመ፣ ዓርብ ባሰበት፤
ቅዳሜ ሞተ፣ እሁድ ተቀበረ!
የጨቡዴ ዳንዴ መጨረሻው ይህ ሆነ።»

ይህ ከላይ የተነበበው የልጆች የጨዋታ መዝሙር ነው። ይሁን እንጂ በሌላ መልኩ ደግሞ ቢታይ የብዙዎች የግል የሕይወት ታሪክ ሳይሆን አይቀርም። ወደዚህ ዓለም መጥተው በየት በኩል እንዳለፉ ሳይታወቅ እንደ አገባባቸው ሹልክ ብለው የወጡ ብዙ ናቸው። አንዳንዶች ደግሞ «የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ» ዓይነት ናቸው። ውስጣቸው «ያለ ምክንያት መኖርን» የተቆጣ ነው። ለእነዚህ ዓይነት ሰዎች የሕይወት ተግዳሮቶች (*Challenges*) ዱብ ዕዳ ሳይሆኑ ዱብ ዕጣዎች ናቸው። የማስናከያውን አለት የመረማመጃ ድንጋይ አድርገው ማለፍ ይችላሉ። አንድ አገር እንዲህ ዓይነት ሰዎች የበዙላት እንደሆን ትፋፋለች፤ በየምክንያቱ ሲያንሱና ሲጠፉ ደግሞ ትቀጭጫለች፤ ይህም ጥናትና ምርምር የማይጠይቅ ግልጥ ያለ እውነት ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ ብዙ ደማቅ ልጆች አሏት። በኪነ ጥበቡ፣ በማኅበራዊውና በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካውና በሌሎች የሕይወት መስኮች የጥበብን ነፋሳት ያነፈሱ ቁጥራቸው ብዙ ነው። የእነርሱን ንፉስ ምን ታሪካቸውን ችላ ማለት «ጨቡዴ ዳንዴነት» ነው። የጀመርነው አዲሱ ሺ ዓመት እንዲህ ዓይነቱ የታሪክ ባለ እዳነት የማይሸጋገርበት እንዲሆን ተመኘን። ስለዚህ የኛዎቹ ከዋክብት ለመጪው ዘመን ተስፋ ድምቀት እንዲሰጡና በአንድ ሰማይ እንዲንተገተጉ ፈለግን።

ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ የከዋክብት አሰሣ ይጀመራል እንጂ አያልቅም፤ በዚህ ቅጽ ከሰፈሩት የኛዎቹ ታላላቅ ሰዎች የሕይወት ውልብታ **«እገሌና እገሊት ወዴት ገቡ?» የሚሉ አንባቢዎች በእርግጥ ይኖራሉ። መቼም አገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ደማቆች አገር ናትና የሁሉንም**



www.ethiopianorthodox.org

የሕይወት ውልብታ በአንድ መጽሐፍ ማካተት አዳጋች ነው። በተጨማሪም ይህ በእጃችን ያለው መጽሐፍ ቅጽ አንድ ነው፤ ገና በቅርቡ በሁለተኛ ቅጽ ከዋክብት ይደምቃሉ፤ በየቅጹ ሰማይ ይፈነጥቃሉ። ስለዚህ ንገሩን እናዳምቃቸው ጠቁሙን እናጀግናቸው እንላለን። እነዚህ በቅጽ አንድና በሌሎች ተከታታይ ቅጾች የሕይወት ውልብታቸው ሊካተት የሚገባቸው ግለሰቦች፣ የሚከተሉትን ነጥቦች ከሞላ ጎደል ማማላት ይኖርባቸዋል ብለን አስበናል።

**ፋና ወጊነት፦** በሙያ መስካቸው ወይም በታወቁበት ነገር የመጀመሪያው ሆኖ መገኘት።

**ልዩታ/ብርቅነት/፦** በዚህ በታወቁበትና ፋና በወጉበት ጉዳይ ከሌሎች ልዩ መሆናቸውን ማስመስከራቸው።

**አስሚነት፦** ይህ ልዩ ያደረጋቸውና የታወቁበት ነገር በማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ በአገርና ከዚያም በላይ እንደ ፊፌው ማስማቱ።

**ዘላቂነት/ዘመን አይሽሬነት/፦** ይህ በመስኩ ልዩ መሆን በአገሪቱ ተከታታይ ትውልድ በዘላቂነት ተይዞ መቀጠል መቻሉ።

**ሰፊነት፦** ይህ ለውልብታ ያበቃቸዋል ተብሎ የታመነው ዐቢይ ክዋኔአቸው በመጀመሪያ የሙያ መስካቸውን፣ ከዚያም አጠቃላይ የማኅበረሰቡን አስተሳሰብ ከመለወጥ አንጻር ያለው የጉልህነት ተጽእኖ ።

**ጽናት፦** በተሰማሩበት የሙያ መስክ ወይም በታወቁበት ጉዳይ ያሳዩት ምሳሌነት ያለው የዓላማ ጽናት።

ምንም እንኳ ይህ መጽሐፍ «የታሪክ መጽሐፍ» ባይሆንም የኢትዮጵያ ታሪክ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት ታሪክ ነውና የአገራችን ታሪክ ከሰዎች ታሪክ ተነጥሎ ሊታይ የሚችል አይደለም። በየትኛውም አገር ቢሆን ትውልድ የሚቋደሰው በረከት ሁሉ የፋና ወጊዎች ውጤት የሆኑ ግኝቶችን ነው። እንዲህ ዓይነት



ሰዎች ሲረሱ የአገር ቁራሽ እንደ መርሳት ይቈጠራል። እነርሱ በማይታወሱበት ሁኔታ የምንኖረው ኑሮ አሰልቺ ነው። «እነርሱ ያለ እኛ እኛም ያለ እነርሱ ምሉዕነት ይኖረን ይሆን?» ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን።

ይህ የደማቆቻችን የሕይወት ውልብታ የእነዚህ ሰዎች ሙሉ የሕይወት ታሪክ አይደለም። የአንዳንዶቹ ሙሉ የሕይወት ታሪክ ራሱን በቻለ ሙሉ መጽሐፍ ሰፍሯል (ለምሳሌ የከንቲባ ገብሩ ደስታ እና የካፒቴን ዓለማየሁ አበበ እንዲሁም የሌሎች የሕይወት ታሪክ)። እንዲህ ዓይነቶቹንም መጻሕፍት ያገኘናቸውን ያህል ለምንጭነት ተጠቅመናል። **ይህ ውልብታ የደማቆቻችንን ደካማ የሕይወት ጎን በቀጥታ አይዳስስም። ይህ የሆነው ግን እንደ ሰው ደካማ ጎን የላቸውም ለማለት ሳይሆን እንዲህ ዓይነቱን ሒሳዊ ትንተና መስጠት የሚቻለው በሰፊ ጥናት ተደግፎ ሙሉ የሕይወት ታሪክ ሐተታ በሚሰጥበት ሰፊ ሥራ ውስጥ ነው ብለን ስለምናምን ነው።** ይሁን እንጂ አተኩረው ለሚያነቡ ተደራስያን ይህንን ሒስ ሊፈልጉ የሚችሉባቸው ነጥቦች አይታጡም። ይህ መጽሐፍ ቃኝ እንጂ ሐታቲ (የሚያትት) አይደለም። ለዚህ ነው «ውልብታ» ያልነው።

አብረን እንጀምን አብረን እንድመቅ
እግዚአብሔር ይርዳን!

:



www.ethiopianorthodox.org

## ልናውቃቸው የሚገቡን

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፣ የደማቆቹ ቅደም ተከተል ዘመን ቅደም ተከተል (Chronological Order) ነው።

ይህ መጽሐፍ በ160 ዓመታት ውስጥ የታዩ አንዳንድ የኢትዮጵያ ደማቅ ልጆች የሕይወት ውልብታ ነው። ከዚህም የተነሣ በዚህ ቅጽ ያልተካተቱ በርካታ ኢትዮጵያውያን ደማቆች አሉ። ይሁን እንጂ በዚህ ቅጽ ያልተካተቱ አንዳንዶች ደግሞ በቅርቡ በቅጽ ሁለት ይደምቃሉ።

ይህ መጽሐፍ ምንም እንኳ ታሪካዊ ጉዳዮችን የሚጠቃቅስ ቢሆንም የግለሰቦች የሕይወት ውልብታ መጽሐፍ እንጂ «የታሪክ መጽሐፍ» አይደለም።



# እነሆ ደማቆቹ



www.ethiopianorthodox.org



# ኦኔሲሞስ ነሲብ (አባ ገመቹስ)
## 1842 - 1923
## ከባርነት ወደ ላቀ ምሁርነት

ልቤ አታስጨንቀኝ፤ ሆዴም አትጎርብጠኝ
ትንሽ ፋታ ስጠኝ ዕረፍቴን አትንሳኝ
እንዳሻልብ ተወኝ ምድሬን አታስታውሰኝ
ዕልመት አታልብሰኝ
ሆዴ የቻለውን ይዞ ያደረውን
ኀዘኔን ብሶቴን
አህያም አይችለው ጀርባው አይሸከመው
ታዲያ ምን ልሁነው ምኔን ምን ላድርገው

www.ethiopianorthodox.org

በ1842 በቀድሞ አጠራር ኢሉባቦር ክፍለ አገር፣ ሁሩሙ በምትባል ትንሽ መንደር ተወለደ፤ «ስምን መልአክ ያወጣል» እንዲሉ፣ «ሂካ» የተሰኘ የተፀውዖ ስም ተሰጠው። ይህ፣ «ተርጓሚ» ለተሰኘው የአማርኛ ቃል አቻ ቀረቤታ ያለው የኦሮምኛ ስያሜ ከ «ሰውየው» ኋለኛ የሥራ ሕይወቱ ጋር የተጣመረ በመሆኑ በርካቶችን ሳያስደምም አላለፈም። ምዕዋ ዘልቆ በስመ ጥምቀቱ «ኦኔሲሞስ» የሚል መጠሪያ የተሰጠው ሂካ በኦሮምኛ ቋንቋ ቅዱሳት መጻሕፍትንና ሌሎችንም ጽሑፎች በመተርጎም ለቋንቋው ሥነ ጽሑፋዊና ሥነ ልሣናዊ ዕድገት ሁነኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይሁን እንጂ፣ ኦኔሲሞስ ወደዚህ ዐቢይ የትርጉምና ጽሑፍ ሥራ ከመዝለቁ አስቀድሞ መሪርና አስከፊ በሆነ የሕይወት ስርጓጉጥ ውስጥ አልፏል::

ገና የአራት ዓመት ልጅ ሳለ ወላጅ አባቱን ሞት ነጠቀበት። ድንጋጤው በቀሪው ቤተ ሰብና በጨቅላው ሂካ ሕይወት የጨለማ ድባብን አጠላ:: የመከራው ገፈት በዚህ ሳያበቃ ተጨማሪ ስቃይና ኀዘን ወደዚህ ጎጆ መንደርደር ጀመረ::

በዘመኑ የድሃውን ጎተራ እየገለበጠ፣ ከብት በዝርፊያ እየነዳ፣ እንደ ቋያ እሳት ቀዬ እያጋየና የሰፈሩን ማቲ ለባርነት እየዳረገ የሚዘዋወር የሽፍታ መንጋ በሁርሙ መንደር ዘልቆ ነጡን ማመስ ጀመረ። ይኼኔ የሂካ ወላጅ እናት ከዚህ መዓት ልጇን ለመታደግ ሽሽት ገባች:: ሆኖም የዕለቱ ጀምበር ፊት ነስታት ኖሮ ሰይፍ ከሚነቀንቁ የሞት መልእክተኞች ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጠች:: በወቅቱ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ የነበረው ሂካ ያቺን ቅጽበት ከጊዜ በኋላ እንዲህ ያስታውሳታል፦





አንድ ሰው እየተንደረደረ መጣና እጇን በመጎተት ወደ ራሱ ሳበኝ፤ እናቴም የተቀረውን እጄን አጥብቃ በመያዝ፣ «ፈጽሞ አትወስደውም!» ስትል ተከላከለች፤ ይኼኔ ሰውየው ሰይፉን መዘዘና፣ «የማትለቂው ከሆነ ሁለታችሁንም እገድላለሁ!» ሲል ዛተ:: እናቴም፣ «ከሚሞትብኝ ባርነት ቢገባ ይሻላል:: » በማለት እጇን አላላች::

በዚህ ዘግናኝ ሁኔታ ከእናቱ መዳፍ ተመንጭቆ በወንበዴዎች እጅ የወደቀበት ቅጽበት ከቶም ከምናቡ እንዳልተፋቀና ውስጡንም ያባትተው እንደነበረ ፣ በ1886 ባሳተመው መጽሐፍ ውስጥ በጫራት ስንኝ አማካይነት መገንዘብ ይቻላል:: ግጥሙ በባርነት ተፈንግሎ ሳለ ለሚያፈቅራት እናቱ፣ ለትውልድ መንደሩና ለዘመዶቹ ናፍቆት ያሰማው የውስጥ ነዲድና ጥልቅ ኀዘን ነፀብራቅ ይመስላል:: ግርድፍ ትርጉሙ እንዲህ ይነበባል፦

ወዴት እንዳቀናሽ ምነው አልነገርሽኝ
ሩቅ አገር ስትነጉጂ ለምን አልጠራሽኝ
እንዲህ ከመለየት በናፍቆት ተቃጥሎ
እንዲህ ከመራራት በስሜት ነሁልሎ
ምነው በወሰደኝ ያገሬ ወንዝ ባሮ

በባሪያ ፈንጋዮች ታፍኖ ከተወሰደ በኋላ ከቀዬው ብዙም ወዳልራቀ ጎጥ ባርነት ገባ፤ ሳይወድ ታግቶ ስለ ተዳረገበት የባርነት ቀንበር ሲያወሳ፦

ማንኛውም ሰው ባሰኘው መንገድ ያዘኛል፤ ታዲያ የቱን ትዕዛዝ አስቀድሜ የትኛውን እንደማስከትል ግር ይለኛል፣ ይሁን እንጂ በተቻለኝ መጠን ትዕዛዛቱን ሁሉ ለማድረግ እጥራለሁ::





www.ethiopianorthodox.org

ልጁ ከነበረችበት ቦታ ብዙ በማያስጉዝ መንደር ውስጥ መሸጡን የሰማችው እናት፣ ማናቸውንም ዋጋ ከፍላ የሆዷን ፍሬ ለመታደግ ወደ መጀመሪያ ጌታው ዘንድ ተጓዘች፤ አሳዳሪው፣ እሱን ፍለጋ ለሚመጣ ሰው ገጽታውን እንዳያሳይ ቢያስጠነቅቀውም ሂካ እናቱን ባየበት ቅጽበት ያን ትዕዛዝ ለማክበር አቅም አልነበረውም። ይሁን እንጂ ይህ የልጅና የወላጅ ፍቅር የወለደው የድፍረት ድርጊት በብላቴናው ሂካ ላይ ሌላ መዘዝ ጫረበት፤ እናቱ፣ አሳዳሪው በተመነላት ዋጋ ልጇን ለመግዛት ከተስማማች በኋላ ክፍያውን ለመፈፀም ወደ መንደሯ በተመለሰችበት ጊዜ የሂካ ጌታ ልጇን ከቶም መልሳ ወደማታይበትና ራቅ ወዳለ ግዛት በሽያጭ ወረወረው።

በተመሳሳይ የሽያጭ ልውውጥ ከአንዱ አሳዳሪ ወደ ሌላው እየተሸጋገረ ክፉኛ ተጉላልቷል። የምጽዋን ዐፈር ረግጦ ባሪያ እየገዛ ነጻ በሚያወጣ በአንድ የፈረንሳይ ቆንሲል እጅ እስኪገባ ድረስ ሁለቴ ተፈንግሎ አራት ጊዜ እንደ እቃ ተቸርችሯል። የባርነትንም ገፈት ጨልጧል። በተለይም ወደ ምፅዋ ያጓዘው የመጨረሻ አሳዳሪው ክፉና አስጨናቂ ከመሆኑ የተነሳ፣ ሂካ ምሬት ገብቶ የቋጠራት ስንኝ የዚያን ወቅት መራር ገጽታ በከፊልም ቢሆን ታመላክታለች።

ልቤ አታስጨንቀኝ፣ ሆዴም አትጎርብጠኝ
ትንሽ ፋታ ስጠኝ ዕረፍቴን አትንሳኝ
እንዳሽልብ ተወኝ ምድሬን አታስታውሰኝ
ዕልመት አታልብሰኝ
ሆዴ የቻለውን ይዞ ያደረውን
ኀዘኔን ብሶቴን



አህያም አይችለው ጀርባው አይሸከመው
ታዲያ ምን ልሁነው ምኔን ምን ላድርገው




ተነስቼ ብከንፍ ምድራቴን ለቅቄ
ይደርስብኝ ይሆን ፈቀቅ ከማለቴ

ወይስ ተቀምጬ እንባዬ ባነጥበው
ይታዘበኝ ይሆን እንደ ጅል ሰው ቆጥረው

ሲል የልጅነቱን የውስጥ ሕቅታና ናፍቆት ካደገ በኋላ በወረቀት ላይ ቢያነጥብ ማን ሊፈርድበት ይችላል?

መኩሪያ ቡልቻ፣ «*Onesimos Nesib's Pioneering Contributions to Oromo Writing*» በሚለው ጽሑፉ እንደ ገለጸው፣ በዚህ የባሪያ ሽያጭ ዝውውር ወቅት ነበር በአንዱ ጌታው አማካይነት «ነሲብ» የሚል ስም የተሰጠው። በዚያ የ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ፣ ወርነር ሙንዚንገር የተባለ ስዊሳዊ ምሁርና አገር አሳሽ፣ የፈረንሳይ ቆንሲል ሆኖ በምጽዋ ይኖር ነበርና የሂካ የመጨረሻ ጌታ ለዚሁ የፈረንሳይ ቆንሲል በሽያጭ አስተላልፈው፤ ሙንዚንገርም ከባርነት ነፃ በማውጣት ወደ ፒተር ሉንድሃል ሸኘው።

በፒተር ሉንድሃል እጅ መውደቁ ለሂካ የተመቻቸ አጋጣሚን ፈጠረለት፤ ከሞጀመሪያ መምህሩ ከሉንድሃል ዘንድም ቃለ እግዚአብሔርን ጠንቅቆ ለማወቅ የሚያስችለውን እድል አገኘ። ታኅሣሥ 24/1872 ዓ.ም ሉንድሃል የሂካን ሁኔታ አስመልክቶ በጻፈው ማስታወሻ፦

> ከጥቂት ወራት ቆይታ በኋላ ሂካ ክርስቶስን አመነ፤ እናም ተጠመቀ፤ በራሱ ምርጫም፣ ኦኔሲሞስ የተ-ሰኘውን የክርስትና ስም ተቀበለ። ኦኔሲሞስ የልብ ወዳጅ፣ ሊቀርቡት የሚገባ፣ ትሁት፣ ፈጽሞ ደከመኝን የማያውቅ ነው። አሁንማ የአማርኛን መጽሐፍ ቅዱስ ጠንቅቆ ከማንበቡም በላይ በውስጡ ያሉትን ዕውቀቶች ከቅን ልብ ጠልቆ ተረድቷል።



ሲል አብራርቷል።



www.ethiopianorthodox.org

«*The Swedish Mission in Ethiopia*» የተሰኘውን ጽሑፍ የጻፈው ዓለም እሸቴ እንደገለጸው፣ ቀዳሚዎቹ የሉንድሃል ተማሪዎች ኦኔሲሞስን ጨምሮ በቁጥር ስድስት ሲሆኑ፣ ትምህርት ቤቱ፣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ በካታኪዝም፣ በአጠቃላይ ታሪክ፣ በጂኦግራፊ፣ በአርትሜቲክ እና በቋንቋ (አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ስዊድንኛ፣ ጀርመን) ተማሪዎችን ያሠለጥናል፤ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስም እንደ አንድ የማስተማሪያ መጽሐፍ ያገለግላል ሲል ጽፏል::

ኦኔሲሞስ ትምህርት በመቅሰም ረገድ ልቡናው ብሩህ እንደ ነበር በትጋቱና ባስመዘገበው ውጤት አሳይቷል። ታዲያ በዚህ ወጣት ውስጥ ያለውን ዕውቀት የመሻት ጉልበት የተገነዘቡ የውጭ አገር መምህራን ልጁን ምዕዋ በሚገኘው የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ብቻ ሊገቱት አልፈለጉም፤ እናም ለበለጠ ትምህርት ባህር ገምሶ ይጓዝ ዘንድ እድል ከፈቱለት::

ሰኔ 1886 ዓ.ም መድረሻውን ስዊድን በማድረግ የምዕዋን ወደብ ለቀቀ:: አድራሽም ሆነ መንገድ መሪ አልተከ-ተለውም:: በአሌክሳንደሪያ (እስክንድሪያ) በቬይና፣ በበርሊንና በሉቤክ ቀዝፎ ካለፈ በኋላ ባቡር ተሳፍሮ ስቶክሆልም ገባ:: "*Onesimos Nesib*" የተሰኘውን መጽሐፍ የደረሰው ተርፋሳ ዲጋ፣ በኢትዮጵያ ጥናት ተቋም የተዘጋጀውንና ለኅትመት ያል-በቃውን፣ «*Dictionary of Ethiopian Biography*» በመጥቀስ ኦኔሲሞስ የእስካንድኔቪያንን ምድር ለመርገጥ የበቃ የመጀመሪያው የኦሮሞ ተማሪ እንደ ነበር ይነግረናል::




ምዕዋ ሳለ የጀመረው የስዊድን ልሳን ለተከታዩ ትምህርት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ጠለቅ ያለውን የቋንቋ ጥናት ገፋበት፤ በጥቂት



ጊዜ ውስጥም ቋንቋውን አስገበረ:: ከዚያም በትምህርት ቤቱ ወደሚሰጠው መደበኛ ትምህርት ዘለቀ፡ በዚያም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ አጠቃላይ ሳይንስ፣ ጂኦግራፊና ቋንቋን (ላቲን፣ ግሪክና ዕብራይስጥ) በዋነኝነት አጠና:: ቄስ ተስገራ፣ «*Abba Gammechis, Oneesimos Nasib*» በተሰኘ ሥራቸው፣ ኦኔሲሞስ አማርኛን፣ ዐረብኛን የስዊድንና የእንግሊዝኛ ቋንቋዎችን ይናገር እንደ ነበርና ጀርመንኛ ቋንቋንም ማጥናቱን ይነግሩናል:: ኢዶሳ ገመቹስ በጻፈው፣ «*የኦናሲሞስ ነሲብ አጭር የሕይወት ታሪክ*» በተሰኘ ጽሑፍ ደግሞ ትግርኛና ጣሊያንኛ ቋንቋዎችን ይናገር እንደ ነበር ተገልጿል::

ስቶክሆልም በሚገኘው «የሐንሉንድ ሚሽነሪ ትሬኒንግ ኢንስቲቲውት» ከአምስት ዓመት የትምህርት ቆይታ በኋላ ሁለት ስዊድናዊያንን አስከትሎ ስቶክሆልምን በመልቀቅ ወደ አገሩ አቀና:: መስከረም 1873 ምዕዋ ደረሰ፤ ቀደም ሲል በወደብ ከተማ የነበረው የሚሲዮኑ ትምህርት ቤት ከምዕዋ 10 ኪ.ሜ ርቃ በምትገኘው እምኩሉ (እንደ አቶ ገብረመድኅን ሃብተእግዚ አባባል) ተዛውሮ ኖሮ ከባልደረቦቹ ጋር ወዲዚያ አቀና፣ ብዙም ሳይቆይ የአፄ ቴዎድሮስ ጸሐፊ የነበረውንና በወቅቱ በጣቢያው በመምህርነት የሚያገለግለውን የጎጃሙን ተወላጅ የአለቃ ኀይሉን ልጅ፣ የአሥራ ዘጠኝ ዓመቷን ኮረዳ ምሕረት ኀይሉን አገባ::

በእምኩሉ ቆይታው ከማስተማር ባሻገር ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለመሻገር የሚያስችለውን የጉዞ እቅድ ይነድፍ ጀመር:: ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ *Pioneers of Change in Ethiopia* በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ በገለጹት መሠረት በወቅቱ አፄ ዮሐንስ





www.ethiopianorthodox.org

በሚሲዮናውያን ላይ አርገውት በነበረው የእንቅስቃሴ እገዳ ምክንያት ከሰሜን ኢትዮጵያ ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለመዝለቅ መካከለኛ የአገሪቱን ክፍል ሰንጥቆ መጓዝ የማይደፈር በመሆኑ የኦኒሲሞስ ቡድን አቅጣጫውን በሱዳን በኩል በማድረግ ወደ ወለጋ የመግባትን እቅድ ከአምስት ኢትዮጵያዊያንና ከሁለት ስዊድናዊያን ጋር አዘጋጀ:: እቅዱንም በተግባር ለመተርጎም ጉዞ ተጀመረ፤ ብዙ እጅግ ብዙ ተጓዙ:: አያሌ በረሃዎችንም አቆራረጡ:: በቀይ ባሕር የተደረገውን የባሕር ጉዞ ጨምሮ መንገዳቸው ሁለት ወር ፈጀ። በመጨረሻም ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ድንበር ቢቃረ-ቡም በጊዜው በነበረው የአካባቢ ግጭትና የፀጥታ መታወክ ምክንያት ካሰቡት ሳይደርሱ እቅዳቸው ጨነገፈ:: ታዲያ በመገባደጃው ጠርዝ ላይ የውሃ ሽታ በመሆኑ ጥልቅ ሃዘን በሁሉም ላይ አጠላ:: ልባቸው ተሰበረ:: ያም ብቻ አይደለም። የበረሃው ንዳድ ጠንቅ ዕኑ በሆነ ደዌ ሁሉንም ያሰቃይና ያንገላታ ጀመር፡ ከመካከላቸው የቡድኑ መሪ የነበሩ ስዊድናዊው ጂ. ኢ. አርሄኒየስና የኦሮሞው ተወላጅ ወጣቱ ፊሊጶስ በረሐው ውስጥ ሕይወታቸው ሲያልፍ የተረፉት ከብዙ ስቃይና ድካም በኋላ ወደ ምፅዋ ተመለሱ፤ ያም ሆኖ የበረሃው በሽታና መዘዙ ኦኒሲሞስንና ትሩፋኑን ለረጅም ጊዜ የሕማም ስቃይ ዳርጓቸዋል::

የመጀመሪያው ጉዞ በእቅዱ መሰረት ባይከናወንም ኦኒሲሞስ ተስፋ አልቆረጠም፤ በእምኩሉ የማስተማር ሥራውን ቀጠለ። አብሮም የተለያዩ መጻሕፍትን ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ በመመለስ ለተከታዩ ጉዞ ይሰናዳ ጀመር:: በዚህ መካከል ማሠልጠኛ ተቋሙ የመንፈሳዊ



መጻሕፍትን ኅትመት ለማሳደግ በ1878 ዓ.ም አነስተኛ የማተሚያ መኪና ወደ ኢትዮጵያ በማስመጣቱ *100 Songs and Psalms (Galata Waaqayoo Gofta Maccaa)* የተሰኘው የኦኒሲሞስ ሥራ የማተሚያ ቤቱ የመጀመሪያ ሥራ በመሆን የኅትመትን ብርሃን አየ::




www.ethiopianorthodox.org


ሁለት ዓመታት አለፉ:: እንደገና ከጥቂት ሰዎች ጋር የሸዋን ግዛት አቋርጦ ወደ ምዕራብ ለማለፍ ጥረት ቢያ-ደርግም የይለፍ ወረቀት በመነፈጉ ወደ እምኩሉ መመለስ ግዴታ ሆነበት:: ተደጋጋሚ የሆነው ይህ ስኬት አልባ ጉዞ ብዙዎችን ሲያሳዝን የኦኒሲሞስን እምነት ግን በአያሌው ፈትኗል:: በኦሮምኛ ሥነ ጽሑፍ የኦኒሲሞን ፈር ቀዳጅ አስተዋጽኦ ያስተነተነው መኩሪያ ቡልቻ፣ ይህንን ጉዞ በሚመለከት ተከታዩን ሐሳብ ሰንዝሯል፦ ከምጽዋ በመነሣት አንዴ በሱዳን፣ አንዴ ደግሞ በጅቡቲ፣ ሌላ ጊዜ በመሀል አገር በማድረግ ከሚሲዮናዊያኑ ጋር ወደ ወለጋ ለመዝለቅ ያደረገው ያላሰለሰ ጥረት በመሃል አገር ሹሞች መጨናገፉ የኦኒሲሞስን ልብ በእጅጉ አድምቷል። ይህንም ሰኔ 16 ቀን 1879 ዓ.ም. ከጻፈው ማስታወሻ መገንዘብ ይቻላል፦

> አሁንም እንኳ እንደ አመጸኞችና ረብሻ ቀስቃሾች ተቆጥረን መባረራችን ያሳዝናል... ለረጅም ጊዜ ስንናፍቀው ወደ ቆየነው ምድራችን እንሄዳለን ብለን ተደስተንና ተስፋም አድርገን ነበር።

ያም ሆኖ እንኳ ተስፋ ቆርጦ አልተቀመጠም:: ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቀውንና እጅግ አድካሚ የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ ይከውን ጀመር:: ቀደም ሲል፣ አራቱ ወንጌላትን ጨምሮ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሩፎ፣ በዘነበና በሉድዊሽ ክራፕፍ አማካይነት ወደ ኦሮምኛ የተተረጎሙ ቢሆንም፣ እንደ ኦኒሲሞስ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ለመተርጎም የተነሳ ግን አልነበረም:: ኦኒሲሞስ ይህን ሥራ ከመጀመሩ አስቀድሞ የተለያዩ መጻሕፍትን የጻፈና ወደ ኦሮምኛ ቋንቋም የተረጎመ ሲሆን በወቅቱ፣



አቻና ተስማሚ ቃላትን በማፍለቅ ረገድ ልዩ የቋንቋ ተሰጥኦ በነበራት በአስቴር ገኖ ተራዳኢነት ተግባሩን ከግቡ ሊያደርስ በቅቷል።

አስቴር ገኖ በ1892 ስዊዘርላድ የታተመውን የኦኔሲሞስ የኦሮምኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ በእጅጉ የረዳች የቋንቋ ተሰጥኦ የነበራትና ልበ ብሩህ ኢትዮጵያዊ ነበረች። ምንም እንኳ ነጻ ከሆኑ ቤተሰብ ብትወለድም በሊሙ ንጉሥ ባርነት ተግዛ ለሽያጭ ወደ አረብ ምድር ስትጓዝ አንድ የጣሊያን መርከብ የተሳፈረችበትን ጀልባ አስቁሞ የስዊድን ኤቫንጀሊካል ሚሽን ወደ ነበረበት ኤርትራ ምድር ይወስዳታል። እዚያም እምኩሉ በሚገኘው የሚሲዮናውያኑ ትምህርት ቤት እየተማረች እያለ የብሩህ አዕምሮ ባለስጦታነቷንና ለኦሮምኛ ቋንቋ ያላትን የተለየ ዝንባሌ ለማወቅ ኦኔሲሞስ ጊዜ አልፈጀበትም ነበር። አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት አስቴር ከኦኔሲሞስም ጋር ሆና ለብቻዋ በርካታ ባሕላዊ የኦሮምኛ ተረትና ምሳሌዎች፣ መዝሙሮችና የመዝሙር መጻሕፍት አዘጋጅታለች። በ18ኛው መቶ መገባደጃም ከኦኔሲሞስና ከሌሎች የኦሮሞ ተወላጆች ጋር በመሆን ከኤርትራ ወደ ወለጋ በመሄድና ትምህርት ቤት በጋራ በመክፈት በነቀምት ከተማ በአስተማሪነት አገልግላለች። ከፍተኛ ጥንቃቄ የጠየቀው ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ ከፍጻሜ ለመድረስ በርካታ ዓመታትን ወስዷል። የአዲስ ኪዳን ትርጉም ከሰባት ዓመታት ጽኑ ምጥ በኋላ ተወለደ፤ ብዙም ሳይቆይ የብሉይ ኪዳን ትርጉም ተጀምሮ ከብዙ ድካምና ጥረት በኋላ ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ በተፀነሰ በ13ኛ ዓመቱ ለፍሬ በቃ። የመጽሐፉ መጠናቀቅ ለብዙዎች ደስታን ከማጎናጸፍ ባለፈ ለተከታዩ የወንጌል ጉዞ የውስጥ ጥንካሬን፣ በተለይም በገዛ ቋንቋው መጽሐፉ ለቀረበለት ሕዝብ የእውነትና የዕውቀትን



ፈለግ በማመላከት ረገድ ዐቢይ የሆነውን ሚና ተጫውቷል። ይህንን መጽሐፍ ለማሳተምና የፈደል ለቀማውን ሥራ ለመከታተል ኦኔሲሞስ



ወደ ስዊዘርላንድ መሔድና ዘጠኝ ወር ያህል መቆየት ነበረበት። ትምህርቱም እየተካሄደ ሳለ ቀደም ብሎ ከፍተኛ ትምህርት የተማረባትን ስዊድንን ለሁለተኛና ለመጨረሻ ጊዜ ጎበኘ። ዶ/ር ድርሻዬ መንበሩ ስለ ኦኔሲሞስ ነሲብ አሙር የሕይወትና የአገልግሎት ታሪክ በጻፉት ጽሑፍ እንደተጠቀሰው፣ ኦኔሲሞስ ይህንን የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ኅትመት ክትትል ዳር ሳያደርስ በኤርትራ እምኩሉ ትቶአቸው ከመጣው ቤተ ሰቡ ክፉ ወሬ ደረሰው። የመጀመሪያ ሚስቱ የነበረችው የጎጃሚ ተወላጅ ምሕረት ከልጅ መውለድ ጋር በተያያዘ ሞታበት ስለ ነበር፣ የወለጋ ተወላጅ የሆነችውን ሊዲያ ደንቦን አግብቶ ይኖር ነበር። ወደ ስዊዘርላንድ ከሪሽና ለኅትመት ዘልቆ እያለ የትንሽ ሴት ልጁን ሞትና የሁለቱን ትልልቅ ልጆቹን በጠና መታመም ሲሰማ ተግባሩን አቋርጦ ፈቱን ወደ ሊዲያና ወደ ኤርትራ ሊያቀና ሲዘጋጅ ባለቤቱ ሊዲያ በፍጹም ሥራውን አቋርጦ መመለስ እንደሌለበት በደብዳቤ አሳወቀችው፤ ከዚህም የተነሳ በባለሙያዎች በድጋሚ ተሻሽሎ ለመታተም እስከ-ተወሰነበት ጊዜ ድረስ ለሰባ አምስት ዓመት ያገለገለውን የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትመት አጠናቆ ወደ አገሩ ተመለሰ።

ቀደም ሲል ወደ ምዕራብ ለመዝለቅ የተደረገው ተደጋጋሚ ሙከራ እልባት ላይ ደረሰ። ሙሉው የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ተጠናቅቆ እንዳበቃ ኦኔሲሞስ ጥቂት ባልደረቦቹን ይዞ ታኅሣሥ 1895 ዓ.ም መንገዱን ወደ አዲስ አበባ አቀና፤ ከረጅምና አድካሚ ጉዞ በኋላ 1896 ዓ.ም መባቻ ላይ አዲስ አበባ ደረሱ። በወቅቱ አፄ ምኒሊክ ወደ ሀለታ ወርደው ስለ ነበር እስኪመለሱ ድረስ አዲስ አበባ ተቀምጦ መጠበቅ ግድ ሆነበት፤በነዚያ የጥበቃ ቀናት መካከል ግን ሥራ ፈቶ



አልተቀመጠም፤ አቡነ ማቴዎስ ዘንድ በመቅረብ፣ «የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች» የተሰኘ ሥራውን አበረከተ። አቡኑም፣ «መልካም!መልካም!» የተ-




www.ethiopianorthodox.org

ሰኘውን ቃል ሰነዘሩ። ቀጥሎም በኦሮምኛ የተተረጎመውን መጽሐፍ ቅዱስ አቀረበ። ንጉሡ ወደ አዲስ አበባ እስኪመለሱም ድረስ አቡኑን በተደጋጋሚ በመጎብኘት ስለ መንፈሳዊ ጉዳዮች አወግተዋል።

አፄ ምኒልክ ወደ አዲስ አበባ እንደተመለሱ አቡነ ማቴዎስ፣ ኦኔሲሞስ ነሲብ የመጣበትን ጉዳይ ለንጉሡ ያቀርብ ዘንድ ሁኔታውን አመቻቹ። ኦኔሲሞስም ወደ ወለጋ ዘልቆ ለማስተማር የሚያስችለውን ፈቃድ ያገኝ ዘንድ ንጉሡን ጠየቀ። ከመጀመሪያው እትም አንዱ የሆነውን የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ለአፄ ምኒልክ ገፀ በረከት አቀረበላቸው። ንጉሡም በደስታ ተቀበሉ። ነጋድራስ ኀይለ ጊዮርጊስንም ባልደረባ በመስጠት የሚገጥመውን ችግር በእርሳቸው አማካይነት እንዲያቀርብ ትእዛዙ ሰጡ። ተከታዩን የይለፍ ደብዳቤም ሰጧቸው፦

ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ይህን ደብዳቤ ይዞ ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር አገር ለሚያቀናው ኦኔሲሞስ ፣ ከርሱ ጋር ላሉ አስር ሰዎችና ሦስት ጠባቂዎቻቸው ፈቃድ ሰጥተናቸዋልና ማንም መንገዳቸው ላይ አይቁም

ምንም እንኳ አቡነ ማቴዎስ ኦኔሲሞስ የወንጌላውያን እምነት ተከታይ እንደሆነ ቢያውቁም ወደ ወለጋ ዘልቆ ቃለ ወንጌልን በህዝቡ ቋንቋ ያቀርብ ዘንድ የፈቀዱ ይመስላል። ኦኔሲሞስ እንደሚለው፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሁለቱም የጋራ ሃብታቸው እንደሆነ ተገንዝበዋል። ታዲያ አቡኑ በወል ከሚያስተሳስራቸው ከዚህ መጽሐፍ ሂዶ እንዲያስተምር የፈቀዱ ቢሆንም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የተፋታ





ትምህርት እንዳይሰጥ ግን አዘውታል። ለዚህም ይመስላል ተከታዩን ደብዳቤ ወደ ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ዘንድ የሰደዱት፦

..እጅግ ለተከበርከውና ለተወደድከው ደጃዝማጅ ገብረ እግዚአብሔር እንዴት አለህ? እኔ የማርቆስ አምላክ ይመስገን ደህና ነኝ። ይህ ከወደብ የመጣው ኦኔሲሞስ ወደ እኛ መጥቶ እንዲያስተምር ጠይቆናል። ከቤተ ክርስቲያናችን ትምህርትና እምነት የተለየ ጉዳይ አስተምሮ እንደሆነ እንድናውቀው አድርግ። ነገር ግን ከኛ ትምህርትና እምነት ያላፈነገጠ ትምህርት የሚሰጥ ከሆነ፣ ይቀጥል፤ማንም አንዳች አይበለው።

የመጀመሪያ ጣቢያውን ነቀምት አደረገ። እንዳሰበው፣ ነቀምቴ አማካይ ስፍራ ብትሆንም የደጃዝማች ገብረእግዚአብሔር መቀመጫ ነጀ በመሆኑ በ1896 ዓ.ም. ወደዚያው አቀና። ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔርም ለቡድኑ ከፍ ያለ አቀባበል አደረጉለት። ኦኔሲሞስም ደስተኛ የሆነበትን አንድ የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ አበረከተላቸው። ደጃዝማቹም ከሌሎች መጻሕፍት ይልቅ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ምርጫቸው እንደሆነ ተናገሩ። ባይሩ ታፍላ እንደሚለው፣ አፄ ምኒልክ 1881 ዓ.ም የአማርኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ለደጃዝማች ልከውላቸዋል። ደጃዝማቹ በተለይ የኦሮምኛው መጽሐፍ ቅዱስ መምጣት በግዛታቸው ለሚገኙ ተወላጆች በረከት እንደሚሆን በመግለጽ ከቀረጥ ነፃ የሆነ መሬት ሰጧቸው።

ከደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር የተደረገለት አቀራረብ የሞቀ ከመሆኑ የተነሣ፣ የቤት መሥሪያ ቦታ ተሰጠው፣ እዚያው ቦታ ላይ ትምህርት ቤት ከፍቶ የአካባቢውን ልጆችና ወጣቶች ሰብስቦ ማስተማር ጀመረ። የአገሬው





www.ethiopianorthodox.org

ሰው ለትምህርት ያለውን ተነሳሽነት በማየትም፣ «መኸሩ ብዙ፣ ሠራተኞች ጥቂት» በመሆናቸው ከወደ እምኩሉ ተጨማሪ ሠራተኞች እንዲላኩለት ጠየቀ። ለዚህም ያገኘው አዎንታዊ ምላሽ የኦኒሲሞንና የመሰሎቹን ወንጌላውያን እንቅስቃሴ ገሃድ እያደረገው መጣ። ይህ ድርጊቱም ስላልተወደደለት የስደት ዒላማ ሆነ። አስቀድሞ በርታ ያለትም አቡን ፊታቸውን አዞሩበት። ወለጋ መግባቱ፣ እንዲሁም የቀለምና የሃይማኖት ትምህርትን ለማስተማር እድል በማግኘቱ ደስተኛ ሆኖ ለጥቂት ጊዜያት ቢቆይም በእምነቱ ሳቢያ የደረሰበት ስደት ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ ተቃዋሚዎቹ ከወለጋ አዲስ አበባ እየመላለሱ ሙግት ከመግጠምም አልፈው ንብረቱ እንዲወረስና በእግረ ሙቅም ታስሮ ወህኒ እንዲወርድ አድርጎታል። በአጭሩ ኦኒሲሞስ ለእምነቱም ሆነ ለነፃው ኑሮ አንጻራዊ ዕረፍት ያገኘው በ1909 አካባቢ ከልጅ ኢያሱ ባገኘው የእምነት ነጻነት በኋላ ነው።

ኦኒሲሞስ ከወንጌል ሥራው በተጓዳኝ የቀለም ትምህርት፣ እንዲሁም ከነበረው መጠነኛ የህክምና እውቀት በመነሳት ህሙማን በነጻ ማገልገል ጀመረ። እንደዚሁ ከሁድን ጋር አብረው የመጡት አስቴርና ፌበን የአሮሞ መኳንንት ሚስቶችን በየቤታቸው እየሄዱ ስለ ቤት አያያዝና ስለ ልጆች አስተዳደግ ያሠለጠኗቸው፣ ፊደል ያስቆጥሯቸውና ወንጌልንም ያስተምሯቸው ጀመር።

ምንም እንኳ መደበኛ ት/ቤት ባይኖርም፣ ኦኒሲሞስ የባላባት ልጆችን በመሰብሰብ መጻፍና ማንበብ አብሮም ወንጌልን ማስተማር ቀጠለ። እንደ አንድ ማስታወሻው መሠረት፣ በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ጊዜአት የተማሪዎች ቁጥር ከ20 የማይበልጥ ቢሆንም በ1887 ዓ.ም ግን ወደ 100 አድጓል። በዚህ መደበኛ ባልሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ የደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔርን ልጅ ጨምሮ ሦስት





አገልጋዮቻቸው በኦኒሲሞስ ስር ተምረዋል። በርካታ ልጆችም በአማርኛ የተጻፉ የወንጌል ክፍሎችን ለማንበብ በቅተዋል፤ ይህም ኦኒሲሞስ በማኅበረ ሰቡ ዘንድ የነበረውን መከበር ከፍ አድርጓል።

የትምህርቱ አሰጣጥ እየሰፋ በሄደበት ሰዓት ላይ የሁኔታው አካሄድ ያላስደሰታቸው የአካባቢው ካህናት አቡነ ማቴዎስ ዘንድ ያስኬደውን ክስ አቀረቡበት። ተቃውሞ ማስፈራራትና ዛቻ በተደጋጋሚ ይሰነዘርበት ጀመር፤ በዚህም ተሰቃይቷል፣ ተንገላቷልም። ይሁን እንጂ በእነዚህ ሁሉ ማዕበላት መካከል በመቅዘፍ ከወዳጆቹ ጋር ሆኖ በአካባቢውና አልፎም ራቅ ካለ ሥፍራ ለመጡ በርካታ ሰዎች ያበረከተው አስተዋጽኦ የተለያዩ ለውጦችን በኅብረተሰቡ ዘንድ ማምጣቱ አልቀረም። ይህንንም ከተከታዩ ደብዳቤ መገንዘብ ይቻላል።

.. በጋብቻ ላይ የሚፈጸም ጋብቻን እና በአካባቢው የሚታዩ ጎጂ ልምዶችን አጥብቀን ተፋልመናል፤ እናም በዚህ በኩል ያደረግነው ትግል ተሳክቶልናል። ከዚህ ሌላ በኅብረተሰቡ መካከል ይዘወተር የነበረው የጥንቆላ፣ የድግምት፣ ለክፉ መናፍስ መሥዋዕት የማቅረብ ልማድ፣ ሐሰተኛ ምስክርነት፣ ውሸትና ሌላም ጎጂ ልምዶች ከዓመት ወደ ዓመት እየቀነሱ መጥተዋል።

ሲል ጽፏል።

ታዲያ በነዚህ ሁሉ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ትግሎች መካከል በጽናት የተራመደ፣ ስደት፣ ግዞትና መገፋት ቢፈራረቁበትም እስከ መጨረሻዋ ርምጃ ድረስ የተጓዘ፣ ራሱንም ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ ለውጥ የሰጠ ይህ ታላቅ ሰው የሥጋ ዕረፍቱ እለተ ሰንበት፣ በሰማንያ አንድ ዓመቱ በወርኀ ሰኔ





www.ethiopianorthodox.org

1923 ዓ.ም. ሆነ። በዕለቱ የወንጌል ስብከት ተረኛ ስለ ነበር እንደ ወትሮው በየመንገዱ ለሰዎች ሰላምታን ሳይሰጥ በጥድፊያ ወደ ቤተ ክርስቲያን አመራ። አውቆታል፤ ሰኞን እንደማያይ፤ ደግሞም ይህንን ለቅርቦቹ ሰዎች ተናግሮታል። እናም የልቡ ድካም ቤተ ክርስቲያን አላደረሰውም፤ እዚያው እደጅ ሰላሙ አካባቢ ወዳለው ዶ/ር ስደርስትሮም ቤት አቀና፤ ይሄኛው ህመሙ ግን የመጨረሻ ነበረና ትንፋሹን በዚያው ቋጠረ። ነፃው ኦኔሲሞስ የቀዳሚውንም ሆነ የኋለኛውን ስሙን ትርጉም በሚገባ ኖሮ አለፈ። ኦኔሲሞስ የሚለው የተጸውዖ ስም የግሪክ ቃል ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ የምናገኘው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር አብሮ ታስሮ የነበረ አንድ ባሪያ ሲጠራበት ሲሆን ትርጓሜውም «ጠቃሚው» ማለት ነው። ታዲያ በስተኋላ ኦኔሲሞስ የሆነው የቀድሞው ሂካ ሁለቱም የስያሜው ትርጉም አንድ ላይ ቢነበብ «ጠቃሚው ተርጓሚ» የሚል ሲሆን ይህም የዚህን ታላቅ ሰው የሰማኒያ አንድ ዓመት ሙሉ የሕይወት ታሪክ የሚቀነብብ ወይም በአጭሩ የሚገልጽ ሆኖ እናገኘዋለን።

## መወድስ

በባሪያ ፊንጋይ ሂካ ተግዞ
ከናቱ ጉያ በግድ ተመዞ
ከፊንጋይ ፊንጋይ እየዋተተ
ባሮን ተሻግሮ ተንከራተተ
አምላክ ዕድሉን ከሩቅ አየና
ለወገኖቹ አረገው ፋና





## ትምህርተ ውልብታ

ሰዎችን የሚንቅ ሥርዓት በግለሰቦች ውስጥ ያለውን እምቅና አገር ጠቃሚ ዕውቀት አብሮ ይንቃል፤

ታላቅ ሥራ ለመሥራት ከትልቅ መወለድ ሳይሆን በሕይወት ተመክሮ ትልቅ ሆኖ ማደግን ይጠይቃል፤





www.ethiopianorthodox.org

## የውልብታ ምንጭ


Baheru Zewde. *Pioneers of change in Ethiopia, The Reformist Intellectuals of the Early Twentieth Century,* Oxford, Athens, Addis Ababa, 2002.

Dirshaye Menberu *Onesimus Nesib c. 1856 to 1931 Ethiopian Evangelical Church Mekane Yesus (EECMY) Ethiopia*

*Encyclopaedia Aethiopica, vol. 1, "Aster Ganno," edited by Siegbert Uhlig, pp. 387,388. Wiesbaden: Harrassowitz.*

Gustav Aren, *Evangelical Pioneers in Ethiopia: Origins of the Evangelical Church Mekane Yesus* (Uppsala: Offset center ab, April 1978.

Gustav Aren, *Envoys of the Gospel in Ethiopia (EFS forlaget Stockholm: the Evangelical Church Mekane Yesus Addis Ababa, 1999).*

*Mekuria Bulcha Onesimos Nesib's Pioneering Contributions to Oromo Writing, University of Uppsala, Sweden, in Nordic Journal of African Studies 4(1): 36 – 59 (1995)*

Onesimos Nesib, *The Oromo Spelling Book* Monkullo, 1894

Terfasa Diga, *Onesimos Nesib, A Short Biography of Onesimos Nesib 1850 – 1931,* Addis Abab 1999

Tesgara Hirphoo, *Abba Gamachiis, Oneesimos Nasimos Nasib,* Hermannsburg, Amajjii 1999

http://en.wikipedia.org/wiki/Aster_Ganno






## የአንባቢው የግል ማስታወሻ






www.ethiopianorthodox.org







www.ethiopianorthodox.org

# ፪



## ከንቲባ ገብሩ ደስታ
## 1848 ፡- 1942
## "የአለቃ ኅባው መዝገብ!"

*ሥራ ሕይወት መሆኑን ተማርሁና ኑሮዬን ማቅናት ቻልኩ*

ስድስት ዘመነ መንግሥታትን ዐይተው አራቱን (ዐፄ ምኒልክን፣ ልጅ ኢያሱን፣ ንግሥት ዘውዲቱን፣ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴን) በተለያየ የኀላፊነት መስክ በማገልገል በ1942 ያረፉት ክንቲባ ገብሩ፣ በመሳፍንት አገዛዝ ማክተሚያ ላይ ከጎንደር የሦስት ቀን መንገድ ርቃ በምትገኘዋ አለፋ ጣቁሳ ጋዝጌ ሲወለዱ ወላጆቻቸው ያወጡላቸው ስም "ጎባው"[1] የተሰኘ ነበረ።

በወቅቱ፣ "በሥልጣን ይገባኛል" ሳቢያ፣ መሳፍንቱ ጎራ ከፍለው በሚያካሄዱት መቈራቈስ አንዱን መስፍን ወግና ውጊያ የሚወርደው ወታደር፣ ዐልፎ ባገደመበት መንደር የሚያገኘውን ጎጆ በእሳት እያጋየ፣ ከብት እየዘረፈና ሊማት እያራቈተ በመዝለቁ ገበሬው ለአስከፊ ሥቃይ ዐልፎም ለቸነፈርና ለረኀብ መጋለጡ አልቀረም። እንደ ኮሎኔል ዳዊት ገብሩ አገላለጽ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ሥልጣን ሲይዙ የጎባው /የገብሩ/ እድሜ አንድ ሱባዔ[2] ደፍኗል። የጎባው ወላጆች እንደ ማናቸውም የመንደሩ ገበሬዎች የዘረፋውና የጥቃቱ ሰለባ በመሆናቸው፣ በሕዝቡ ላይ የረበበው ድኽነት እነርሱንም መጫኑ አልቀረም።

ጎባው የዐሥር ዓመት ልጅ ሳሉ፣ ከወላጅ አባታቸው ደስታ ወልደ እሜይ ጋር ወደ ደንቢያ አቀኑ። ይሁን እንጂ ዐፄ ቴዎድሮስ በ1848 ደንቢያን መትተው የአገሬው ከብት በታጣቂ በመዘረፉ ሀብት ንብረት ያጣውን ነዋሪ ችግርና ረኀብ ተፈራርቀው ጎሳሰሙት። ደስታ ወልደ እሜይም በአገር ላይ ከመጣው ከዚህ ሥቃይ ሊያመልጡ አልቻሉም። ሀብት ንብረታቸውን ለዘራፊዎች ገብሩ፤ ልጆቻቸውንም በየአዝማዱ ቤት መበተን ግድ ሆነባቸው። በዚያን ጊዜ ነበር የ11 ዓመቱ ጎባው የዐፄ ቴዎድሮስ የጦር ሻለቃ ለነበሩት ለአጎታቸው ለአቶ ውቤ በዐደራ የተሰጡት።

የውቤ ቤት ለወጣቱ ጎባው ምቹ አልነበረም። ጎባው አድገው፣ "ክንቲባ ገብሩ"

---

[1] ጎባው ማለት በጎንደርና በጎጃም አካባቢ «ከፍ ያለው» እንደ ማለት ነው። [2] ሱባዔ ሰባት ቍጥርን የሚያመለክት ቃል ነው



ከተሰኙ በኋላ ስላለፈው ዘመናቸው በተለይም ስለ ውቤ ቤት ክራሞት አንሥተው ሲያወሱ፣ "የመከራ ጊዜ" በማለት ነበር የሚያስታውሱት። ይሁን እንጂ በውቤ ቤት ለአንድ ዐመት ያህል የቀለም ትምህርት ቀስመዋል። ሁኔታዎች ከዕለት ወደ ዕለት እየከፉ በመምጣታቸው የ12 ዓመቱ ጎባው እግር ወደ መሪቸው እብስ አለ። ያጎታቸውን ቤት ለቅቀው ተሰደዱ። ታዲያ ያች ውሳኔ ለጎባው የሕይወት አቅጣጫ ፈር ቀዳጅ ሆና ሁነኛ ለውጥ አመጣች።

አቤት ባዮች ጉዳያቸውን ከንጉሡ ችሎት ለማድረስ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ወደ ደብረ ታቦር ይተምማሉ፤ እናም ወጣቱ ጎባው ፍትሕ ፈላጊውን ተቀላቅለው በወቅቱ የንጉሡ መቀመጫ ወደ ነበረችው ወደ ደብረ ታቦር አቀኑ። "የወንጌል እምነት እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ" የተሰኘውን የታሪክ መጽሐፍ የጻፉት ፊቃዱ ጉርሜሳ ስለዚሁ ጉዳይ ሲያወሱ፣ "በልጅነቱ ችግረኛ ስለ ነበር ዐፄ ቴዎድሮስ ለድኾች እንደሚመጸውቱ ሰምቶ ወደ ደብረ ታቦር ይጓዙ የነበሩ ሌሎች ችግረኞችን ተከትሎ ግቢው ደረሰ። ከበርካታ ሰዎች ጋር ተኮልኩሎም የንጉሡን ድርጎ ይቀበል ጀመር፤ በዚያም ቫልድሜየር የተባለ የሁለ ገብ ሚሲዮናዊ ባልደረባ ይህን ወጣት አይቶ ስላዘነለት አስጠግቶ እያበላ፣ እያጠጣ፣ ማንበብና መጻፍ እያስተማረ አሳደገው። የሌሎች አስተማሪም አደረገው። ከዚያም ቫልድሜየር የዐፄ ቴዎድሮስ የቅርብ ወዳጅ ስለ ነበረ ዘወትር ከንጉሡ አይለይም ነበር። ጎባውም አዘውትሮ ከሁለቱም ጋር ይሆን ነበር። በ1868 ዓ.ም. ከመቅደላው ጦርነት በኋላ ሚሲዮናውያኑ የአበሻን አገር ለቅቀው ወደ ኢየሩሳሌም ሲያመሩ ጎባውና ሌሎች ሁለት ልጆችን አስከትለው ሄዱ። ጎባውና ሁለቱ ልጆች ኢየሩሳሌም ወደ ነበረው የሳሙኤል ጎባት ትምህርት ቤት ገብተው ለመማር ዕድል አገኙ።.. ሲል ዘግቧል። ታሪክ ጸሓፊው ጉስታብ አሬን በበኩሉ፣ "Envoys of the Gospel in Ethiopia" በተባለው መጽሐፍ እንደ ተረከው ፣ ጀርመናዊው «ባለ እጅና» የቴዎድሮስ ባለሟል ቴዎፍሎስ ቫልድሜየር፣ የዐሥራ አንድ ዓመቱን



www.ethiopianorthodox.org

ልጅ ኀባው ደስታን ከመቅደላ ውድቀት በኋላም ወደ ኢየሩሳሊም ደብተ እንደ ተጓዘ ዘግቧል። የከንቲባ ገብሩ ልጅ ኮሎኔል ዳዊት ደግሞ

"...ኀባው ደስታም ከአቤት ባዮች ጋር ወደ ቤተ መንግሥቱ ሄደው ድርጎ ለመቀበል ተኮለኮሉ። በዚህ ጊዜ አቶ ዮሴፍ ቤል የተባለ ሰው የተኮለኮሉትን አይቶ ኀባው ደስ ስላሉት መርጦ ለአንድ ሚሲዮናዊ አስረከባቸው. . . ለኀባው ያቺ ቀን ታላቅ ዕለት ሆነች። ልብስና ምግብ እየተቀበሉ ንባብና ጽሕፈት በነጻ እየተማሩ ሌሎቹንም እንዲያስተምሩ ተደረገ። ቫልድሜየር ከንጉሡ ጋር በሚጓዙበትና ወንጌልን ለማስተማር በተፈቀደበት ቦታ ሁሉ በሚዘዋወሩበት ጊዜ ዐብረው ሲሄዱ ቈይተው ከመቅደላው ጦርነት በኋላ በ1861 ከሁለት ሌሎች ኢትዮጵያውያን፣ ከኃይሉ ወሰንና ከሰንበቱ ዳንኤል ጋር በሚሲዮኑ ወደ ኢየሩሳሊም ተላኩ።" በማለት ያወሳሉ።

ቫልድሜየር ወጣቶቹን ኢየሩሳሊም በሚገኘው የሳሙኤል ጎባት ትምህርት ቤት ላኳቸው። በዚያም በቀለም፣ በሙያና በቋንቋ ትምህርት እየሠለጠኑ ለከፍተኛ ትምህርት ይዘጋጁ ጀመር። ኀባው የኢየሩሳሊም ቈይታቸውን እንዲ ያስታውሳሉ፦

"ኢየሩሳሊም ትምህርት ቤት እንደ ገባሁ ሰሞን ከተማሪዎች ጋር የደረቀ ፍግ በአካፋ እየዛቅን በሚገፋ ጋሪ ወደየትክልቱ እንድናፈስ ታዘዝን። ተማሪዎቹ የለመዱት ሥራ ስለ ነበር እየተዝናኑ እየተጫወቱ ይሠራሉ። የክፍል አለቃዬ መጣና፣ ኀባው አትሠራም እንዴ? ቢለኝ፣ እኔ ፍግ ለመዛቅ አልመጣሁም ለመማር እንጂ! ብዬ መለስኩለት። የክፍል አለቃዬ ይህንኑ ሄዶ ለዋናው አስተዳደር ነገራቸው። እሳቸውም፣ ተዉት ግድ የለም እሱ የመጣው ሥራ መሥራት ካልለመዱት አገር ስለ ሆነ እስኪላመድ ድረስ አትንኩት ብለው ሲናገሩ ሰማሁ። እኔም ጥቂት ደቂቃዎች ከቈየሁ በኋላ ቶሎ ኘና የሚገፋውን ጋሪና አካፋዬን ይዤ እንደ ጓደኞቼ እየተሻማሁ መሥራት ጀመርሁ። ከዚያ በኋላ ሥራ ሕይወት መሆኑን ተማርሁና ኑሮዬን ማቅናት ቻልኩ"



ከኢየሩሳሊም የትምህርት ቈይታ በኋላ ኀባው በ1864 ዓ.ም. ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ስዊድን ተላኩ። ከዚያም በመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕም ሥራ ክራፍ የተባለ ጀርመናዊን ለመርዳት ወደ ሹተንበርግ አቀኑ። ፍቃዱ ይህን ሁኔታ ሲያብራራ፣

በ1872 ዓ.ም. "ኀባውና ሌሎች ሁለት ተማሪዎች ወደ አውሮጳ ሄደው ትምህርታቸውን ቅዱስ ክሪሾና ትምህርት ቤት እንዲከታተሉ ተደረገ። ከእነርሱም መካከል ኀባው በ1876 ዓ.ም. በነገረ መለኮት ትምህርት በዲፕሎማ ተመረቀ። ከዚያም ወደ አገሩ ለመመለስ ቢፈልግም፣ አበሻ ከግብጽ ጋር ያደርግ በነበረው ጦርነት ሳቢያ መንገዱ አስተማማኝ ባለ መሆኑ ሉድዊክ ክራፍ ወደ ነበረበት ወደ ሹተንበርግ ሄዶ በዐማርኛ ቋንቋ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕም ዕርማት ለጥቂት ጊዜ ሲሠራ ቆየ። ከዚያም በ1879 ዓ.ም. ወደ አገሩ ተመለሰ" በማለት ገልጿል።

ኀባው በምጽዋ፣ በሃማሴን፣ በሠራዬና በአድዋ አቋራርጠው አዘዞ ገቡ። ወደ አገር ቤት እንደ ተመለሱ የገጠማቸውን ሁኔታ በአንደኛው ማስታወሻቸው እንዲህ በማለት አስፍረውታል፤ "እናቴ ወ/ሮ ትርንጎ ወልደ ተክሌ ልጅዎ መጥተዋልና አዘዞ ነይ ተብለው መጡና ትክ ብለው ከተመለከቱኝ በኋላ ልጄን የማስታውስበት ምልክት አለ አሉና ከትከሻዬ ከአንገቴ ሥር መዳሰስ ጀመሩ። የሚፈልጉትንም እንደ ኪንታሮት ያለች ምልክት ዳብሰው ሲያገኙ፣ «ኀባው!» ብለው አገላብጠው ሳሙኝ፣ አንገቴንም ዐቅፈው ለብዙ ደቂቃዎች አለቀሱ። ወንድሞቼን ብጠይቅ ሁሉም አልቀዋል አሉኝ። በዕድሜ ቅርብ ጓደኛዬ የነበረው ካሣሁን ደስታ የሚባለውም በመሞቱ በጣም ዐዘንሁ። ከቤተ ሰቦቼ ከተለየሁ ዐሥራ ዐምስት ዓመት ያልፋል። ከዚያ በኋላ ዘመድ ተሰብስቦ ድግስ ተደገሰ።"

ከጥቂት ቈይታ በኋላም ቤተ እስራኤላውያኑን ለማስተማር አዘዞ ላይ



www.ethiopianorthodox.org

ትምህርት ቤት ከፈቱ። ይሁንና የሥራቸው ሁኔታ እንዳሰቡት መሥመር ይዞ ሊዘልቅ አልቻለም። ከአካባቢው ካህናት ጋር መግባባት ተሳናቸው። ይህንኑ ችግር ጠቅሰው ከማርቲን ፍላድ ጋር ሐሳባቸውን በደብዳቤ መለዋወጥ ጀመሩ፤ ማርቲን ፍላድም ጉዳዩን ለመፍታት ስዋኪን ሱዳን ይገናኙ ዘንድ ቀጠሮ ያዙ። ኅባው ከሱዳን እንደ ተመለሱ ወደ ወሊጋ ዘልቆ የመሄድ ሐሳብ በውስጣቸው አንሰራራ፤ እናም ጀርባቸውን ለአዘዞ ፊታቸውን ደግሞ ለወሊጋ ሰጡ።

አባይን ተሻግሮ ባለው ደቡባዊ ግዛት ከጎጃም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፈቃድ ሳያገኙ መላወስ አይሞከርም። ታዲያ ለኅባው ዐይነቱ አፍቃሬ ትምህርት ቀና አመለካከት የነበራቸው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወጣቱ ኅባው አባይን ተሻግረው እንዲሄዱ ፈቀዱላቸው። እናም ወጣቱ ኅባው በጉድሩ ኦሮሞዎች መካከል ትምህርት ቤት ከፍተው ማስተማር ጀመሩ። በወቅቱ በሸዋና በጎጃም ነገሥታት መካከል በተካሄደው ጦርነት ከአባይ በስተ ደቡብ የነበሩትን ግዛቶች ዐፄ ምኒልክ ሲጠቀልሏቸው ኅባው በጉድሩ በከፈቱት ትምህርት ቤት መቈየትን ስለመረጡ ራስ ጎበና ሥራውን እንዲቀጥሉ ፈቀዱላቸው።

በማስተማር ሥራ ላይ እንደ ቆዩ ከዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን ጀምሮ የነበረውንና ወደ ሸዋ የመጣውን ጆን ሜየርን ለመጠየቅ ወደ እንጦጦ አቀኑ። በዚያም የነበሩት ሜየርና ቢንደር ከዐፄ ምኒልክ ጋር አስተዋወቁአቸው። ይሁን እንጂ በ1879 እነ ሜየር ከአገር እንዲወጡ ሲገደዱ ገብሩም ከሜየር ጋር ዐብረው ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዙ። ከዚያም ወደ ሶሪያ ወርደው በጀርመን ሚስዮን ትምህርት ቤት ውስጥ ለጥቂት ጊዜ አስተማሩ። ብዙም ሳይቈዩ ሚስዮኑ ዳር ኤ ሰላም (ዳሬሰላም) ወደ ከፈተው አዲስ ጣቢያ አዛወራቸው። በወቅቱም የተጀመረውን ጣቢያ በማቋቋምና በማጠናከር ሥራ ላይ በብርቱ ደከመዋል። በዚያም የነበራቸውን ሥራ አጠናቀው ወደ ኢየሩሳሌም በማቅናት ላይ ሳሉ በእንግሊዞች እጅ ወደ ነበረችው ወደ ኤደን በርካታ ኢትዮጵያውያን





በባርነት ተፈንግለው[3] መምጣታቸውን ሰሙ። የእንግሊዝ የባሕር ተቈጣጣሪዎች ከዐረብ የባሪያ ነጋዴዎች ያስጣሏቸውና ለሚስዮኑ ጣቢያ ያከፋፈሏቸው ወደ ሰማኒያ የሚጠጉ ወንድና ሴት ነበሩ፤ ከእነርሱም መካከል አብዛኛዎቹ የኦሮሞ ተወላጆች ስለ ነበሩ፣ ኅባው በሚያቀላጥፉት የኦሮምኛ ቋንቋ ሐሳባቸውን በመግለጽ ሊግባቡ ቻሉ። ባዩት ሁኔታም ልባቸው ተነካ፤ እናም ወደ ኢየሩሳሌም የሚያደርጉትን ጉዞ ሰርዘው ሰዎችን በማስተማርና ረጂዎቻቸውን በማገዝ ተግባር ላይ ተሰማሩ። ኮሎኔል ዳዊት እንደሚሉት፣ ከባርነት ሰንሰለት ነጻ ከወጡት ወጣቶች መካከል ጥቂቶቹ፣ በምሥራቅ አፍሪካ ነዋሪ የነበሩት አቶ ነገሮ፣ አቶ ቶሎሳና ወ/ሮ ሰንበቶ ወጪአቸውን ስለ ሸፈኑላቸው፣ ወደ ደቡብ አፍሪካ በመሄድ በዕርሻና በማእድን ሥራ ላይ ተሰማሩ። በኤደን ቈይታቸው ምክንያት ኢየሩሳሌም የነበሩት ወዳጆቻቸው በብርቱ ተቀየሙ። የምሥራቅ አፍሪካውን ተልእኮ ዘንግተው የትም ይዞራሉ በሚል ሰበብም ክስ ቀረበባቸው። በዚህ ጊዜ ነበር ጆን ሜየር ሳይጽፈው አይቀርም የተባለ ደብዳቤ ለኅባው የደረሳቸው።

"ይድረስ ለወንድሜ ኅባው የእግዚአብሔር ሰላም ከአንተ ጋር ይሁን። አሜን! በሰማይ ያሉት መላእክት አሜን ይበሉ። ከተለያየን ቀን ጀምሮ እኔም ለጤናዬ ደኅና ነኝ። ታጅራ ከመጣሁ አንድ ዓመት ዐለፈኝ። ዐፄ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክም አንተን በማስታወስ ያነሡህ ነበር። ንጉሡ የሜየር ሚሲዮን እንደ ካቶሊክ ሚሲዮን አይደለም። የሚሠሩትና የሚያስተምሩት በራሳቸው ቤተ ክርስቲያን ስለ ሆነ በሸዋ እንዲያስተምሩ ፈቅጃለሁ አሉ። አንተ ጉዳዩን ሳታመዛዝን ቸኵለህ የሄድህበት ምክንያት አልገባኝም። በአበሻ አገር ውስጥ ለመሥራት ቶሎ ተስፋ መቍረጥ የለብህም።

---

[3] በባሪያው ሥርዐተ ማኅበር የባሪያ ግዥና ሽያጭ፣ «ባሪያ ፍንገላ» ይባል ነበር።





www.ethiopianorthodox.org

ትዕግሥት ይጠይቃል። የኢትዮጵያ ሁኔታ በጣም እያደገና እየተሻሻለ ስለሚሄድ ተስፋ የሚጣልበት ነው። ሐረር በንጉሥ ምኒልክ ጦር ተመትቶ ብዙ ዕልቂት ደርሶበታል። ባላምባራስ መኰንን የንጉሡ አክስት ልጅ ደጃዝማች ተብለው የሐረርን ጦር ይመራሉ። . . እባክህ አንተም ቶሎ እንድትመጣ! ከመምጣትህ በፊት ግን ለንጉሡ ጻፍላቸው። ላለመምጣት እንዳታመነታ። ሁሉንም ነገርህህ። ለንጉሡም እንዲሁ እነግርልሃለሁ"

ኅባው በ1882 ዓ.ም. የቢንደርን ልጅ ማርታን አግብተው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ። ብዙ ሳይቈዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ሽያጭ ወኪል በመሆን ወደ ሐረር አቀኑ። በመንፈቁ በሐረር የተነሣው የኮሌራ ወረርሽኝ ነፍሰ ጡር ባለቤታቸውን ነጠቃቸው። በነበራቸው የመግባባት ችሎታ የሐረሩን ገዢ ትኵረት ያገኙት ከንቲባ ገብሩ በዕዳ የተያዘውን የኢየሩሳሌም ገዳም ካርታ ያስለቅቁ ዘንድ በራስ መኰንን ትእዛዝ ከደብሩ አለቃ ከመምህር ወልደ ሰማያት ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ተላኩ። በኢየሩሳሌም ቈይታቸው የእንግሊዝ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ውክልና ሰጥቷቸው ስለ ነበር፣ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ ሦስት የተለያየ ጥራዝ ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ በማምጣት ለዐፄ ምኒልክ አበረከቱ። ዐፄውም ዛሬ ለንደን በሚገኘው የማኅበሩ ጽ/ቤት ውስጥ ተቀምጦ ያለውንና ስማቸው የተቀረጸባቸው ሁለት የዝሆን ጥርሶች በመላክ ደስታቸውን ገለጡ።

የገብሩን ዕውቀት የተገነዘቡት ራስ መኰንን፣ ሐረርጌን ማስተዳደር እንደ ጀመሩ የከተማው ሹም እንዲሆኑ ጠየቋቸው። ገብሩም የርስት መዛግብትን በዘመናዊ መንገድ በማስቀመጥ ነገሮችን መልክ በማስያዝ ተግተው ይሠሩ ጀመር። በዚህም ሙሉ በሙሉ ባይሆንም የአስተዳደር ጠንቅ የሆነውን ጉቦኝነትን መቀነስ ችለዋል። ሕዝቡም የመሬት ሙግት በተነሣ ቍጥር፣ **"የአለቃ ኅባው መዝገብ ይመስክር"** ይል እንደ ነበር ይወሳል። ይህ የአለቃ ኅባው መዝገብ የሐረርን ርስት ዘጠና ሦስት ዓመት ሲዳኝ ቆይቶ በ1967 ዓ.ም. በታወጀው የገጠር መሬት አዋጅ ተዘጋ።



www.ethiopianorthodox.org

በአድዋ ጦርነት ዋዜማ ራስ መኰንን ከሐረር ከመነሣታቸው ቀደም ብሎ ሁለት ደብዳቤ በማስያዝ ኅባውን ወደ ሸዋ ሰደዱአቸው። እሳቸውን በቀጥታ የሚመለከተው የአንደኛው ደብዳቤ ሐሳብ እንዲህ ይነበባል፣

". . አለቃ ኅባው የሰጠው ያልተቆጠበ አገልግሎት ብዙ ጠቅሞኛል። . .ታማኝ ሎሌዎ ነውና ከፍ ባለ ጉዳይ በታማኝነትና በማስተዋል ሊያገለግልዎ ስለሚችል ወደ ግርማዊነትዎ ልኬዋለሁ።

ወረይሉ ላይ የነበሩት ምኒልክ የኅባውን ፍላጎት "ምን ላድርግልህ" በማለት ጠየቁ። ኅባውም ገብሩ ከሚለው ስም ጋር የጎንደርን ከንቲባነት ሰጥተው ወደ አገሬ ይላኩኝ አሉ። ይህማ ቀላል ነው፤ አሁን ለዘመቻው እየተነሣን ስለ ሆነ ቀንቶን ቀኙ የእኛ ሆኖ ስንመለስ በማለት ዐፄ ምኒልክ ተናገሩ።

በ1888 ዓ.ም. የአድዋ ጦርነት እንዳበቃ ኅባው፣ "ገብሩ" በመሰኘት የጎንደር ቀዳሚ ከንቲባ ለመሆን በቁ። በጊዜው የበጌምድርና የጎጃም ገዢ የነበሩት ራስ መንገሻ አቲከም ሁኔታውን በሥልጣናቸው የመግባትን ያህል ስለ ቈጠሩት፣ በገብሩ ሹመት ደስተኛ አልነበሩም። ይሁንና በሐረሩ ገዢ የመጀመሪያ ድጋፍ ያገኙት ከንቲባ ገብሩ፣ በ1882 (በዐፄ ዮሐንስ ጊዜ) ተማርከው ወደ ሱዳን የተወሰዱ ኢትዮጵያውያንን እንዲያስመልሱ በዐፄ ምኒልክ ውክልና አግኝተው ወደ ሱዳን ወረዱ። በዐረብኛ ቋንቋ ይዘጋጁ የነበሩት የሱዳን ጋዜጦች የገብሩን ሐሳብ ተቀባብለው ዘገቡ፤ በመጨረሻም ከሊፋው በጕዳዩ በማመኑ ምርኮኞች ሁሉ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ፈቀደ። ይሁን እንጂ በሰብአዊ ተልእኮ ሱዳን መጓዛቸውንና የሁለቱን አገራት መቀራረብ ያልወደዱት እንግሊዞች ራስ መንገሻን በማነሣሣት ገብሩን የፖለቲካ ሰለባ አደረጓቸው። በዚህም በዐፄ ምኒልክ ትእዛዝ አንኮበር ግዞት ተላኩ። ያም ሆኖ ራስ መንገሻ አቲከም

ከማረፋቸው አስቀድሞ፣ «ከንቲባ ገብሩ የተወረሰውና የተጋዘው ያለ ኃጢአቱ ነው» በማለት መናገራቸው ይወሳል።

ገብሩ ግዞት ላይ እያሉ፣ በ1915 ዓ.ም. የመጀመሪያውን፣ "የአማርኛ ሰዋሰው" አዘጋጁ። የመጀመሪያው ማተሚያ ቤት እንደ ተቋቋመ የመጽሐፉ ረቂቅ ለኅትመት የበቃ ሲሆን፣ እርሳቸውን ጨምሮ በርካታ የዘመኑ ተማሪዎች የዚህ መጽሐፍ ተጠቃሚዎች እንደ ነበሩ ልጃቸው ኰሎኔል ዳዊት ያወሳሉ። ይህም ሥራ ቀዳሚ እንደ መሆኑ ለትምህርት መስፋፋት የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል ማለት ይቻላል። ጣሊያን አገራችንን በወረረ ጊዜ ከንቲባ ገብሩ ታስረው ወደ ኢጣሊያ በመወሰዳቸውና በዚያን ጊዜም ቤታቸው ሲበዘበዝ መጽሐፉ በመጥፋቱ ምክንያት በድጋሚ ማሳተም አልተቻለም።

ከንግሥት ቪክቶሪያ ዕረፍት በኋላ ዙፋን ላይ በተሰየመው ኤድዋርድ ሰባተኛ በዓለ ንግሥ ላይ ለመገኘት የአውሮፓን ቋንቋ የሚያውቅ ሰው ተፈልጎ ኖሮ፣ አንድ የግቢ ሰው፣ "ተቀይሞ ይሆናል እንጂ ገብሩ ለዚህ ሥራ ጠቃሚ ነበር" የሚል አሳብ አቀረበ። ንጉሡም፣ "በአገሩ ጉዳይ አይለወጥምና በቶሎ ከአንኮበር እንዲመጣ።" በማለት አዘዙ። ገብሩ ምሕረት ከተደረገላቸው በኋላ፣ በራስ መኰንን መሪነት ወደ ለንደን ከሚጓዘው ልኡክ ጋር ተቀላቀሉ።

ከንቲባ ገብሩ ከለንደን መልስ በተለያዩ ምክንያቶች ታስረዋል፤ መከራም ተቀብለዋል። ይህ ሁሉ ይሁን እንጂ አንድም ጊዜ ለአገራቸው በጎ ከማድረግና ወዳጆቻቸውን ከመርዳት ተቈጥበው አያውቁም። ቫዝማን የተሰኘው የጀርመን ሚስዮናዊ፣ ካህናትና ቀሳውስቱ ንግሥት



ዘውዲቱን በመጫን፣ ይልቁንም መሬት በግዢ በመያዝ አንዳች የወንጌል ሥራ መሥራት እስከማይቻል ድረስ እያከላከሉ በቈዩበት የውጥረት ጊዜ ጭንቀታችንን የሚያረግብ ሁኔታ



www.ethiopianorthodox.org

ድንገት ተፈጠረ በማለት የጻፈውን ሐተታ ፈቃዱ ጉርሜሳ ሲዘግብ፣ "በ1928 ዓ.ም. ከፋሲካ በኋላ እሑድ ቀን በገጠር መሬት የነበረውና የጀርመንኛ ቋንቋ የሚናገር አንድ ኢትዮጵያዊ ከእኛ ጋር ሊያመልክ ወደ እኛ መጣ። እርሱም በገጠር ካለው መሬቱ ሊሰጠን ቃል ገብቶ፣ ይዞታው የት እንደ ሆነ በካርታ ላይ አመለከተን። በካርታው ላይ ያመለከተን ይዞታ በቀጥታ እኛ ልንሄድ ካሰብንበት ከቦቶር አጠገብ የሚገኝ አይራ የሚባል ነበር. . . ኤርንስ ባውሮክሌ የተባለው ሚስዮናዊ ደግሞ ስለ ለጋሹ ሰው ሲጽፍ፣ "በአዲስ አበባ ከንቲባ ገብሩ የሚባል ለሚሲዮናውያኑ ወዳጅ የሆነ ሰው ነበር። ገብሩ ሚሲዮናውያኑ ሥራ እንዲጀምሩበት መሬት ሰጠ። መሬቱ አይራ በሚባል ቦታ በግምቢ አውራጃ ይገኝ ነበር። ከንቲባ ገብሩ ከሚሲዮናውያኑ ጋር ከመገናኘቱ በፊት በአንድ ወቅት በመንግሥት ሥራ ታዝዞ ወደ ደምቢዶሎ ሄደ። እግረ መንገዱን በአይራና በግምቢ አድርጎ እየተመለሰ እያለ አይራ ሲደርስ ሁለት ጋሻ መሬት እንደሚሸጥ ወሬ ሰማ። ወዲያው መሬቱን ገዛው" በማለት ማንነቱን ይገልጣል።

ምንም እንኳ በገዛ ወገኖቻቸው የተለያየ ግዞት፣ እስራትና መገፋት ተፈራርቀው የደረሱባቸው ቢሆንም፣ አገርን በተመለከተ ግን በተፈለጉበት ጊዜ ሁሉ የሸሹበትና ቅር፡ታ ዐድሮባቸው ሕዝባቸውን ከማገልገል ተስፋ ቈርጠው የታዩበት ወቅት አልነበረም። ከተለያዩ የኢትዮጵያ ልዑካን ጋር በመሆን የመንግሥታቸውን ጉዳይ በሌሎች ነገሥታት ፊት ይዘው ቀርበዋል።

በ1923 ዓ.ም. የመጀመሪያው ፓርላማ ሲቋቋም የሕግ መወሰኛ ምክትል ፕሬዛዳንት ሆኑ። የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አሜሪካን ሲሄድ ዐብረው የተጓዙት ከንቲባ ገብሩ፣ የአገራቸውን ሁኔታ አስመልክተው በተለይ ለኒውዮርክ ታይምስ የሰጡት ማብራሪያ የበርካታ ጥቀ-ር አሜሪካውያንን ቀልብ ከመሳቡም በላይ ስለ አገሪቱ የነበራቸውን ቍንጽል ዕውቀት ይበልጥ



እንዳሳደገው ከዚያ ወዲህ የታዩ ተግባራዊ ውጤቶች አረጋግጠዋል።

ወደ አሜሪካ ባቀኑበት ወቅትም፣ በዚያ የሚገኙ ጥቍር ምሁር አሜሪካውያን ወደ ኢትዮጵያ ምድር ፊታቸውን እንዲመልሱ ጥሪ አድርገዋል። በወቅቱ ካነጋገሯቸው ምሁራን መካከል አርኖልድ ጆዛያ ፎርድ ይገኙበታል፦

አገራችሁ መግባትም አትፈልጉምን? አፍሪካ ነው አገራችሁ። ያላችሁን ዕውቀትና ገንዘብ ይዛችሁ ብትገቡ ራሳችሁንም አገራችሁንም ትጠቅማላችሁ። የኢትዮጵያ አየር ለኑሮ የሚስማማ ነው። ሀብቷ ልክ የለውም። በሀብቷ የሚበለጽገው ግን የውጪ አገር ሰው ነው። ለምሳሌ ጥሬ ሀብት በርካሽ ለውጭ እየሸጥን ተሠርቶ በሚመለስበት ጊዜ መቶ በመቶ በሆነ ትርፍ ስለሚሸጥልን ይህንን እንድትመረምሩና እንድትጠቀሙ፣ እንድትጠቅሙንም እንሻለን ይሏቸው ነበር።

ኢየይዘውም፣ "ኢትዮጵያ በመልማት ላይ ስለ ሆነች የአሜሪካ አገር ምቾት ስለማይገኝባት ለጥቂት ጊዜ ችግሩን መቋቋም አለባችሁ። " በማለት እውነት የሆነውን ጉዳይ ከማስረዳት አልቦዘኑም።

ንግሥት ዘውዲቱ ከንቲባ ገብሩ ለአገራቸው ለሰጡት አገልግሎት ወሮታ በጅባትና ሜጫ አውራጃ ኖኖ በሚባል ሥፍራ ኀምሳ ጋሻ መሬት፣ በተጨማሪ ወርቅም እንዲያወጡበት በወለጋ፣ ደግሞም በበጌምድርና በማጂ ምሪት ሰጥተዋቸው ስለ ነበር፣ ለጥቍር አሜሪካውያን መሥፈሪያና ጥበባቸውንም መግለጫ ለማድረግ አስበው እንደ ነበር ልጃቸው ኮሎኔል ዳዊት ይነግሩናል።



ጣሊያን ኢትዮጵያን ሲወር ከንቲባ ገብሩ ወደ ጎሬ አቀኑ። በዚያም ሆነ ባሕር ማዶ በግዞት ተልከው እያሉ መከራ ክፉኛ ጐንትሏቸዋል። ቤተሰባቸው



ተንገላቷል። ልጆቻቸውም በፋሺስቶች በግፍ ተገድለዋል። ይሁንና በጦርነቱ ማብቂያ ጣሊያኖችን ከአገር ለማስወጣት ሥልጣን ለተሰጣቸው አለቆቹ ረዳት ሆኖ ይሠራ የነበረውን ልጃቸውን እንዲህ ሲሉ ነበር የመከሩት፣ "ዐደራህን ልጄ ጣሊያኖች በኢትዮጵያውያን ላይ በደል ቢያደርሱም፣ እኛ ክርስቲያንነትንና ትልቅነታችንን ማሳየት እንጂ ላደረሱብን በደል መበቀል ብንሞክር ከእነርሱ ያልተሻልን ሁነን እንገኛለን።"

ከንቲባ ገብሩ በነጻነት ማግሥት ወደ ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ተመልሰው የመወሰኛው ምክር ቤት ፕሬዘዳንት በመሆን ማገልገል ጀመሩ። በዚያም ለአገር የሚጠቅሙ በርካታ ጉዳዮችን አሳውቀዋል፤ ከውነዋልም። እኒህ ምሁር ባገለገሉበት ዘመን ሁሉ ከማንም ባልተናነሰ ሁኔታ ለአገር ጠቃሚ የሆኑ ሐሳቦችንና ተግባራትን በመፈጸም የኖሩ ቢሆንም፣ ያለፉት የተከፈተ ልብ ሳያገኙ ነበረ ። ይህን መሰሉን ሁኔታ በተለይም፣ የጎንደሩን ተልእኮ አስመልክቶ ታሪክ ጸሓፊው ጉስታብ፣ "የወንጌል እምነቱ፣ ከአገር ውጪ ተሻግሮ የነሮጮችን ትምህርት መቅሰሙና ከዝቅተኛ ቤተ ሰብ መወለዱ ተዳምረው የተቀናቃኞቹን ቍጣ ቀስቅሷል" በማለት ሲነግረን፣ ፈቃዱ በበኩሉ፣ "ከንቲባ ገብሩ ጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። በትውልዳቸውም ፈላሻ አልነበሩም። በአበሾቹም ዘንድ እምብዛም የተወደዱ አልነበሩም." ይለናል። ኰሎኔል ዳዊት ይህንኑ ጉዳይ አንሥተው ሲያወሱ፣ "የዘመኑ መኳንንትና መሳፍንት ከንቲባ ገብሩን በሞያቸው እየወደዷቸው፣ ዕድገትንና የሥራ ደረጃን በተመለከተ ግን ትውልዳቸው እንደማይፈቅድላቸው በመቍጠር አቌርቍዘዋቸዋል። ከንቲባ ገብሩ ዕውቀት እንጂ ሀብት ያላቸው ሰው ስላልነበሩ የሚቀጥሉት ዓመታት የከባድ ችግር ዓመታት ሆኑባቸው" በማለት ዘግበዋል።

ከንቲባ ገብሩ ውጣ ውረድና ድካም የበዛበትን የዚህ ዓለም ጉዞ አገባደው በ1942 ዓ.ም. ዐረፉ። የታሪክ ምሁር የሆኑት ፕሮፌሰር





www.ethiopianorthodox.org

ባሕሩ ዘውዴ፣ የውጪ አገር ትምህርት ቀስመው ከተመለሱ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ምሁራን ተርታ የሚፈርጇቸው ገብሩን፣ ልጃቸው ኰሎኔል ዳዊት፣ በዘመኑ ከነበረው ማኅበራዊ ሥቃይና ሊታሰብ ከማይችለው ከዚያ ሩቅ የገጠር መንደር በመርፌ ቀዳዳ የመሹለክ ያህል አፈትልከው ከምሁራን ተርታ ለመመደብ መብቃታቸው እንደ ታሪክ አጋጣሚ፣ እንደ ጸጋ፣ ዐልፎም እንደ ዕድል ይቈጠራል በማለት ያወሳሉ።

የተለያዩ አጥኚዎች ከተለያየ የሕይወት ፈርጅ በመነሣት የጎሩያንንም ሆነ የእኩያንን ሕይወታዊ ፈለግ መዘከራቸው ያለ ሲሆን የከንቲባውን ምድራዊ ሕላዌ ከተንጣለለው እና ባህር ከሆነው አኗኗራቸው ላይ በማንኪያ ስንጨልፍለት ይህን መስሎ ብቅ ብሏል።

## መወድስ

ከታች ተነሣ ከድኻ ሰፈር
ከንቲባ ገብሩ ሊጠቅም ላገር

የሚጠሉትን እየጠቀመ
ላገሩ ፍቅር እርሱ ታመመ

ኀባው ከፍ ያለ ባለ መዝገቡ
ታሪክህ ደማቅ ጒልሕ ኮከቡ

## ትምህርተ ውልብታ

እየጠሏቸው እንደሚጠቀሙባቸው ልባቸው ቢያውቀውም ለአገር ጒዳይ እስከ ሆነ ለሹም እዝ እሺ ባይ መሆናቸው አገር ወዳድነታቸውን ያሳያል።





ጭልም ባለባቸው ጊዜ የእምነት ርምጃ መውሰዳቸው ለሕይወታቸው መለወጥ ምክንያት መሆኑንና መንፈሰ ጠንካራነታቸውን ያሳያል።

ውጤት ተኮር በሆነ መልኩ ብቻ ሳይሆን በተሰማሩበት መስክ የተቻላቸውንና የበኩላቸውን ድርሻ ለማበርከት መጣራቸው የዓላማ ጽናታቸውን ያመላክታል።

የደረሰባቸው በደልና ሥቃይ በቀላሉ የሚታለፍ ባይሆንም ራሳቸውን ከቂምና ከጥላቻ ነፃ በማድረግ የሕይወት ጒዟቸውን መቀጠላቸውና ልጆቻቸውም በእርሳቸውን ዱካ እንዲከተሉ ማስተማራቸው ትልቅ የምሳሌነት ሕይወት ነው።

## የውልብታ ምንጭ


ዳዊት ገብሩ (ኮሎኔል)፣ *ከንቲባ ገብሩ ደስታ የኢትዮጵያ ቅርስ* ፣ አዲስ አበባ፣1985

ፊቃዱ ጉርሜሳ ኩሳ፣ *የወንጌል እምነት እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ*፣ አዲስ አበባ፣ጃንዋሪ 1999 ዓ.ም

Aren, Gustav *Envoys of the Gospel in Ethiopia*. Stockholm, 1999 Evangelical pioneers in Ethiopia. Origins of the Evangelical church Mekane Yesus. Stockholm & Addis Ababa, 1978

Baheru Zewde. Pioneers of change in Ethiopia, The ReformistA History of modern Ethiopia 1855-1974.London, Athens & Addis Ababa,






www.ethiopianorthodox.org

## የአንባቢው የግል ማስታወሻ





# ፫



## አለቃ ታዬ ወልደ ማሪያም
## 1853 –1916
## የጨለማው ብርታት የጎፈነነው ምሁር

:

*ለአገሬ መንግሥት ቅንኣት እንደ ሳት በላኝ . . ምንኮ አደርጋለሁ? ዐዝኜ ወደ መቃብር እወርዳለሁ*

www.ethiopianorthodox.org

እስከ ዛሬ ድረስ ወደ ሩቅ አገር ተሰደው ወይም ወደ አበሻችን ከመጡት ፈረንጆች ጥቂት ጥበብ ተምረው ያገራቸውን መንግሥት ሊጠቅሙ የሚፈልጉ ወንድሞቻችንን መናፍቃን፣ የሊላም መንግሥት ሰላዮች እየተባሉ ሲራቡ፣ ሲከሰሱም እናይ የለምን? የእነዚያን መከረኞች ስም ስንት ብለን እንቍጠረው? የሚከተሉት የሁለት ሰዎች ስም እንዲወሱ የግድ ነው። እነርሱም ከንቲባ ገብሩና አለቃ ታዬ ናቸው። ሦስት ዓመት ሙሉ አዲስ አበባ ላይ ስቀመጥ እንደነዚህ ሁለት ሰዎች አድርጎ መንግሥቱን የሚወድ ሰው አላየሁም። ይህ ደግነታቸው ግን እስከ ዛሬ ድረስ አልታወቀላቸውም ይመስለኛል። እጅግ ያሳዝናል። የእነሱን ዕድል ያየ ሰው የኢትዮጵያ መንግሥት ለወዳጅ አይጠቅምም ብሎ ተስፋ ይቈርጣል።

ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ

አዛውንቱ ገብረ ማርያም ኪዳነ ማርያም ዳዊት ከመድገም ያለፈ ዕውቀት አልነበራቸውም፤ ከጥቍር ዐፈር ጋር ታግለው የመሬትን እምብርት በመገልበጡ ሙያ ግን ተክነውበታል። ያብራካቸው ክፋይ ታዬ ደግሞ፣ ሞፈር ከቀንበር ማቀናጀት የማለዳ ዕጣ ክፍላቸው አልነበረም፤ መቃ ብርዕ ከብራና ወይም ከወረቀት ጋር አዋድደው ሆህያትን የሚያበራዩ ሥሉጥ የቀለም ቀንድ እንጂ።

እምር ታህል ልጅ እያሉ ወደ ቤተ ክህነት ትምህርት የተላኩት ታዬ ስምንት ዓመት ሲሞላቸው ንባብና ጽሕፈትን አቀላጥፈው እንደ ቻሉ ይነገርላቸዋል። የተወለዱበትን ዘመን አስመልክተው በዕድሜ ከገፉ በኋላ ከኪሳቸው በማትለይ አንድ የግል ማስታወሻቸው ላይ የተገኘው ጽሑፍ እንዲህ ይነበባል:-

*የአለቃ ታዬ ልደት 1853 ዓ.ም. በዘመነ ወንጌላዊ ሉቃስ 20 ወአሐዱ ለኅዳር ነው። ይህም ዐፄ ቴዎድሮስ በነገሡ በ7ኛው ዓመት ነው። ካፄ ቴዎድሮስ መንግሥት 8 ዓመት አመጣለሁ። በአውሮጳ አቈጣጠር ግን 1861 በኖቬምበር ወር 30ኛው ቀን ተወለድኩ።*



ኤሪክሰን የተባለው የውጭ አገር ዜጋ ይህን የግል ማስታወሻ ካነበበ በኋላ በአውሮፓውያን የዘመን አቀማመሩ ላይ መጠነኛ ማስተካከያ አድርጎአል፤ «ታዬ



www.ethiopianorthodox.org

'ተወለድሁ' የሚሉን በኢትዮጵያውያን ዘመን አቈጣጠር ኅዳር 21፣ 1853 ከሆነ፣ የዘመኑ ስሌት ወደ አውሮፓውያን ቀመር ሲመነዘር ከቶም ኖቬምበር 30፣ 1861 ሊሆን አይችልም» ሲል ኤሪክሰን አሳቡን ያቀርባል። ቢሆንም የታዬን የግል ማስታወሻ የዕድሜአቸው መቁጠሪያ አድርገን እንዝለቅ።

እንደ ታሪክ ጸሐፊው ጉስታቭ ዘገባ ከጣና ሐይቅ በስተ ምሥራቅ በምትገኘውና ደፋግ በተሰኘችው የገበያ ማእከል የተወለዱት ታዬ ዕድሜያቸው ዐሥር ዓመት ሲሞላ የዳኹባት መንደር በወረርሽኝ መቅሠፍት ተመታች። አስቀድሞ መንደሪቱን ለቀው ከሄዱት ወላጅ አባታቸው በቀር አምጠው የወለዷቸውን እናታቸውን ጨምሮ የቀሩት ዘመዶቻቸው በበሽታው ረገፉ። በዚህ ምክንያት በእኚህ ሰው ልብ ውስጥ ሰቀቀን ነገሠ። ብቸኝነታቸው አባታቸውን ፍለጋ አገር ጥለው እንዲሄዱ ገፋፋቸው።

የአለቃ ታዬን የሕይወት ታሪክ የጻፈው ኃይሉ ከበደ ባልታተመ የጽሑፍ ሥራው፣ አለቃ ታዬ ለስደት ከወጡበት ማግስት ጀምሮ ያለውን ሁኔታ እንዲህ ሲል ይተርካል፤ ". . . አባታቸው ወደሚገኙበት ወደ ሸዋ ጠቅላይ ግዛት ለመሄድ ሞክረው ሳይሳካላቸው ስለ ቀረ የእናታቸው ወንድም የሚሆኑት አጎታቸው ትግራይ ይኖሩ ስለ ነበር ጕዞአቸውን ወደዚያው አመሩ። ትግራይ እንደ ደረሱ አጎታቸውን ስላጧቸው ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ዐቅደው ምጽዋ ደረሱ፤ እግረ መንገዳቸውን በስዊድን ሚስዮን ትምህርት ቤት እንዳረፉ በዚያው ትምህርት ቤት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ጀመሩ።

ጉስታቭ አሬን የተሰኘው ጸሐፊ፣ "Evangelical Pioneers in Ethiopia" በተሰኘ ሥራው ይህንኑ የታሪክ ሂደት እንዲህ ሲል አስፍሮታል፤ " . . የ19 ዓመቱ ታዬ ምጽዋ ከወረዱ በኋላ አጎታቸው ባሕር ቀዝፈው ወደ ሕንድ መዝለቃቸውን ሰሙ፤ በዚህም ምክንያት ሐሳባቸውን ቀይረው እምኩሉ ወደሚገኘው የወንዶች ትምህርት ቤት ለመግባት ወሰኑ። ከተቀሩት ልጆች አንጻር ሲታይ በዕድሜ ጠና ማለታቸውን የገመተው ሉንደል የሚባል የትምህርት ቤቱ ኀላፊ በመጀመሪያ ታዬን ተቀብሎ ለማስተናገድ ቢያንገራግርም፣ ጥቂት ወራት ካለፉ በኋላ ግን እንዲማሩ ፈቀደላቸው።



በትምህርት ቤት በቈዩባቸው ወቅቶች ብሩህ አእምሮ እንደ ነበራቸው አስመስክረዋል። በወቅቱ የነበሩት ዊንክቨስት እና ኤሚሊ ሉንደል የተባለት መምህራን እንዳጤኑት፣ «ታዬ በባህላዊ ትውፊቶች በመመሰጣቸው፣ ከምዕራባውያን ትምህርት ይልቅ ለምሥራቁ ቅድሚያ ሲሰጡ ታይተዋል። ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ልዩ ዝንባሌ አላቸው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ለማጥናት ሰፊ ጊዜ ይሰጣሉ፤ አብዛኛውን ጊዜም እስከ ሌሊቱ አጋማሽ ድረስ ከግእዝ መጻሕፍት እያጣቀሱ ይመረምራሉ» በማለት መስክረውላቸዋል።

ኤሚሊ ሉንዳል፣ ባለቤቷ ከመሞቱ አስቀድሞ ስላዘጋጃቸው የጽሑፍ ሥራዎች ባወሳችበት ማስታወሻዋ ላይ፣ የሉንደል ዐቢይ ሥራ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ መሆኑን ጠቅሳ፣ ሥራው የተከናወነው ታዬ እምኵሉ ትምህርት ላይ በነበሩበት ወቅት ቢሆንም፣ ጽሑፉን በመገልበጥና ቋንቋውን በመግራት በኩል ግን አለቃ መልካም እገዛ እንዳደረጉ ታወሳለች። ኤሚሊ እንደምትለው ሉንዳል ባረፈበት ወቅት በዮሐንስ ወንጌል ላይ የሠራው ሐተታ አብዛኛው እጅ የተጠናቀቀ ቢሆንም፣ መላልሶ በመከለሱና ለኅትመት ብቁ አድርጎ በማዘጋጀቱ ተግባር ውስጥ የእሷ /ኤሚሊ/፣ የታዬና የኦኔሲሞስ ተሳትፎ እንዳለበት አስፍራለች። በተከታዩ ዓመት ማለትም በኖቨምበር 1882 ታዬ ቅኔ ለመቀኘት ፊታቸውን ወደ ቤገምድር መለሱ። ይህን የመልስ ጕዞ አስመልክቶ ኃይሉ እንዲህ ይላል፤ ". . . እምኵሉ በተባለው ሚሲዮን ትምህርት ቤት ውስጥ ለብዙ ዓመት የወንጌልን ቃል ሲመራመሩ ቈይተው እንደገና ወደ ትውልድ ሀገራቸው ተመለሱና የግእዝ ቅኔ ትምህርት ቤት ገቡ። በዚያም የግእዝን ቋንቋ ጠንቅቀው እንዳወቁ በ1877 ወደ ምጽዋ ተመልሰው በመምህርነት ሙያ አገለገሉ። በዚህ ዘመን የድርሰት ሥራ እንደ ጀመሩ ይታመናል፤ መጽሐፈ ሰዋሰው የተባለውን መጽሐፍም በዚሁ ጊዜ ጻፉት። "



አለቃ ታዬ የበርካታ መጻሕፍት ባለቤት ቢሆኑም፣ አብዛኛዎቹ ሥራዎቻቸው ወደ ሕዝብ እጅ አልደረሱም። ከሥራዎቻቸው መካከል፣ እስከ አሁን በስዊድንኛ ቋንቋ ብቻ የሚገኝና በወጣትነት ዘመናቸው እንደ ጻፉት የሚገመተው "En Teologisk strid inför Ras Mengescha" *(A Theological Debate Before Ras Mengesha*



ነገረ መለኮታዊ ክርክር በራስ መንገሻ ችሎት) እንዲሁም 450 ገጾችን አካቶ የያዘውንና ምናልባትም በዕድሜ ዘመናቸው ማብቂያ ላይ ሳይደርሱት እንዳልቀረ የሚገመተውን በእጅ ጽሑፋቸው የተዘጋጀ (አብዛኛው ማጣቀሻ በግእዝ ቋንቋ የሆነው) የአማርኛ መዝገበ ቃላት ወይም የጽንሰ ሐሳብ መዝገብ ናቸው።

ጉስታቭ አሬን ይህን ሁኔታ ሲያብራራ፣ ታዬ ወደ መንደራቸው የተመለሱት ሊጣቸውን ሳይሆን ያገኙትን መንፈሳዊ ዕውቀት ጭምር ይዘው ነበር። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳታቸውን ለሌሎች ሊያጋሩ ቢፈልጉም እንኳ የቀዬውን ቀልብ ሊያገኙ አልቻሉም፤ በመሆኑም የቅኔ ትምህርታቸውን በሙሉ ልብ ቀጠሉ። ምርምራቸውንም ዕውቅና ባላቸው በተለያዩ አድባራትና ገዳማት ካጠናቀቁ በኋላ፣ «አለቃ» የተሰኘውን ከፍተኛ ማዕረግ አገኙ። ከዚያም በ1883 ዓ.ም. ወደ እምኵሉ ተመልሰው በመምህርነት፣ በአስተርጓሚነትና በወንጌል ሰባኪነት አገልግለዋል።

በ1890 እንደ ገና ወደ ትውልድ መንደራቸው ተመለሱ። በዚያም ትዳር መሥርተው የወንጌል ስብከታቸውን ቀጠሉ። በሙያቸው ተወዳጅነትን በማትረፋቸው በዘመኑ ቤገምድርን በከፊል ይገዙ በነበሩት ራስ መንገሻ አቲክም ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትን አገኙ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም የታዬን ሊቅነት በመገንዘብ ራስ መንገሻ አሽከራቸውን ባልደረባ ሰጥተው በ1891 ዓ.ም. ወደ አፄ ምኒልክ ሰደዱአቸው።

ወቅቱ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ያመፁበትና የሸፈቱበት ጊዜ ስለ ነበር፣ በራስ መኰንን የሚመራ ጦር ወደ ትግራይ ዘመተ። ንጉሡ አፄ ምኒልክ የሰራዊቱን ሁኔታ በቅርበት ለመከታተል ወሎ ደነባ ላይ ዐርፈው ሳለ አለቃ ታዬ ከንጉሡ ፊት ቀርበው ተዋወቁ። እምኵሉ ሳሉ አሳትመውት የነበረውን መጽሐፈ ሰዋሰው የተሰኘውን መጽሐፋቸውን ለንጉሡ አበረከቱ። ንጉሡም ሥራውን አይተው በመደሰት ሊቁን ካበረታቷቸው በኋላ ወደ ትውልድ ቦታቸው ሄደው በዚያው እንዲቈዩ አዘዟቸው።



ከፊል ትምህርታቸውን ከውጪ አገር ዜጎች በመቅሰማቸው ሰበብ አንዳንድ የቤተ



www.ethiopianorthodox.org

ክህነት ሰዎች በአለቃ ታዬ ላይ ተቃውሞ ያነሡባቸውና ያስነሡባቸው ስለ ነበር፡ ይህንኑ ጉዳይ ለአፄ ምኒልክ አቅርበው የሚከተለውን ደብዳቤ ተቀበሉ።

> *ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ አለቃ ታዬ ገብረ ማርያም የሚባል ሰው ምጽዋ የነበረ ሃይማኖቱን እኛ መርምረነዋልና ማንም አንዳች አይበለው በሃይማኖት ነገር። በኅዳር 6 ቀን 1891 ዓ.ም. በወረኢሉ ከተማ ተጻፈ።*

ከዚያ በኋላ ወደ በጌምድር ተመልሰው ሥራቸውን ቀጠሉ። አፄ ምኒልክ ከወሎ ተነሥተው አዲስ አበባ እንደ ደረሱ ታዬም ወደዚያው ሄደው ከንጉሡ ጋር በመገናኘት ጸሓፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴን በባልደረባነት ተቀበሉ። በጊዜው አንዳንድ ሰዎች፣ የታዬ ሃይማኖት የፈረንጅ ነው፣ ንጉሡ ይህን ሳያውቁ ነው ማኅተም የሰጡት በማለት ስላስወሩ፣ አቡነ ማቴዎስና ጸሓፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ተቀናቃኝ ሆነው ተነሡባቸው። ይህም ሁኔታ በጸሓፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በኩል ወደ አፄ ምኒልክ የመቅረብ ዕድላቸውን አከሰመው።

እንደሚባለው አቡነ ማቴዎስ ጉባኤ ከተው አለቃ ታዬን ካስጠሩ በኋላ፣ «አንተ አህያ ሃይማኖትህ ምንድን ነው?» በማለት ለጠየቋቸው ጥያቄ፣ አለቃ፣ «እኛን አህያ የሚያሰኘን እናንተን በመሾማችን ነው» ብለው እንደ መለሱላቸው ይነገራል። ነገሩ እየከረረ በመምጣቱና በአለቃ ላይ የተፈጸመው በደል ምኒልክ ዘንድ በመድረሱ፣ ንጉሡ ጸሓፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴን ገሥጸቸው፤ በማይገባ ሁኔታ አለቃን በማንገላታታቸው በአቡኑም ላይ የተሰማቸውን ቅሬታ ገልጸዋል።




በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ታዬ ወንጌልን ከማስተማር ጐን ለጐን የጽሑፍ ሥራቸውን ቀጠሉ። ይህንንም ተግባር በትጋት በማከናወን ላይ ሳሉ፣ ከንጉሡ ዘንድ እንዲህ የሚል የማዘገር ደብዳቤ ደረሳቸው፦



> *ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ ይድረስ ከአለቃ ታዬ እንዴት ሰንብተሃል። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ። ከጀርመን መንግሥት ተልከው የመጡ ሰዎች በምጽዋ በኩል ወደ ሀገራቸው ለመሄድ በጐጃም በኩል ወጥተዋል። ነገር ግን ከኢትዮጵያ የሄዱ በአገራችን ብዙ የጥንት መጻሕፍት አሉ። ያንን የሚያውቅ ብልኅ ሰው ይሂድና እንዲያይ ይሁን ብለውኛል። አንተ የዚያን አገር ባህል ለምደኸዋልና እናንተ ዘንድ በደረሱ ጊዜ አንተም ከእነሱ ጋር ዐብረህ እንድትሄድ ይሁን። መጋቢት 9 ቀን 1897 ዓ.ም. ዐዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ።*

ይህን ጥሪ አስመልክቶ ክሪስ ፕሩተ፣ "*Empress Taytu and Menilek II*" በሚል ሥራው፣ ከጀርመኖች ዘንድ የመጣውንና በበርሊን የኦሬንታል (ምሥራቃዊ) ጥናት ተቋም ውስጥ ባለሙያ የማስማራቱን ጥያቄ በበቂ ሁኔታ ሊያሟላ የሚችል ከታዬ የላቀ ስመ ጥር የግእዝ ምሁር በምኒልክ አእምሮ ውስጥ አልነበረም፤ ያም በመሆኑ ለዚህ ኀላፊነት ዕጭ ተውታል በማለት ጽፎአል።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ የሕይወቴ ታሪክ በተሰኘ መጽሐፋቸው ይህንኑ ሁኔታ እንደሚከተለው ገልጸውታል፤ የጀርመን መንግሥት የግእዝ ቋንቋ የሚያስተምር አንድ ሊቅ ይሰጠኝ ብሎ አፄ ምኒልክን በለመነ ጊዜ፣ አለቃ ታዬን መርጠው ሰደዱአቸው። በጀርመን መንግሥት ሦስት ዓመት ሙሉ የግእዝ ቋንቋ አስተምረው ኒሻን ተሸልመው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ፣ አፄ ምኒልክም ኒሻን ሸልመው የአባታቸውን አገር ሰጥተው ወደ በጌምድር ሰደዱአቸው።

ታዬ በአገራቸው ብቻ ተወስነው አልቀሩም። ወደ አውሮፓም አቅንተዋል። በዚያም በርካታ ከተሞችን የጎበኙ ሲሆን ለዚህም ዋቢነት ማስታወሻዎቻቸው ሊጠቀሱ ይችላሉ፦






www.ethiopianorthodox.org

ማክሰኞ ግንቦት 22/1897

*በዚህ ቀን ሌሊቱን ስንሄድ ዐድረን ማለዳ ሲቂሊያ በ6፡00 ሰዓት ደረስን። ስንሄድ ውለን ማታ በ7፡00 ሰዓት ኒያፓል ገብተን ዐደርን። ሲቂሊያ የኢጣሊያን ክፍል ናት። እርስዋም ቃሮዳን የምታህል ታላቅ ደሴት ናት። ከተሞችዋም በባሕር ዳር ለዳር ተሠርተው እጅግ የሚያምሩ ናቸው። ኒያፖልም በባህር ዳር የተሠራ የጥንት የጣሊያን ነገሥታት ከተማ ነው። ዛሬ ግን ራሱ ከተማው ሮም ነው።*

ቅዳሜ ግንቦት 26/1897

*በዚህ ቀን በማርሴል ዋልን፤ ባቡሩ፡ ዕቃ ስታወርድ፣ ዕቃ ስትቀበል ዋለች። እኔና ዮሴፍ ሱማሊ በ8፡00 ሰዓት ከባቡር ወጥተን በሠረገላ ከተማ ለከተማ እኩል ሰዓት ሄድነ። ወርደን በእግራችን ደግሞ እየዞርን ብዙ ነገር አየነ። በዚያም እጅግ ኀፍረት የሌላቸው ደፋሮች ጋለሞቶች አየነ። በ5፡00 ሰዓት ወደ ማታ ከባቡራችን ገብተን ዐደርነ።*

አለቃ በጀርመን ቈይታቸው ከአፄ ምኒልክ ጋር በመጻጻፍ መፈጸም የሚገባቸውን ሁሉ በትጋት ያከናውኑ ነበር፤ በግእዝ የተጻፉትን መጻሕፍት ከመመርመርና ከመሰብሰብ በተጨማሪ አማርኛንና ግእዝን በበርሊን ዩኒቨርስቲ ውስጥ አስተምረዋል።

አለቃ በዚያ አገር ውስጥ በከራረሙበት ዘመንም አንዳንድ ሁኔታዎችን ከየአቅጣጫው ከቃኙና ካስተዋሉ በኋላ ጳጉሜ 3 ቀን 1898 ዓ.ም. ለአፄ ምኒልክ የሚከተለውን ደብዳቤ ጽፈዋል፦




*. . እኔ ያስተማርኳቸው አማርኛና ግእዝ ያነባሉ፣ ይጽፋሉ። ደኅና ሰዎች ናቸው። የጃንሆይ መልእክተኛ ብለው አክብረውና አፍቅረው ይዘውኛል። ከአገር ናፍቆት በቀር የጐደለብኝ ነገር የለም። ለጥበባቸው ፍጻሜ የለውም። በየዕለቱ ዐዲስ ነገር አያለሁ፤ ዐዲስ ነገር እሰማለሁ።*



*ጃንሆይ ከአገርዎ ልጆች ወደ አውሮጳ ሰደው ብልኀት ቢያስተምሩ መልካም በሆነ፣ የያጃንና የሞሪክ መንግሥት ሰው እየሰደዱ አስተማሩ። ይህን አይቼ ለአገሬ መንግሥት ቅንዓት እንደ ሳት በላኝ . . ምንክ አደርጋለሁ? ዐዝኜ ወደ መቃብር እወርዳለሁ። የጃንሆይ ብር እንዲሠለጥን የፈተኛውን ብርና አሞሌ ያጥፉ።*

በማከታተልም ግንቦት 1899 ዓ.ም. የውስጣቸውን ብሶትና የአገራቸውን ኋላ ቀርነት የሚያጣቁምና መንሥኤውን የሚዘረዝር አንድ ደብዳቤ ለአፄ ምኒልክ ሰደዱ። ክሪስ የተሰኘው ታሪክ ጸሓፊ ስለዚሁ ደብዳቤ ሲያወሳ፣ ታዬ በሜይ 1907 ቀጭት የተሞላበት ደብዳቤውን ለአፄ ምኒልክ የጻፈው በዚህ መልክ ነበር፦

*እኛ ሀበሾች . . በመንፈሳዊና በሥጋዊ ጥበብ ወደፊት የማንገፋበት ምክንያት ምን ይሆን ብሎ ለሚጠይቅ . . .ሕዝቡ ሁሉ ባይማርና የወንጌልን ስብከት በብዙው ባይሰማ፣ እውነተኛ ዕውቀትና አፍቅሮ ቢጽ ትሕትና ቢጠፋ ነው ... ። በአገራችን ጥቂት ዕውቀት ያላቸው ሰዎች በመክበር ፈንታ ስለሚሰደቡና ስለሚዋረዱ፣ ስለሚጠቁም የሚያውቁትን ጠቃሚ የጥበብ ሥራ ትተው በቦዘን መኖርን መረጡ።*

በማለት ከተናገረ በኋላ ንጉሡ በጉዳዩ ላይ አጥብቀው እንዲያስቡ፣ ችግሩንም ከፍጻሜው እንዲያደርሱ በመጠየቅ ይደመድማል ሲል ጽፎአል።

ክሪስ ያልጠቀሰው የደብዳቤው ቀሪ ክፍል እንዲህ ይነበባል፦

*የአዳምን ልጆች ዓለሙን ሁሉ የፈጠረ አድልዎ የሌለበት አንድ ልዑል እግዚአብሔር ነው። ላንዱ ወገን ሕዝብ ሙሉ፣ ላንዱ ወገን ጐደሎ ልብ አልፈጠረም።*






www.ethiopianorthodox.org

በፍጥረቱ የአዳምን ልጆች ሁሉ አስተካክሎ እንደ ፈጠረ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። እንዲህ ከሆነ ስለ ምን ያውሮፓና የእስያ ሰዎች ከአፍሪካ ክፍልም ጥቂቶች ብልኀቶኞች ሲሆኑ እኛ ሀበሾች . . . መጽሐፍ ቢማሩ ኮቸሮ ለቃሚ . . .፣ ብርና ወርቅ ቢሠሩ ቀጥቃጭ ቡዳ . . .፣ እንጨት ቢሠራ አናጢ ዕንጨት ቈርቋሪ . . .፣ ቈዳ ቢፍቅ ጥንበ በላ ፋቂ . . . እየተባለ፣ ለየሥራው ሁሉ ስም እየተሰጠ ስለሚሰደብ የጥበብ ሥራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀዘቀዘ ጠፋ። ስለዚህ ጒዳይ ጃንሆይ አስበው እንዲህ ያለው ስድብ ሁሉ ባዋጅ እንዲከለከል . . . ሰዎቹ እንዲከበሩ ቢያደርጉ፣ . . . በሌላ መንግሥት ስምና መልክ በተቀረጸ ገንዘብ ከመገበያየት፣ በጃንሆይ መልክና ስም የተቀረጸበት ገንዘብ እንዲወጣ ቢያደርጉ ነጻ መንግሥትም ራሱን የቻለና የተሟላም ይሆናል . .

ታሪክ ጸሓፊው ክሪስ እንደሚለው፣ የታዬ ደብዳቤ ከተጻፈ ከ4 ወር በኋላ ማለትም በጃንዋሪ 1908 አፄ ምኒልክ የትምህርትን አስፈላጊነትና የሥራን ክቡርነት ያካተተውን ዐዋጅ አሳወጁ።

ከጀርመን መልስ ሦስተኛውን የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ኒሻን ከአፄ ምኒሊክ ዘንድ የተሸለሙት ታዬ ወደ ትውልድ አገራቸው በመዝለቅ ሥራቸውን ቀጠሉ። በዚያም ከተሰጣቸው ጉልት ገሚሱን በኀይል ከነጠቁ በኋላ ቀሪውን ደግሞ ለመጠቅለል እየተንቀሳቀሱ የነበሩት ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ ባለጋራ ሆነው ተነሡባቸው። በጊዜው የበጌምድር ገዢ ለነበሩትም ለንጉሥ ወ/ጊዮርጊስ እንዲህ ብለው ጻፉላቸው፤ አለቃ ታዬ ሃይማኖቱ የንስጥሮስ ነው፤ ይህንንም ሃይማኖት ለሕዝቡ



ያስተምራል። ከዚያ በኋላ ንጉሥ ወ/ጊዮርጊስ ብስጭት በሞላበት መንፈስ የሚከተለውን ደብዳቤ ጽፈው ለአለቃ ታዬ ሰደዱ፦



የተላከ ከራስ ወ/ጊዮርጊስ ይድረስ ከአለቃ ታዬ እንዴት ሰንብተሃል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ። ዝም ብለህ ተቀመጥ ስንልህ እንደዚህ ያለ ትምህርት ከየት ያመጣኸው ነው? በምን ተጣላኸኝ እንዳትል። በ1903 ዓ.ም. ኅዳር 24 ቀን ተጻፈ።

አለቃም ደብዳቤው እንደ ደረሳቸው ሃይማኖታቸው ተዋሕዶ መሆኑንና የተፈጸመባቸውም ግፍ ተገቢ እንዳይደለ ለንጉሥ ወ/ጊዮርጊስ በመግለጽ የተወሰደባቸውን መሬት እንዲያስመልሱላቸው ጠየቁ፤ ንጉሡም ደጃዝማች መሸሻ ወርቄን አስጠርተው የወሰዱባቸውን ጉልት ለአለቃ ታዬ እንዲመልሱላቸው ፈረዱ። ሁኔታው ያልተዋጠላቸው ደጃዝማች መሸሻም፣ታዬ ሃይማኖቱ ፀረ ማርያም ነውና አገር መግዛት አይገባውም በማለት ሌላ ክስ ከፈቱ።

ንጉሥ ወ/ጊዮርጊስም ጒዳዩ ሃይማኖት ነክ በመሆኑ ታኅሣሥ 24/1903 ክሱን ወደ አቡነ ማቴዎስ መሩት። ጥር 28 በዋለው ጉባኤ አለቃ ፈለቀ ከሳሽ ሆነው በመቅረብ፣ "አለቃ ታዬ ለሥዕልና ለመስቀል አይሰግድም፤ በሞቱ ቅዱሳን አማላጅነት አያምንም፤ ዝክርና ምዕዋት የሞተ ሰውን ሊያጸድቅ እንደማይችል ይናገራል፤ የልማድ ጾም ዋጋ እንደሌለው ይሰብካል፤ ቀናትን አያከብርም" ሲሉ የክሱን ጭብጥ በጉባኤው ፊት አብራሩ።

በቀረቡት ክሶች ላይ ከፍ ያለ ክርክር ከተደረገ በኋላ ጳጳሱ ከባልደረቦቻቸውና ከመኳንንቱ ጋር መክረው ለወደ ፊቱ ይህን ትምህርት እንዳያስተምሩ ገሥጸው አሰናበቷቸው። በአለቃ ታዬ መለቀቅ የተበሳጩት ካህናት በጊዜው የአፄ ምኒልክ ባለሙሉ ሥልጣን እንደ ራሴ ለነበሩት ለራስ ተሰማ በማመልከት ያለ ሕግ ከታላቁ ወኅኒ ቤት እንዲገቡ አደረጉ።



አለቃ ታዬ ወኅኒ ቤት ታስረው ከከረሙ በኋላ ተፈቱ፤ ከዚያም በመጀመሪያ



www.ethiopianorthodox.org

ከደጃዝማች ሙሉጌታ፣ ቀጥሎም ከደጃዝማች ይገዙ በሃብቱ ጋር በቁም እስር እንዲቈዩ ተደረገ። በመጨረሻም በ1912 ዓ.ም. ለመንግሥት አማካሪነት ተመርጠው መሥራት ጀመሩ። ምሁሩ ታዬ የሕይወት ዘመናቸውን ከመከራ፣ከሥቃይ፣ከድካምና ከእንግልት ጋር ከገፉ በኋላ ነሐሴ 15 ቀን 1916 የሰው ልጆች ሁሉ ዕጣ ክፍል ወደ ሆነውና ከቶም ሊቀርበት ወደማይቻለው ዓለም አመሩ፤ ዐረፉ። እንደሚባለው በቀብራቸው ወቅት (እኅታቸው?) ወ/ሮ ላቀች አምንህ ያሞሹት የሐዘን እንጉርጉሮ፣አለቃ ታዬ ዘመናቸውን ሁሉ ከኢ-ፍትሓዊነትና ከአለማወቅ ጋር ያደረጉትን እልህ አስጨራሽ ተጋድሎ ሰብሰብ አድርጎ የሚያሳይ ይመስላል፦

*ከወኅኒ ቤት አስረው የዘጉበት ማንቃ፣*
*ብሎ ተናግሮ ነው የወንጌል ቃል ይብቃ።*
*የወንጌልን ሥርዐት ተማሩ ቢላቸው፣*
*ትልቁም ትንሹም ሁሉም ደደብ ናቸው።*
*ኤሉት ፀረ ማርያም መልስ ቢሳናቸው።*
*ዕውቀት እና ምግባር ጉድጓድ ተከተተ፤*
*አራት ነው እንጂ መች አንድ ሰው ሞተ።*
*ወዝውዘው ነዝንዘው ጣሉት እንደ ዝሆን፤*
*ያው ወደቀላቸው ይበሉት እንደሆን።*
*ከጨለማ መሃል ቢወጣ ብርሃን፣*
*አጥፉት አጥፉት አሉ እንዳይታየን።*







## መወድስ

ጽኑ አለቃ ታየ ጨለማውን ጠልቶ
ኢትዮጵያችን ትድመቅ አለ እጅጉን ጸንቶ

የጨለማውም ኀይል በጣሙን በርትቶ
ታየን ገዘገዘው ታገለው ጎትቶ

እውነት መያዝና የጥበብ ምርምር
ብዙ አይሞገስም በአበሻችን ምድር

እውነትና ጥበብ ቢቆስልም ቢደማም
ያሽልባል እንጂ ማገገሙ አይቀርም

ለአገርህ መንግሥት የቀናኸው ቅንአት
ታየ ዛሬ ደምቆ ፀሓይ ነህ የሌሊት







www.ethiopianorthodox.org

## ትምህርተ ውልብታ

ለተረዱትና ላመኑት እውነት ጸንተው መቆማቸው ታላቅ የጽናት ትምህርትን ይሰጣል።

ልክ የሚያስገቡ ጥበበኛ መልሶቻቸው በትምህርት መብሰል የሚያስገኘውን ጥቅም ያመለክታሉ።

የአገር ፍቅርና ዕድገት ቅንአታቸው የሚያስቀና ነው።

«ለካ ወንጌልንና አገርን አያይዞ መውደድ ይቻላል» የሚያሰኝ ነው። እንዲህም በመሆኑ በየእምነቱ ለሚገኙ የዛሬ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ትልቅ አብነት ነው።

የሰው ልጆች ለተሰማሩባቸው የሥራ መስኮች የሚሰጡት ክብር ትልቅ ምሳሌ ነው።





## የውልብታ ምንጭ

ኃይሉ ከበደ፣ የአለቃ ታዬ ገ/ማርያም የሕይወት ታሪክ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ፣1963

ኅሩይ ወ/ሥላሴ፣የሕይወት ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣1951

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፣አፄ ሚኒልክ እና ኢትዮጵያ ፣ብርሃን ይሁን፣አሥመራ፣1912

Aren, Gustav. *Envoys of the Gospel in Ethiopia*, Stockholm, 1999

__________*Evangelical pioneers in Ethiopia*; *Origins of the Evangelical church Mekane Yesus*. Stockholm & Addis Ababa, 1978

Baheru Zewde. *Pioneers of change in Ethiopia, The Reformist Intellectuals of the Early Twentieth Century, Oxford,* Athens, Addis Ababa, 2002.

__________ A History of modern Ethiopia 1855-1974.London, Athens & Addis Ababa, 1991

Getachew Hayle, Aasulv Land, Samuel Rubenson (eds.) *The Missionary Factor in Ethiopia*. Papers from a Symposium on the Impact of European Mis sions on Ethiopian Society, Lund University, Au gust 1996.

Prouty, Chris *Empress Taytu and Menilek II,* Ethiopia, 1883-1910.London, 1996.





www.ethiopianorthodox.org

## የአንባቢው የግል ማስታወሻ



፸፪



፬



**አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ**

**1864 -1936**

**የቀለም ቀንድ ፥ የቃላት ጉልላት**

ሥራን በሥራም ጭምር እንጂ በቃል ብቻ
መንቀፍ አይበቃም

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

የሥነ ጽሑፍ ጉዳይ ሲነሣ ስማቸው ዐብሮ የሚነሣ ታላላቅ ሰዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል አንዱ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (ከዚህ በኋላ ኪ.ወ.ክ.) ናቸው። ኪ.ወ.ክ. "**ታላቁ ሊቅ**" የሚያሰኛቸው አንድ ሁነኛ ምክንያት አለ፤ ይኸውም እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ከተሠሩ ታላላቅ ትምህርታዊና ሊቃውንታዊ ሥራዎች ተርታ በቀዳሚነት ሊሰለፍ የሚችል ሥራ ለሕዝብ ማበርከታቸው ነው። «**መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ**» **እና እንዲሁም** «**ሃይማኖተ አበው ቀደምት**» የተሰኙት ሁለት ሥራዎቻቸው እጅግ ፊር ቀዳጅ የሆኑ ናቸው። በተለይ የመጀመሪያው ሥራቸው ከእርሳቸው በኋላ መዝገበ ቃላት ያዘጋጁ ሰዎችንና ተቋሞችን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የኪዳነ ወልድ ክፍሌ ባለዕዳ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

«ሞት እንኳ ጨክኖ ወስዶ ከሚያስቀረው ምናለ ደጋጉን ዳግመኛ ቢፈጥረው» የሚለው የድምፃዊ ጥላሁን ገሠሠ ዜማዊ ቍጭት እውን ቢሆን ፣ በዚህ ምድር ላይ በሥጋ ዳግመኛ እንዲኖሩ ከምንመኛቸው ሰዎች አንዱ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ይሆኑ ነበር። ከታሪክ እንደምንረዳው ለመጪው ትውልድ ጠቃሚ ቅርስ አውርሰው ያለፉ ሰዎች ቍጥራቸው ጥቂት ቢሆንም በሥራቸውና በምሳሌነታቸው መጪውን ትውልድ ባለ ዕዳ አድርገውታል። እኛም የእነርሱን መልካም አርአያ እንድንከተል ሥራቸው ሁልጊዜ እነርሱን እንድንመስላቸው ጥሪ ያቀርባል። ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በጊዜው ማንም ሊደፍረው ያልቻለውን ሥራ የሠሩ ታላቅ ሰው ናቸው። ዛሬ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሊያብብ የቻለው፣ እኒህ ታላቅ ሰውና እርሳቸውን መሳዮች ካበረከቱልን ምርጥ የቃላት መድበል የተነሣ ነው።



ስለ ኪ.ወ.ክ. የተጻፈ ብዙ ነገር ባይኖርም፣ ታሪካቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ ባጭሩ የጻፉልን ዶ/ር ብርሃኑ አበበ የኪ.ወ.ክን ታሪክ በሦስት ዐበይት ዘመኖች አስፍረውታል፤[1] ይኸውም (1)



የወጣትነት ዘመን በመንዝ (2) የገዳም ሕይወት በኢየሩሳሌም (3) ሕይወት በድሬ ዳዋ (አልፎ አልፎ አዲስ አበባ በመመላለስ)።

ኪ.ወ.ክ. ሙሉ ስማቸው ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ወልደ አባ ተክሌ ነው (ወልደ አባ ተክሌ ወይም ቤተ ተክለ ሃይማኖት)።[2] ኪ.ወ.ክ. መንዝ ተጉለትና ይፋት ውስጥ ከነፋሻማነቱ የተነሳ «ቆብ አስጥል» በሚል ቅጽል በሚታወቅ ከረብታማ አካባቢ፣ ልዩ ስሙ እምቢጣጣ በሚባል ስፍራ በ1864 ዓ.ም. ተወለዱ። አባታቸው ደብሩ የውነቱ ይባላሉ። አያታቸው መምህር የውነቱ በጣም የተማሩ ሊቅ ሲሆኑ ኪ.ወ.ክ.ን የቁም ጽሕፈትና ሌላም ነገር ያስተማሯቸው እርሳቸው ናቸው።

ኪ.ወ.ክ. 20 ዓመት ሲሆናቸው ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ የምንኩስና ሕይወት ለመኖር ወሰኑ። ወደዚያም ሲያቀኑ በግብጽ ውስጥ አንድ ዓመት ያህል ቈዩ። ከዚያም በ1890 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም በሚገኘው የኢትዮጵያውያን ገዳም ገቡ። ኪ.ወ.ክ. በኢየሩሳሌም ሳሉ ለኑሯቸው የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ የሚያገኙት ከብዙ የውጭ አገር ሊቃውንት በሚቀርብላቸው ጥያቄ መሠረት፣ የብራና ጽሑፎችን በመገልበጥ ነበር። ሆኖም ለድካማቸው የሚከፈላቸው ገንዘብ በጣም አነስተኛ ነበር።

---

[1] ዶ/ር ብርሃኑ አበበ ከደስታ ተክለ ወልድ አንዳንድ መረጃዎችን ወስደው ይህን ዐጭር ታሪክ ባይጽፉልን ኖሮ፣ ስለ ኪ.ወ.ክ. የሚኖረን ዕውቀት ከዚህም ባነሰ ነበር። ይሁንና ዶ/ር ብርሃኑ አበበ ታሪካቸውን በፈረንሳይኛ ቋንቋ መጻፋቸው አሁንም ነገሩ በተወሰኑ ሰዎች ዘንድ ብቻ ታውቆ እንዲቀር አድርጓል። ዶ/ር ብርሃኑ አበበ እንደ ገለጹት ደ.ተ.ወ በሕይወት ሳሉ ስለ ኪወክ ባይነግሩን ኖሮ፣ ስለ እርሳቸው ብዙ የሚታወቅ ነገር ሊኖር ባልቻለም ነበር። ደግሞም ራስ ተፈሪ (በኋላ ንጉሥ ተፈሪ) ለኪ.ወ.ክ. የጻፉላቸው ወደ 15 የሚጠጉ ደብዳቤዎች የኪ.ወ.ክ.ን ታሪክ በጊዜ ቅደም ተከተል የሚሠሩት ሰብስቦ ለመያዝ ሁነኛ መንደርደሪያ ይሆናሉ። ራስ ተፈሪ እነዚህን ደብዳቤዎች ለኪ.ወ.ክ. የጻፉላቸው ከጥር 29 ቀን 1913 ዓ.ም. እስከ ኅዳር 27 1923 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ነው።

[2] "አባ ተክለ ሃይማኖት" የሚለውን ቅጽል ያገኙት "**ሃይማኖተ አበው ቀደምት**" ከሚለው መጽሐፋቸው ነው።



ኪ.ወ.ክ. "አስኬማ"[3] የሚለብሱበትን ቀን በጉጉት ሲጠባበቁ ሳለ የሕይወታቸውን ጉዞ ሙሉ በሙሉ የሚቀይር አንድ ክሥተት አጋጠማቸው፤ ያም በ1897 ዓ.ም. መምህር ክፍለ ጊዮርጊስ (ከዚህ በኋላ ክ.ጊ.) የተባሉ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣት ነበር። ክ.ጊ. ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጡ ኪ.ወ.ክ. የ27 ዓመት ወጣት ነበሩ። ሁለቱም የአንድ አካባቢ ተወላጆች መሆናቸውና ከካህናት ቤተ ሰብ መወለዳቸው ይበልጥ እንዲቀራረቡ ሳያደርጋቸው አልቀረም። ክጊ የኪ.ወ.ክ.ን ልዩ ተሰጥዖና ዝንባሌ ለማስተዋል ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም። ከዚህም በመነሣት በዘመናቸው ሁሉ ያካበቱትን ዕውቀትና ተመክሮ ለዚህ ትጉህና ንቁህ ወጣት ለማውረስ ቈርጠው ተነሡ። ክ.ጊ. ሮም ቈይተው ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጡ፣ ጅምር ሥራቸውን ከፍጻሜ የሚያደርስላቸው ሰው በብርቱ ይፈልጉ ነበር። ሁኔታውን ሲገልጹ፣ "ከመካከላቸው ከቶ አንድ ሰው ላገኝ አልቻልሁም፤ ከቶ አንድ ሰው። ለ2 ዓመት ያህል ፈለግሁ፤ በመጨረሻ ከ2 ዓመት በኋላ አንድ ታማኝና አስተዋይ ሰው አገኘሁ" ብለዋል። ይህ ሰው ሌላ ማንም ሳይሆን ኪ.ወ.ክ ናቸው። ክ.ጊ. ለዚህ ብልኅና አስተዋይ ወጣት በመሆናቸው ከቁርሎስ፣ ከዮሐንስ አፈወርቅና ከኤጲፋንዮስ በመጀመር መጽሐፈ ሊቃውንትንና መጽሐፈ አቡሻህርን (የዘመናትና የቀናት አቆጣጠር) በሚገባ አስተማሩ።

ክፍለ ጊዮርጊስና ኪዳነወልድ ለ11 ዓመት ያህል በኢየሩሳሌም ዐብረው ኖሩ። መለያየት ግድ የሆነባቸው ክ.ጊ.ን ነጣቂው ሞት በ1908 ዓ.ም. ሲወስድባቸው ነው። ክ.ጊ ጅምር ሥራቸውን ሁሉ በዐደራ ያስረከቡት ለኪ.ወ.ክ. ነው። ኪ.ወ.ክ.ም የተረከቡትን ዐደራ ፈጸሙ እንጂ መምህራቸውን አላሳፈሩም። ይልቁንም የዕብራይስጥ፣ የሱርስትና የጽርእ (ግሪክ) ቋንቋዎችን በማጥናት የመምህራቸውን ሕልም እውን ለማድረግ ይተጉ ጀመር።

---



[3] **አስኬማ** በቁሙ *(Literally)* ልብሰ ምንኵስና ማለት ነው፤ ከተሚስ፣ ከቅናት፣ ከቆብ በኋላ በመጨረሻ የሚለበስ ማለትም የፍጻሜ የምንኵስና ምልክት ነው። ከአስኬማ በኋላ ባሕታዊ እንደ ሆኑ መኖር እንጂ ከገዳም መውጣትና ወደ ዓለም መግባት ክልክል ነው።



ኪ.ወ.ክ. ከመምህራቸው ሞት በኋላ ሌላ 11 ዓመት ተደምሮ ንጉሥ ተፈሪ እስከ ጠሯቸው ጊዜ ድረስ ለ30 ዓመታት ያህል በኢየሩሳሌም ኖሩ። በኢየሩሳሌም ሲኖሩ ቈይተው ወደ አገራቸው ተመልሰው መጡ። "የመጡበትም ምክንያት የኢትዮጵያ መንግሥት ዐልጋ ወራሽ (በኋላ ቀዳማዊ ዐፄ ኀይለ ሥላሴ) ትችል እንደ ሆነ መጥተህ ሕዝቅኤልን ተርጕምልኝ የሚል ደብዳቤ ስለ ጻፉላቸው ነው"። ስለዚህ የኪዳነ ወልድ ክፍሌ ከክፍለ ጊዮርጊስ ጋር መገናኘትና ከኢትዮጵያ ንጉሥ የተደረገላቸው የአገልግሎት ጥሪ ሁለት ታላላቅ የሕይወታቸውና የሙያቸው ምእራፎች እንደሆኑ ሊታሰቡ ይችላሉ።

ኪ.ወ.ክ ብዙ ነገር የተማሩት ከመምህር ክ.ጊ. (1825-1908) ነው። ክ.ጊ. ስመ ጥር ሊቅ ናቸው። ደስታ ተክለ ወልድ (ከዚህ በኋላ ደ.ተ.ወ.) በመጽሐፋቸው መቅድም ላይ ስለ መምህር ክጊ ታላቅነት እንዲህ ይላሉ፤ "ከኢትዮጵያ ሊቃውንት በዕውቀት መዝመሪያ . . . አራት ዐይና . . . ታላቁ ሊቀ ሊቃውንት ያንኮበሩ መምህር . . ."። በኢትዮጵያ ውስጥ "አራት ዐይና" ተብለው የተጠሩ ሰዎች በጣም ጥቂት ናቸው፤ አራት ዐይና ማለት የአራቱ ጉባኤ ማለትም የብሉይ፣ የሐዲስ፣ የሊቃውንትና የመጽሐፈ መነኮሳት ሊቅ ማለት ነው።

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱትና የሥራውም ትልቅነትና ጥራት እንደሚጠቁመው ይህ የግእዝ-አማርኛ መዝገበ ቃላት ሥራ የአንድ ሰው ሥራ ነው ለማለት አያስደፍርም። ስለዚህ የተጀመረው በመምህር ክፍለ ጊዮርጊስ ነው።[4] በመሆኑም ክፍለ ጊዮርጊስ ጧትና ማታ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ጅምር ሥራውን ከዳር እንዲያደርሱት መወትወታቸው አልቀረም።

---

[4] ክፍለ ጊዮርጊስ በአቡጊዳ የፊደል ተራ ያዘጋጁት የግእዝ መዝገበ ቃላት አለ፤ ይህ መዝገበ ቃላት ለኅትመት አልበቃም፤ በእጅ እንደ ተጻፈ ነው፤ ሆኖም ሦስት ቅጆች አሉ። ማርሴል ኮኸን እንደሚለው የመጀመሪያው ቅጅ የተዘጋጀው በ1880 ዓ.ም. ነው።





www.ethiopianorthodox.org

የብርሃን መስቀል ደጀኔና የጌታሁን ሽብሩ «የሥርቱምእት፥ የብርዕ ምርት»የተሰኘ ድንቅ የጸሕፍት አሻራ አሰሳ እንደሚያመለክተው፣ ጥበብ ጥመኛው ክፍለ ጊዮርጊስ፣ የሕይወት ሥጋ መዘጊያቸው መዳረሱ በገባቸው ጊዜ ዐደራቸውን አጠበቁ፣ እንዲህ ብለው፦

> ልጄ ሆይ፣ ይህንን ግስ ማሳተም ብትፈልግ እንደገና ጥቂት ዕብራይስጥ ተምረኽ ማፍረስና ማደስ አለብህ፤ በመገርመሪያው አበገደን ጥፈህ የፊደሉን ተራ በዚያው አስኪደው። አንባቦችም እንዳይቸገሩ ከፊደል ቀጥለኽ ዐጭር ሰዋሰው አግባበት፥ የጎደለውና የጠበበው ኹሉ መልቶ ሰፍቶ ሊጣፍ ፈቃዴ ነው፤ ከሊላው ንግድ ይልቅ ይህንን ፩ መክሊት ለማባዛትና ለማበርከት ትጋ፤ ዘር ኹን ዘር ያድርግኽ ፤ ካላጣው ዕድሜ አይንፈግህ፤ ለሀገርኽ ያብቃህ …

ኪዳነ ወልድ የመምህራቸውን ጉትጎታ ቸል ሳይሉ ሥራውን በሙሉ ኀይላቸው ቀጠሉ። ሆኖም እርሳቸውም እርጅና ጠላት ሆነባቸው። ስለዚህ ከዓመታት በፊት በአንድ አጋጣሚ የደስታን የግእዝ ችሎታ ተረድተው ስለ ነበር ዐደራውን ከደስታ ሌላ የሚቀበል ሰው እንደሌለ ተገነዘቡ። ደስታንም ጠርተው ዐደራውን ተቀበል፤ ሥራውንም ከዳር አድርሰህ ለኅትመት አብቃው አሏቸው። ከብዙ ድካምና ጥረት በኋላ ደስታ በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የግእዝ-አማርኛ መዝገበ ቃላት በ1948 ዓ.ም. በኪዳነ ወልድ ክፍሌና በክፍለ ጊዮርጊስ ስም አሳተሙ።[5] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የሞቱበትንና (1934 ዓ.ም.) ደስታ ተክለ ወልድ መዝገበ ቃላቱን ያሳተሙበትን ዘመን (1948 ዓ.ም.) ስናነጻጽረው፣ ደስታ የመምህር ክፍለ ጊዮርጊስንና የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን ሕልም እውን ለማድረግ ቢያንስ 14 ዓመት ደክመዋል ማለት ነው። ኪዳነ ወልድ የግእዙን ሰዋስው መዝገበ ቃላት ጽፈው በመጨረሻ በደ.ተ.ወ. አማካይነት እስከ ታተመበት ድረስ ሥራው በጠቅላላ 30 ዓመታት ፈጅቷል።



[5]ብዙ ጊዜ ልብ እንለውም እንጂ በመዝገበ ቃላቱ አርእስት ገጽ (title page) ላይ የተጠቀሰው የሁለቱም ስም ነው (በአርእስት ገጹ ለይ "እምኀበ መምህር ዐቢይ ክፍለ ጊዮርጊስ ወእምኀበ ረድኡ ንኡስ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ወልደ አባ ተክሌ" የሚል ተጽፎ እናገኛለን)።



እንግዲህ በመዝገበ ቃላቱ ሥራ ውስጥ ሦስት ታላላቅ ሰዎች ተሳትፈዋል ማለት ነው። ይህ ሥራ በኢየሩሳሌም ተጀመረ፤ በድሬዳዋ ቀጠለ፤ በአዲስ አበባ ታተመ።[6] በዚህም ደ.ተ.ወ ዐደራ ጠባቂ በመሆናቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

ደስታ ተክለ ወልድ (የኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት አሳታሚ) በመዝገበ ቃላቱ መግቢያ ላይ እንደ ገለጹት ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በርግጥም "ታላቁ ሊቅ" ናቸው። ምክንያቱም በመዝገበ ቃላቱ ውስጥ የምናገኘው የቃላትን ፍቺ ብቻ ሳይሆን የመጻሕፍትንና የነገረ መለኮትን ትርጓሜም ጭምር ነው። መዝገበ ቃላቱም በርግጥም "ብርሃናዊ መጽሐፍ" ነው። ምክንያቱም ከቋንቋ ጀምሮ እስከ ወግና ባህል፣ ከሰዋስው ጀምሮ እስከ ትርጓሜ ድረስ መሠረታዊ ዕውቀትን ይገልጥልናል።

ኪ.ወ.ክ. በሕይወት ዘመናቸው ከዐምስት በላይ መጻሕፍት ጽፈዋል። መጻሕፍቱ በጊዜ ቅደም ተከተላቸው መሠረት (1) መጽሐፈ ሕዝቅኤል (2) አበገደ (3) መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ (4) መዝገበ ፊደል (5) ሃይማኖተ አበው ቀደምት ናቸው። የኪ.ወ.ክ. የአንድምታ ትርጓሜ የላቀ ምሁራዊ ትንተና ታይቶበታል። በአንድምታቸው ውስጥ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን፣ ፊልዮን፣ ሰብዓ ሊቃናትን፣ የኢየሩሳሌምንና የዮናታንን ትርጉም፣ ሚድራሽን፣ ሊቃውንተ አይሁድን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትንና ዐውደ ጥበባትን፣ በዐረብኛና በሌሎች ቋንቋዎች የተጻፉ መጻሕፍትን አመሳክረዋል።

[6] ኪዳነወልድ ክፍሌ ከዚህ ዓለም ሊሰናበቱና የጀመሩትንም ሥራ ከዳር ሊያደርሱት እንደማይችሉ በተረዱ ጊዜ ደስታ ተክለወልድን ለሥራው ያጩቸዋል። ይህ በአንድ በኩል ለደስታ የሥራ ዕድል የከፈተ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ግን የደስታን መጪ ሕይወት ፍጹም የቀየረ ነበር። ኪዳነወልድ ክፍሌ በወቅቱ ድሬ ዳዋ በሚገኘው የአላዛር (የላዛሪስት) ማተሚያ ቤት ተቀጥረው ይሠሩ ነበር። ደስታንም የጠየቋቸው ተመሳሳይ ሥራ አብረው እንዲሠሩ ነበር። ደስታ ድሬ ዳዋ በዚህ ሥራ ላይ ለ16 ዓመት ከቆዩ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በመጀመሪያ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በኋላም በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ሠርተዋል። በድምሩ 46 ዓመት በማተሚያ ቤት ሠርተዋል።





www.ethiopianorthodox.org

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እንደሚመሰክሩት እስከ ዛሬ ድረስ በመጽሐፈ ሕዝቅኤል ላይ ይህን የመሰለ አንድምታ አልተጻፈም።[7]

ከእነዚህ በእጅጉ የሚልቀው "**መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ**" ነው። ሞልቬር እንደ ገለጸው ይህ መዝገበ ቃላት በኢትዮጵያ ውስጥ የታተመ የመጀመሪያው ትልቁ የግእዝ-አማርኛ መዝገበ ቃላት ነው። መዝገበ ቃላቱ ሁለት ዐበይት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል (ገጽ 1-191)፣ ስለ ኪ.ወ.ክ.ና ስለ ክ.ጊ. ሕይወት በዐጭሩ ይተርክና ወደ ረጅሙ የሰዋስው ሐተታ ይዘልቃል። ሁለተኛው ክፍል (193-908) በአበገደ የፊደል ተራ መሠረት የመዝገበ ቃላቱን ትንተና ይቀጥላል። ኪ.ወ.ክ ይህን **መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ** የተሰኘውን መጽሐፍ ሲያዘጋጁ አያሌ መጻሕፍትን አመሳክረዋል። መዝገበ ቃላቱን ለማዘጋጀት በምን ያህል ምንጮች እንደ ተጠቀሙ ለማወቅ በመጽሐፉ ላይ የዘረዘሯቸውን 64 መጻሕፍት መመልከቱ ብቻ በቂ ነው።

እንዲህ ዐይነቱ ታላቅ ሥራ ብዙ ጥረት ይጠይቃል። ብዙ ማሰብንና ብዙ ማገናዘብን ይፈልጋል። ጥቂት ቀናት ወይም ጥቂት ወራት ብቻ ሳይሆን ሥራው ለኅትመት በቅቶ በሰው እጅ እስኪገባ ድረስ ብርቱ ትጋት ይሻል። እኚህ ሊቅ ይህን ሥራ እንዴት ከዳር ሊያደርሱት እንደ ቻሉ ደስታ ተክለ ወልድ ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፤ "[ኪዳነ ወልድ ክፍሌ] በሥራ ውለው ማታ ነፋስ በመቀበል ጊዜ አንድ ሐሳብ ቢያገኙ፣ በማስታወሻ ለመጻፍ ከውጭ ወደ ቤት ይመለሳሉ። በምሳ ወይም በራት ጊዜ አንድ ትርጓሜ ቢታሰባቸው ምግቡን ትተው ብድግ ይላሉ። ሌሊትም ተኝተው ሳሉ አንድ ምስጢር ቢገለጥላቸው፣ ከመኝታቸው ተነሥተው መብራት አብርተው ይጽፋሉ" ዛሬ በእጃችን የሚገኘው መዝገበ ቃላት አንድ ለትውልድ የሚያስብ ትጉህና ቅን ሰው ከዕድሜው ክፍሎና ሕይወቱን ሠውቶ ያበረከተልን ውድ ስጦታ ነው።



[7] አንድ መምህር በግል የሰጡት አስተያየት። መጽሐፉ ከታተመ ከ74 ዓመታት በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ በኢ.ኦ.ተ.ቤ. አማካይነት ሲታተም የጸሐፊው ስም በሽፋኑ ላይ አልተጠቀሰም። ስማቸው የተጠቀሰው ለመጽሐፉ በተዘጋጀው መልእክት ላይ ነው። በፊት የነበረው የትርጓሜ ስልት ሳይፈጠመርበትና ሳይቀነስለት ታትሟል።



ደስታ ተክለ ወልድ እንዳሉትም "ሥራቸው... የኢትዮጵያን ልጆች ዘላለም ሲያስተምር ይኖራል።"

አለቃ ኪዳነ ወልድ እንደሚሉት ይህ መዝገበ ቃላት ጥልቅ ጥናትና ምርምር ተደርጎበታል። "ሥራን መንቀፍ በሥራ ነው እንጂ በቃል ብቻ መንቀፍ አይበቃም" የሚለውን ብሂል ሲጠቅሱ ለሥራቸው ምን ያህል ትኩረት እንደሰጡ መግለጻቸው ነበር። ስሕተትን ስሕተት ነው ለማለት ስሕተቱ የቱ ላይ እንደሆነ ማሳየት ያስፈልጋል። ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በመዝገበ ቃላታቸው ውስጥ ብዙ ጊዜ "አያሰኝም" የሚል ቃል ተጠቅመዋል። ይህን በሚሉበት ጊዜ ሁሉ "አያሰኝም" ያሉበትን ምክንያት ጠቅሰዋል። ይህ የሚያሳየው የሚነቅፉትን ነገር በደፈናው ሳይሆን በምክንያት እንደሚነቅፉ ነው። ለዚህ ደግሞ ምርምርና ጥናት ያስፈልጋል። የጉዳዩም ባለቤት መሆን ያሻል።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ለሆህያት ትልቅ ስፍራ ይሰጣሉ። ቃላትን በመደበኛው ሆሄያቸው አለመጻፍ እርሳቸው እንደሚሉት ጸያፍ ብቻ ሳይሆን ግፍ ነው። ርግጥ ሦስቱ ሀ፣ሐ፣ኀና ሁለቱ አ፣ዐ፤ ሁለቱ ሠ፣ሰና ሁለቱ ጸ፣ፀ የድምፅ ልዩነት ባይኖራቸውም የመልክ ልዩነት አላቸው፤ ከሁሉ በላይ ግን ምስጢራቸውና ትርጒማቸው እንደ መልካቸው ለየቅል ነው። ስለዚህ "የሦስቱ ሀ፣ሐ፣ኀ፣ የሁለቱ ሠ፣ሰ፣ የሁለቱ አ፣ዐና የሁለቱ ጸ፣ፀ አገባብና አጠቃቀም ስሕተት እንዳይታይበት መጠንቀቅ ያስፈልጋል" ይላሉ።[8]

በርግጥ የኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ግር የሚያሰኝ ነገር ይታይበታል። ይኸውም የመዝገበ ቃላቱ የፊደል ተራ የ"ሀለሐመ"ን ሳይሆን የጥንቱን የአሌፋትን ማለትም የ"አበገደ"ን መንገድ መከተሉ ነው። ይህም ለዚህ ዘመን አንባቢ ነገሩን ውስብስብ ያደርግበታል። የሚፈለገውን ቃል ቶሎ ፈልጎ ለማግኘትም ያስቸግረዋል።



[8] አንድን ቃል በትክክለኛው ፊደል (ሆሄ) አለመጻፍ ትልቅ የትርጒም ልዩነት ያመጣል። ለምሳሌ ምሁር በዕውቀት የኀለበተ፥ ሊቅ ምሑር ይቅር የተባለ፤ ምሕረት ያገኘ።



www.ethiopianorthodox.org

አንባቢዎች እንዳይቸገሩ ሌሎች አርታዕያን በ"ሀለሐመ" የፊደል ተራ የሚዘጋጅበትን መንገድ ምናለ ቢፈልጉልን ያሰኛል። የፊደል ተራው እንደሚከተለው ነው፤ አ, በ, ገ, ደ, ሀ, ወ, ዘ, ሐ, ኀ, ጠ, የ, ከ, ለ, መ, ነ, ሠ, ዐ, ፈ, ጸ, ፀ, ቀ, ረ, ሰ, ተ, ጰ, ፐ። ደ.ተ.ወ. የፊደል ተራው ለምን በአበገደ መንገድ መሆን እንዳለበት አንድ ምክንያት ይጠቅሳሉ። "ኢዝንበርግ በትግሬ አውራጃ ሳለ አበገደን ከግራ ወደ ቀኝ በደንጊያ ተቀርጾ ስላገኘው ሥዕሉን አንሥቶ በግሱ ውስጥ አሳትሞታል፤ ስለዚህ አበገደ ጥንታዊ ነው እንጂ እንደ ሀለሐመ ኋለኛ አይደለም"። ኪ.ወ.ክ.ም መዝገበ ፊደል በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ የጥንቱ መንገድ አበገደ እንደሆነና ከእኛ በቀር በሀለሐመ የሚጀምር እንደሌለ በመግለጽ "በዚያው በዱሮው መንገድ በዱሮው አካሄድ በጥንቱ ተራ አበገደ ብለን እንጥፋለን" ይላሉ። ለጥንታዊው ለአበገደ የፊደል ተራ የተቀኙት ግጥም እንዲህ ይላል፦

የጌታችን ዕድሜ ሰባት ዓመት ሲያኽል
ለመምር ሰጡችው እናቱ ድንግል።
መምሩም ሲያስተምረው አለው አሌፍ በል
በታምረየስ ተጽፏል ይህ ቃል።
ጌታም ለመምሩ ጥያቄ ሰጠው
ምስጢረ ፊጣሪን ገልጦ ሊያስረዳው
ምንት ትርጓሜሁ ለአሌፍ አለው።
አሌፍ ስለ ኾነ የፊደሎች በኩር
የትም አገር የለ በሀ መጀመር።
ዕብራይስጥና ዐረብ ሱርስትም ይቅሩና
በትግሬ ግዛት በአኵስም መዲና
የሳባ ፊደል ግእዝ ያባተው
በአ ነበርና የሚጀምረው
ለሀ መነሻነት ምስክር የለው
እንዲያው ፈጠራና ልብ ወለድ ነው።




ኪዳነ ወልድ የቋንቋ ሊቅ ናቸው። ከግእዝና ከዐማርኛ ቋንቋዎች በተጨማሪ የዕብራይስጥ፣ የሱርስት፣ የጽርእ (ግሪክ)፣ የሮማይስጥና (ላቲን)፣ የዐረቢኛ ቋንቋዎችን ይችላሉ። በመዝገበ ቃላታቸው ውስጥ ከእነዚህ




ቋንቋዎች የተወረሱ ቃላትን ያለ ምንም መግለጫ እንዳለ ይጠቀሙባቸዋል። ቃላቱ ከእነዚህ ቋንቋዎች እንደ ተወረሱ የማያውቅ አንባቢ የግእዝ ቃላት ሊመስሉት ይችላሉ።[9]

ኪ.ወ.ክ.ለቋንቋ ብቻ ሳይሆን ለነጻነትም ተጋድለዋል። ከዚህም የተነሣ ለእስር የተዳረጉበት ጊዜ ነበር። በተለይ በ1929 ዓ.ም. ቀዳማዊ ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ከስደት ወደ አገራቸው ተመልሰው ሲመጡ ኪ.ወ.ክ. ነገሩን ያዩ ያዙት ከነጻነት ጋር ነበር። የንጉሡ ነገሥቱ ተመልሶ መምጣት ግን ለፋሺስቶቹ የሚዋጥ ነገር አልነበረም። ስለዚህ ለንጉሠ ነገሥቱ ቀኝ እጃቸውን የሰጡ ሁሉ በጣሊያኖች ጥርስ ውስጥ ገቡ። ኪ.ወ.ክ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪቃ ነጻነት በድፍረት የሚናገሩ ሰው ነበሩ። ይህ ይበልጥ በጣሊያኖች እንዲጠሉ አደረጋቸው። በመሆኑም ጣሊያኖች ኪ.ወ.ክን ወደ ወኅኒ ጣሏቸው። ደ.ተ.ወ. እንደ ገለጹት ፋሺስቶች ኪ.ወ..ክን በጨለማ ውስጥ አስረዋቸው ስለ ነበር ዐይናቸው ጠፋ! ኪ.ወ.ክ. በአንድ በኩል ለቋንቋ እድገት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለአገር ነጻነት ብርቱ ትግል አድርገዋል። በዚህም ለመጪው ትውልድ ቅርስንና ምሳሌነትን ትተዋል። ኪ.ወ.ክ. ዐይናቸው ቢጠፋም እንኳ በሕይወት እስካሉ ድረስ ቁም ነገር ሠርተው ለማለፍ የተጉ ሰው ነበሩ። ደ.ተ.ወ. እንደ ገለጹት የሀገርና የስም ተራ ለመሰብሰብና ለመተርጐም ዐስበው ነበር። ይሁንና አይቀሬው ሞት ማንንም እንደሚገዳደርና እንደሚጥል ሁሉ እርሳቸውንም ተገዳደራቸውና ጣላቸው።

ኪ.ወ.ክ. የመጨረሻ የሕይወት ዘመናቸውን ያሳለፉት በችግር ነው። እንደሚታወቀው በዓለማችን ላይ ታላላቅ ሥራ ያከናወኑ ሰዎች ለትልቅ ስኬት የበቁት በብዙ ችግርና መከራ ውስጥ ዐልፈው ነው። ብዙዎቹ ተርበዋል፤ ተጠምተዋል፤ ታርዘዋል። ለስደትና ለእስርም የተዳረጉ ብዙዎች ናቸው። ኪ.ወ.ክ.ም እነዚህን የመሳሰሉ ታላላቅ ሥራዎችን ሲያከናውኑ ብዙ ፈተና ደርሶባቸዋል።

---

[9] ለምሳሌ ናፋል (ወደቀ ማለት ነው) እና ዶድ (አጐት ማለት ነው) የተወሰዱት ከዕብራይስጥ ነው። አበደን (ፈጽሞ፣ በጭራሽ ማለት ነው) እና ቦለድ (አገር ማለት ነው) የተወሰዱት ከዐረብኛ ነው።






www.ethiopianorthodox.org

በአንድ ወቅት እንዲያውም የሚበሉትና የሚጠጡት ዐጥተው የከፋ ሥቃይ ላይ ወድቀው ነበር። ችግራቸውን ተረድተው ቀዳማዊ ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ቀለብና ድርጎ ባይሰፍሩላቸው ኖሮ፣ የመጨረሻ ዘመናቸው ይበልጥ አስከፊ ይሆን እንደ ነበር መገመት ይቻላል። የክቡር ብላታ አሽኔ ኪዳነ ማርያም ባለቤት ክብርት ወይዘሮ በላይነሽ ጉበና ኪ.ወ.ክ.ን በመርዳትና በመደገፍ ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል። ከቀዳማዊ ዐፄ ኀይለ ሥላሴ የተፈቀደላቸውን ቀለብና ድርጎ አብቃቅተው የሚሰጧቸው ወይዘሮ በላይነሽ ነበሩ።

ለግእዝና ለዐማርኛ መስፋት የጣሩና የተቈረቈሩ ሰዎች ባይኖሩ ኖሮ፣ ዛሬ ቋንቋችን እንዲህ ሞልቶና ሰፍቶ ለማየት ባልተቻለም ነበር። ደ.ተ.ወ. እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፤ "ዐማርኛችንንም ኢዝንበርግ በእንግሊዝኛ፣ አንቷን ዳባዲ በፈረንሳይኛ፣ ጕይዲ በጣሊያንኛ ጽፈውት አየን እንጂ ያገራችን ሊቃውንት የጻፉትን ባይናችን አላየንም፤ በጆሯችንም አልሰማንም። በቃል ያለ ይረሳል፤ በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል በማለት ለግእዙም ኾነ ላማርኛው ከመምህር ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በቀር ያሰበለትና የጣረለት፣ የተቈረቈረለት አንድም አልተገኘም"። ኪ.ወ.ክ. ለዐማርኛና ለግእዝ ቋንቋ መስፋት የነበራቸው ምኞት ወደር የለውም። ይህን ብርቱ ምኞታቸውን እንዲህ በለማት ገልጸውታል፦

እናንተ እንጂ ናችኹ የፍሬቃ ራስ ቅል፣
ባለ ዘውድ ቋንቋ ባለ ነጻ አክሊል።
ግእዝ ዐማርኛም ኹለቱ ቋንቆች፣
ታላቅ ታናሽ አባይ የፍሬቃ ወንዞች፣
ካፍሪቃ ዐልፈው ተርፈው በባሕር በየብስ፣
ገና ይሰፋሉ እንደ ግዜር መንፈስ።
ስላማርኛና ስለ ግእዝ ክብር፣
ዋዜማ ተቂሟል በብዙ አህጉር።



የቃላት ጉልላቱ፣ የቀለም ቀንዱ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ እያደር የስኳር በሽታና የጆሮ ህመም ጠናባቸው። ሥራ የሚኑዋቸው ሹማምንት ቸል ባሏቸው ጊዜ፣ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር በነበሩት፣ በ «ቀለሙ ሰው» በከበደ



ሚካኤል ተራዳኢነት በራስ ደስታ ሆስፒታል ሲታከሙ እንዲቆዩ ቢደረጉም፣ እርሳቸው ግን ግዙፉ ሥራቸውን ተድመው ተከናወኑ። እናም 20 ዓመት በመንዝ፣ 30 ዓመት በኢየሩሳሌም፣ 22 ዓመት በድሬዳዋና በአዲስ አበባ ሲማሩና ሲያስተምሩ ኖረው "በተወለዱ በ72 ዓመታቸው ቅዳሜ ሰኔ 24 ቀን 1936 ዓ.ም ዐርፈው ደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ።"

ኪ.ወ.ክ. ብዙ አልመው ብዙ የሠሩ ሊቅ ናቸው። በአንድ ወቅት ስለሚሠሩት ሥራ ልመናና ምልጃ (ስእለት ወአስተብቍዖት) አቅርበው ነበር። ልመናውና ምልጃው የተማሩትን ለሌሎች ሳያስተምሩ እንዳለ ይዘው ከዚህ ዓለም እንዳያልፉ ነው። ይህም ቢሆን በታላቅ ትሕትና የቀረበ ነው። እንዲህ ይላል፦

ይኽን ጨቅላ መጽሐፍ የምታዩ ኹሉ፣
ዐደራ ስለኔ ማርያም ማርያም በሉ፤
በሆዴ ያለውን የትምርት ሽል፣
አለጭንቅ እንድወልድ እንድገላገል፤
ከኻያ ስድስቱ ወንዶች ፊደላት፣
አርግዣለሁና መዝገበ ቃላት።

ስንት እልፍ አበው ናቸው አርግዘው የሞቱ
ቀኝ እጃቸው ዐጥሮ ጥፈት በማጣቱ፤
እጄ እንዳባቶቼ እጅ ተምሮ ባይጥፍ፣
ከሆዴ ባሎጣም ይህ ጨቅላ መጽሐፍ።
ለትምክሕት አይዶለም ይህን መናገሬ፤
ለማስቀናት እንጂ ሰነፉን ገበሬ፤
ሐዋርያም ሲጥፍ ወዳርድእቱ መንጋ፣
ቅኑ አስቀኑ ይላል ለምትበልጥ ጸጋ።[10]

ከአባቶች ተምረን፣ ሥራቸውን ዘክረን፣ ንጹሕ ዘር ዘርተን እንድናልፍ አንድዬ እኛንም ቀኖችና ትሑቶች ያድርገን!!

---

[10] ኪወክ በዚህ ቅኔ በአንድ በኩል ወደፊት ለሕዝብ የሚያበረክቱት መዝገበ ቃላት እንዳለ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አሁን ለሕዝብ ያበረከቱት መጽሐፍ እንዳለ (መዝገበ ፊደል) እየተናገሩ ነው። ዋናው መልእክት ግን ትኅትና ይመስላል።





www.ethiopianorthodox.org

## መወድስ

ከክፍለ ጊዮርጊስ አደራውን ወስዶ
ከታማኙ ደስታ በሥራው ተጣምዶ
መዝገበ ቃላቱን ተማምጦ ወልዶ
የፊደል ገበታ የቋንቋ ሥርዓቱ
የቃላት የት መጣ ሥርወ መሠረቱ
ውበቱ እንዲጠበቅ ታገለ በበርቱ
ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ልሳነ በዕሩ
ሞት ጨክኖ ወስዶት ይናገራል ግብሩ

## ትምህርተ ውልብታ

ወዲያው የሚታይ ውጤት ባይኖረውም አንድን ነገር ግብ ለማድረስ መሥዋዕት ለመክፈል መዘጋጀት።

ትልቅ ሥራ ግቡን የሚመታው በኅብረትና በሥራው ዓላማ አምነው ከሚሰለፉ ሰዎችጋር አብሮ በመሥራት ነው።

ከመምህር ክፍለ ጊዮርጊስ፣ ከአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌና ከደስታ ተክለወልድ ሕይወት የእውነተኛ ጓደኝነት ትርጒም ይታያል።






## የውልብታ ምንጭ


Berhanu Abebe, *The faith of forefathers Ethiopian text Teachings of Memher Kifle Giorgis, put together by Aleka Kidane Wold Kifle, compiled by his disciple Desta Tekle Wold with an introduction on the lives and works of these three scholars.*

Cowley, Roger *A Geez Prologue Concerning the Work of Mamher Kefle Giyorgis on the Text and Interpretation of the Book of Ezekiel*, in Ethiopic Studies. Dedicated to Wolf Leslau on the Occasion of his Seventy-fifth birthday, November 14, 1981. Edited by Stanislav Segert and Andras Bodrogligeti (Wiesbaden: Otto Harrassowitz, 1983)

Leslau, Wolf, *Comparative Dictionary of Geez (Geez-English and English-Geez)*, Wiesbaden: Otto Harrassowitz, 1987.

_________, *Concise Dictionary of Geez*, Wiesbaden: Otto Harrassowitz, 1989.

Molvaer, Reidulf K., *Black Lions: The Creative Lives of Modern Ethiopia's Literary Giants and Pioneers*, Lawrenceville: The Red Sea Press, Inc., 1997.

Ullendorff, Edward, *The Ethiopians: An Introduction to the Country and People*, London: Oxford University Press, 1960.

ደስታ ተክለ ወልድ፣ *ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት* (አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962)።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ* (አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948)።

_________, *ሃይማኖተ አበው ቀደምት*።

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፣ አፄ ምኒልክ እና ኢትዮጵያ፣ ብርሃን ይሁን፣አሥመራ፣1912።


ብርሃነ መስቀል ደጀኔና ጌታሁን ሽብሩ ከ፲፱ እስከ ፳፻ ድርሰት ያሠሩት ምእት የብርዕ ምርት ክፍል ፩ ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፺፱






www.ethiopianorthodox.org

## የአንባቢው የግል ማስታወሻ





# ፫



**ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ**

**1878 – 1912**

**ቀድሞ መጣ ቀድሞ ሔደ ሩቅ አሰበ ቅርብ ዐደረ**

እውነተኛውንም ታሪክ ለመጻፍ ቀላል ነገር አይደለም፤
የሚከተሉት ሦስት የእግዚአብሔር ስጦታዎች
ያስፈልጋሉ፤ መጀመሪያ ተመልካች ልቡና
የተደረገውን ለማስተዋል፤ ሁለተኛ የማያደላ አእምሮ
በተደረገው ለመፍረድ፤ ሦስተኛ የጠራ የቋንቋ አገባብ
የተመለከቱትንና የፈረዱትን ለማስታወቅ ይረዳል..

www.ethiopianorthodox.org

ሻቃ ባይከዳኝ በ1882ቱ የመተማ ጦርነት ከንጉሥ ዮሐንስ ጋር ተሰልፈው ሲዋጉ ቢሞቱም፣ እዚያው ትግራይ ለአድዋ ከተማ ቅርብ በሆነች በማይሚሻም ቀበሉ. በ1878 ዓ ም ከወይዘሮ ታለፉ ወልደ ሥላሴ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝን ወልደዋል። ወይዘሮ ታለፉ ባለቤታቸውን መተማ ጦር ሜዳ ቢያስቀርባቸው፣ በማይሚሻም አራት ዓመት ያህል በትዕግሥት ከቈዩ በኋላ የሰባት ዓመቱን ገብረ ሕይወት ይዘው ወደ ሀማሴን አቀኑ። ከዚህም የተነሣ የገብረ ሕይወት ቀዳሚ የልጅነት ኑሮ ለጥቂት ዓመታት ከእናቱ ጋር ቀጠለ። ነገር ግን ብዙም ሳይከራርም፣ በልጅነት እድሜው ከመሰል ጓደኞቹ ጋር በመሆን የምፅዋን ወደብ ተተግና የቆመች የጀርመን መርከብ ለመጐብኘት ወደ ውስጥ ዘልቆ እያለ 'የጓደኞቹን መውረድ ሳያስተውል' መርከቧ በመነሣቷ መዳረሻውን ነምሳ ኦስትሪያ አደረገ።

የመርከቧ ካፒቴን ገብረ ሕይወትን ለኦስትሪያዊቷ ለወ/ሮ ሶሬኔ አስረከበው። ወ/ሮ ሶሬኔም እንደ እናት ሆነው ገብረ ሕይወትን አስተማሩት፤ የጀርመንን ቋንቋ እዚያው ቤተ ሰብ ውስጥ ቀልጥፎ ተማረ። ጥቂት ቈይቶም በአሳዳጊዎቹ ድጋፍ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ በርሊን በመዝለቅ ዩኒቨርስቲ ገባ። እንደ ልጃቸው ባላምባራስ አሸብር ገብረ ሕይወት[1] አባባል፣«ገብረ ሕይወት በ18 ዓመቱ የሕክምና ድግሪውን አገኘ። በወቅቱ አፄ ምኒልክ ሐኪም እንዲላክላቸው የጀርመንን መንግሥት በጠየቁት መሠረት ገብረ ሕይወት ከዶ/ር ሰንቲግራፍና ካርልስ ጋር በመሆን ወደ ኢትዮጵያ መጣ። ይሁን እንጂ ገብረሕይወት አፄ ምኒልክን የማከም ዕድል ባያገኝም የንጉሡ ልዩ ጸሓፊና አስተርጓሚ ሆኖ አገልግሏል።»

---

[1] ባላንባራስ አሸብር ገብረ ሕይወት ሦስት መጻሕፍት ጽፈዋል፤ 1) የኪዳን ቃል፣ ቲያትር 1948 ዓም በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ታተመ፤ 2 ) የንግሥት አዜብ ታሪካዊ ጉዞ 1951 ዓም በንግድ ማተሚያ ቤት ታተመ፤ 3) ፍቅር አያረጅም በ1952 ዓም በንግድ ማተሚያ ቤት ታተመ፤ አሸብር ገብረ ሕይወት የሕግ ሙያን በስዊዘርላድ እንደ ተማሩ ፕሮፌሰር ባሕሩ ይጠቅሳሉ ገጽ 81





በምኒልክ የመጨረሻ የአገዛዝ ዓመታት የነበረውን የሥልጣን ሽኩቻ በዝምታ ማለፍ ያልፈለጉት ገብረ ሕይወት ከእቴጌይቱና ከመኳንንቱ ጋር ሊስማሙ አልቻሉም። በለውጥ ፈላጊነታቸው ሳቢያ በአንዳንዶች ዘንድ ለኢትዮጵያ ባህልና ሃይማኖት አሥጊ ሰው እንደ ሆኑ ተደርገው ተቈጠሩ። በተለይም በእቴጌ ጣይቱ አለመወደዳቸው ከቤተ መንግሥት አካባቢ ገለል እንዲሉ አስገድዷቸዋል። በዚህም ሳቢያ በትግራይ በኩል አድርገው ወደ ሱዳን በመሔድ ሁለት ዓመት ያህል እዚያ ቆዩ። ምንም እንኳ በዚህ የሱዳን ቆይታቸው ከጠሏቸው የቤተ መንግሥት ሹማምት ገሸሽ ቢሉም፣ ቅኝ ግዟ ሱዳን በልማት ከነጻይቱ ኢትዮጵያ ተሽላ ማየታቸው የበለጠ ቅንአት የጫረባቸው ጊዜ ነበር። የሁለት መጻሕፍት ደራሲ የነበሩት ገብረ ሕይወት በፖለቲካና በኢኮኖሚ ዙሪያ ጥልቅ የሆኑ ትንታኔዎችን እንደ ማንሣታቸው ማኅበራዊ ጉዳዮችንም ዳስሰዋል። ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ «የኢትዮጵያ ታሪክ» በተሰኘ መጽሐፋቸው ስለ ገብረ ሕይወት ሲጽፉ፦

> ከዘመኑ ምሁራን ሁሉ ልቆ የሚታየው ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ውጭ አገር ሄዶ ዘመናዊ ትምህርት ሊቀስም የቻለው በግል ጥረቱ ነው። ገና በሎርቃነቱ በመርከብ ተደብቆ ኦስትሪያ በመሄድ የሕክምና ትምህርት አጥንቶ ወደ አገሩ ተመለሰ። ተመልሶ ዓለምን ያስደነቀው ግን በሕክምና ጥበቡ ሳይሆን የፖለቲካ ኢኮኖሚን አበጥሮ በማወቁና በተለይም ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ለማዛመድ በመቻሉ ነው። እንግሊዞች ያስተዳድሯት በነበረችው በሱዳንም የዐጭር ጊዜ ቈይታው ነጻይቱ ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ከሆነችው ሱዳን ምን ያህል ወደ ኋላ እንደ ቀረች በመገንዘቡ ክፉኛ ታውኮ መጥቷል።

በማለት የነጋድራስነት ሹመቱም በሐረር በነበረበት የመንግሥት ሥልጣን እንደ ነበረም ተናግረዋል።

ትውልድ ሁሉ ከሚዘክራቸው የእኒህ ሰው ሥራዎች ውስጥ የተወሰኑት ተነቅሰው በተለይ በታሪክ ፣ በእምነትና በአገር ነክ ርእሶች





www.ethiopianorthodox.org

ላይ ያደረጉትን አስተዋፅኦ ለመግለጽ ቢያስፈልግ በቀዳሚ ምንጭነት የሚረዱ መጻሕፍት በ1904 ዓ.ም. «አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» እንዲሁም በ1916 እና በ1953 ሁለት ጊዜ የታተመው «መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር» በሚል ርእስ የጻፉት የራሳቸው የግብረ ሕይወት መጻሕፍት ናቸው። ምንም እንኳ እነዚህ መጻሕፍት የግብረ ሕይወት የአእምሮ ጭማቂና የብርዕ ጠብታዎች ቢሆኑም፣ ግብረ ሕይወት ግን ከእነዚህ መጻሕፍት መታተም ጋር ስማቸው እንዲጠቀስ የሚፈልጉት የሚከተሉት ሰው ናቸው፦

ይድረስ ካቶ ጳውሎስ መናመኖ
ወዳጄ ሆይ

እነሆ ከእግዚአብሔር በታች ባንተ ደግነት ከሞት ዳንሁ። በብርቱ ታምሜ ተስፋ ቈርጬ በምጥዋ በኦስፔዳሌ ወድቄ ሳለሁ በገንዘብህ አገገምኹኝ። ለቸሩ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ በመንገርህም የበለጠ የደግነት ሥራ አደረግህልኝ፤ እነሆም ላገራችን ጥቅም ይሆናል ስል ይህንን ትንሽ ቃል ለመጻፍ በቃሁ። የተመሰገንልኝም እንደሆነ ምስጋናው ላንተ ነው። ለእኔ ዕድሜ እንደሰጠህልኝ አምላክ ረጅም ዕድሜ ይስጥህ። ደግነትህን እስከ ሞት ድረስ ከማይረሳ።

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ

ጳውሎስ መናመኖ የግብረ ሕይወት ጤና እንዲሻሻል፣ እንዲሁም በፈረንሳይኛና በአማርኛ መጽሐፍ እንዲያዘጋጅ ምክንያት ከመሆን ባሻገር ገብረ ሕይወትም ከሞቱ በኋላ በእጃቸው ጽፈውት በጊዜው ግን ለኅትመት ያላበቂት «መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር» የተሰኘው መጽሐፋቸው እንዲታተምም ወደ አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የቀረቡ እኒሁ ጳውሎስ መናመኖ ለመሆናቸው በመጽሐፉ መግቢያ ላይ እንዲህ የሚል ይገኝበታል፦





ይድረስ

ለልዑል ጌታዬ የኢትዮጵያ መንግሥት ዐልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን፣ መድኅኒ ዓለም ጤና ይስጥልኝ ብዬ እጅ እነሣለሁ... ነጋድራስ ገብረ ሕይወት በትምህርቱና በዕውቀቱ በጣም የተመሰገነ ነበረ፤ በታዘዘውም ሥራ ላይ በጣም ትጉህ እንደ ነበር ጌታዬ ልዑልነታቸውም ያወቁታል። ነገር ግን በሰው ላይ ሞትን የሚያህል ዕዳ አለና ሰው ሁሉ ያሰበውን ለመፈጸም ባለመቻሉ እጅግ ያሳዝናል... የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ዕውቀት እንዲያው በከንቱ መቅረቱ ለወዳጆቹ ሁሉ በጣም ያሳዝናል። ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ሲሞት ዕድሜው ገና 31 ዓመት ነበረ። ገና 50ና እስከ 60 ዓመት ቈይቶ ቢሆን አሳቡ እየተደላደለ፣ ዕውቀቱ እየሰፋ ለመንግሥቱና ለሕዝቡ የሚጠቅም ብዙ ሥራ ይሠራ ነበር።...

ልዑል ሆይ

የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ስሙ እንዳይጠፋ ማሰብዎንማ በገንዘብዎ ልጁን ከትምህርት አግብተው በማስተማርዎ ተረድተነዋል። ደግሞም ልጁን ቢያስተምሩለት ጥቅሙ ለልጁ ብቻ ነው። ይህን መጽሐፉን ቢያሳትሙለት ግን አስቀድሞ ለስሙ መታሰቢያ ይሆናል፤ ቀጥሎም ለመንግሥትዎና ለሕዝብዎ ሁሉ ትልቅ ጥቅም የሚያስገኝ ነውና ለማሳተም ፈቃድዎ እንዲሆን አጥብቄ እለምንዎታለሁ።

መስከረም ፳ ፲፱፻፲፬ ዓመተ ምሕረት
ፈቃደኛዎና ታዛዥዎ ጳውሎስ መናመኖ

እኒህ ሰው ለዐልጋ ወራሹ (በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ) ባቀረቡት ልመና መሠረት ልዑሉ ከሁለት ዓመት በኋላ መጽሐፉ ታትሞ እንዲወጣ አደረጉ።

የግብረ ሕይወት ልጅ አሸብር ገብረ ሕይወትም «የንግሥት አዜብ ታሪካዊ ጉዞ» በማለት በቲያትር መልክ ባቀረቡት የ1951





www.ethiopianorthodox.org

ዓ.ም. መጽሐፋቸው ላይ «ሀሣ አጥማጅ» በማለት ተሳታፊ ያደረጉት ገጸ ባሕርይ «የአባታቸውን የሕይወት ሂደትና አመለካከት» የሚገልጥ ሊሆን እንደሚችል ብዙዎች የሚስማሙበት እንደ ሆነ ይገመታል፤ ይህንን ጠቋሚ ከሆኑት ሁለቱ የመጽሐፉ ክፍሎች እንደሚከተለው ይነበባሉ፡-

> ...አምላኬ ሆይ ሦስት ጊዜ መረቤን ወደ ባሕር ጣልሁ እንደምታውቀው በመጀመሪያ ጊዜ የሞተ አህያ ግንባር አጠመድሁ፤ በሁለተኛ ጊዜ ዐመድና ግብስባሶ የሞላበት ማሰሮ በመረቤ ተይዞ ከባሕር ወጣ በሦስተኛው ጊዜ ስብርባሪ ገልና የሐረግ ብጥስጣሽ ነው የተገኘተተልኝ። እማጸንሃለሁ ሕያው አምላክ ልመናዬን ስማኝ አምላክ አማልክት ለለመኑህ መታደግ የአምላክነትህ ግብር ነው... ።

ሀሣ አጥማጁ ገብረ ሕይወት በዚህ የልጃቸው ገለጻ ላይ በዘመናቸው ስኬትን ሳይሆን ውጤት አልባነትን በየሙከራዎቻቸው ሁሉ ላይ መታየቱ፣ የወቅቱ አስተዳደሪዎችና የቅርባቸው ሰዎች እንደ አዲስ አለማየሁ «ጉዱ ካሣ» እንደቆጠራቸው ያመለክታል። በሌላ ገጽ ሀሣ አጥማጁ ለንጉሥ ሰሎሞን፣ ለልዑላኑና ለባሕር ሰገድም ይህን ይሉቸዋል፡-

> በግርግር አልበላ፣ በሽክምም አልለብስ፣ በገንቦ አልጠጣ፣ ከአንዲት ክፍል መኖሪያ ቤት አላልፍ፣ ከአንድ ሰው መኝታ ዐልጋ አልተርፍ፣ ፍጡር የሚመኘውን ሁሉ ብጠይቅ እኔ የምገለገልበት በመጠኑ ነው... በችሎታዬና በተፈጥሮዬ መጠን አስፈላጊውን ሁሉ ሰጥተኸኛል፤ ካስፈላጊው በላይ መጠየቅ ኀጢአት ነው፤ ትርፍ ሀብት አይጠቅመኝም፤ ባለ ትርፍ ሀብት መሆን ትርፉ [ሀብቱን መጠበቅ] ነው።




እንግዲህ ከተለያየ አቅጣጫ የወጣቱ ገብረ ሕይወት አስተዳደግ፣ አስተሳሰብና ዕውቀትን መጠቋቆም ከተቻለ ቀደም ብሎ ወደ



ተጠቀሱ ሦስት ትኩረቶች ማለትም በታሪክ፣ በእምነት እና በአገር ነክ ጉዳዮች ላይ ወደ ነበሯቸው አስተሳሰቦችና አቋሞች መለስ ቢባል የሚከተሉትን እናገኛለን። ምንም እንኳ ገብረ ሕይወት፣ ከምእራቡ ዓለም የሕክምና ትምህርት ተምረው ቢመጡም፣ የጽሑፍ ሥራቸው ያተኮረው ታሪክ ላይ ነው። ምሁሩን ስለ ታሪክ ጽሑፎቻቸው ይዘት የተለያየ አስተያየት ቢሰጡም የአገር ልማትን ታሪክ በሚመለከት የተጠቀሙበት የታሪካዊ ዳራ (Historical Background) አጠቃቀምና ሥነ ዘዴ (Methodology) ዓይነተኛ ስለ ሆነ በአገራችን ታሪክ አጻጻፍ የዚህ ስልት ጀማሪ እንደሚያደርጋቸው ስለ እርሳቸውና ስለ ጽሑፎቻቸው ምሁራዊ ትንተና የሰጡት ፕሮፌሰር ሺፈራው በቀለ ይገልጻሉ። ገብረ ሕይወት፣ ታሪክን ማን ያጥናው? ማንስ ይጻፈው? እንዴትስ ይተግበር? በተሰኙት ዋነኛ ጉዳዮች ላይ በ1904 መጽሐፋቸው ላይ እንዲህ ይላሉ፡-

> ታሪክን መማር ለሁሉ ሰው ይበጃል፤ ለቤተ መንግሥት መኳንንት ግን የግድ ያስፈልገዋል። የድሮ ሰዎች ስሕተትንና በጎነትን አይቶ ለመንግሥቱና ላገሩ የሚበጀውን ነገር ያውቅ ዘንድ። የታሪክ ትምህርት ግን የሚጠቅም የእውነተኛ ታሪክ ትምህርት ሲሆን ነው። እውነተኛንም ታሪክ ለመጻፍ ቀላል ነገር አይደለም። የሚከተሉት ሦስት የእግዚአብሔር ስጦታዎች ያስፈልጋሉና። መጀመሪያ ተመልካች ልቡና የተደረገውን ለማስተዋል፣ ሁለተኛ የማያዳላ አእምሮ በተደረገው ለመፍረድ፣ ሦስተኛ የጠራ የቋንቋ አገባብ የተመለከቱትንና የፈረዱትን ለማስታወቅ። የአገራችን የታሪክ ጸሮች ግን በእነዚህ ነገሮች ላይ ኃጢአት ይሰራሉ፤ በትልቁ ነገር ፈንታ ትንሹን ይመለከታሉ፤ ለእውነት መፍረድንም ትተው በአድልዎ ልባቸውን ያጠባሉ፤ አጻጻፋቸውም ድብልቅልቅ እየሆነ ለአንባቢው አይገባም።




የገብረ ሕይወት የታሪክ መልእክት የዛሬ 100 ዓመት የተለፈፈ ቢሆንም፣ ለሺ ዓመታዊው (ሚሊኒየማዊው) ማኅበረ ሰብ አሁንም ቆሞ ያስተጋባል።



www.ethiopianorthodox.org

ገብረ ሕይወት እውነተኛን የታሪክ አጻጻፍ ጽንሰ ሐሳብ ከሚያዩዋቸው ተግባራዊ ምሳሌዎች ጋር በማጣቀስ ትክክለኛ የታሪክ መረጃን ባለ ማሳወቅ ሊመጣ የቻለውን ጦስ እንዲህ ያመለክታሉ፡- «አንድ ልበ ብሩህ የአበሻ ሰው መሬት ትዞራለች ብሎ ቢያስተምር አሁን በቅርቡ በሐረርጌ በዳኛ ተይዞ አልነበረምን? አሁንስ በ1900 ዓ.ም. አንድ ሰው የተዋሕዶን ሃይማኖት ቢነቅፍ አዲስ አበባ ገበያ ላይ በደንጊያ አልተቀጠቀጠምን?» በማለት ታሪክን አጥበው በወገናዊነት ሊተረጉሙ የወደዱ ያስከተሉትን ያለ ማወቅ ጥፋት በመግለጽ ከጠዋቱ ጀሮ ያለው ይስማኝ ብለው አሳስበዋል። ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ *«Pioneers of Change in Ethiopia»* በሚለው መጽሐፋቸው ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ከሌሎች የእሳቸው ዘመን ጓድ (Contemporary) የለውጥ ሐዋርያት ጋር ያደረጉትን የትምህርት ተሐድሶ ጥረት በተነተኑበት በስድስተኛው ምዕራፍ ውስጥ ገብረ ሕይወትንና ጥረታቸውን ለየት ባለ አጽንዖት ገልጸዋል። ካመለከቷቸው ፀበይት ነጥቦች ውስጥ አንዱ ንጉሦች ወይም በዙሪያቸው ያሉ መኳንንት ምርጫቸው ያደረጉት ታሪክን በሐቅ ላይ ተመሥርቶ መዘርዘርን ወይም ማስከበርን ሳይሆን፣ በየጊዜው ስለ እነርሱ ውዳሴና ምስጋና በማቅረብ አሞካሽተው የሚዘክራቸውንና የሚጽፍላቸውን በመሸለም፣ ርስት በመስጠትና በመሾም ታሪክ እንዲጻፍ እንደሚመርጡና በዚህም ታሪክ ጸሓፊውም ሆነ የተጻፈለት ከእውነት እንደ ተራራቁ ይተነትናሉ። አያይዘው በየዘመኑ ድልድይ የሚሰሩ፣ ትምህርት ቤት ለመሥራት የሚጥሩ፣ ዘመናዊ አኗኗርን የሚያስተዋውቁ ምንም ስፍራ እንዳልነበራቸው እንደ ገብረ ሕይወት ያሉት በማስተዋላቸው ይህ እንዲታረም ጥረት ያደርጉ እንደ ነበር ይገልጻሉ።



ገብረ ሕይወት ታሪክ ታሪክ ሆኖ በሰፈሩት ሦስት መለኪያም ያልፍ ዘንድ፣ «ሰዎች ከእንቅልፍ በመባነን የተግባር ሰው መሆን አለባቸው» ከማለት ባሻገር፡- ምርምር የየግለሰቡ



ግላዊ ሀብት እንደ ሆነ ራሳቸውን ቀዳሚ አድርገው ይመክሩ ነበር። ለዚህም እንደ ብርቱ ተምሳሌት የሚያስቈጥራቸው «በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ነው በማለት የዓለምን ዕድሜ ከ 8000 ዓመት አለማስበለጡ በሕዝብ የተለመደ አባባል እንጂ ተገቢ እውነት አይደለም በማለት የምድርን ዕድሜ ከሥነ ምድር ውጤት ጋር በማቆራኘት በትንሹ ወደ 150,000 ዓመታት ወደ ኋላ ማስመለስ እንደሚገባ» .. መጻፋቸው ነው። ገብረ ሕይወት ይህን ሲሉ፡-መጽሐፍ ቅዱስን ጥያቄ ውስጥ ሊከቱ ሳይሆን መጽሐፍን በማንበብ ሊተረጉሙ የሚነሱ ሁሉ ዙሪያ ዐቀፍ ትንታኔ ሊይዙ እንደሚገባ ማሳየታቸው ነበር።

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ እምነትን በተመለከተ ኅብረተ ሰቡ እርስ በርስ በመቀባበል ሊተያይ የሚችልበትን መሠረታዊ ቁም ነገሮች አስተላልፈዋል፤ ይህንንም የአጤ ምኒልክ የግዛት ዘመነ መንግሥት ሊፈጽመው ካልቻለ ዐሊጋ ወራሻቸው ልጅ ኢያሱ እንዲፈጽሙት በማሳሰብ ዐሥር ጽኑ መልእክቶችን ጽፈዋል፤ ከዝርዝሮቹ ብዛት የተነሣ ሁሉን መጥቀስ ባይቻልም ሁለተኛው፣ አምስተኛውንና ዐሥረኛውን ብቻ አለፍ አለፍ ብለን ስንመለከት ባጭሩ የሚከተለውን ይመስላል፦

መንግሥታችንም እንድትቀና የሚከተሉቱ ዐሥር ነገሮች በቶሎ ቢፈጸሙ ማለፊያ ነበር። መጀመሪያ ...

⋮

ሁለተኛ ሕዝቡ ለመንግሥት የሚከፍልው ግብር እንደየሀብቱ መጠን ቁርጥ ሆኖ ይታወቅለት። የሕዝቡም ቁጥር በመዝገብ ይግባ። እንዲሁም በየዓመት የሚወለደውና የሚሞተውም የሚጋባውና የሚፋታውም በመዝገብ ይታወቅ።

አምስተኛ



ፍትሐ ነገሥታችን ከዛሬው ያደባባይ ሥርዓት ጋራ አይስማማም። ስለዚህ መንግሥት የሥርዓት አዋቆችን ሰብስቦ ከኤሮጳ ሥርዓት ጋራ የተስማማ ፍትሐ ነገሥት ያውጣ። ይህም ሲደረግ የኤሮጳን ሥርዓት የሚያውቅ አማካሪ



www.ethiopianorthodox.org

ያስፈልጋል። የተጻፈ ሥርዓት የሌለው መንግሥት ብዙ ዕድሜ የለውም።

ዐሥረኛ፣ የሃይማኖት ዐርነት ይታወጅ። የሃይማኖት ዐርነት ጥቅም መሆኑን የማያወቅ ብዙ ሰው ይኖራል፤ ስለዚህ የሚከተለውን ብናስተውል ደግ ነው ፤ ያገራችን ሰው የተዋሕዶ ሃይማኖት ከሁሉ ሃይማኖት ይበልጣል ብሎ ያምናል፤ በልጦ ግን ምን ረባን? ማን ዐወቀው? የአገራችን ካህናት መንግሥት ጠበቃቸው ሁኖ ሌላ ሃይማኖት ሊገባ እንዳይፈቅድ ዐውቀው ሃይማኖታቸውን ለሕዝቡ ሊገልጹለት አሳብ የላቸውም። ስለዚህ ሕዝቡ እንኳን ተዋህዶ ማለት ምንድር እንደ ሆነ ሊለይ ቀርቶ የክርስቲያን ሃይማኖት አውራ መሠረት የሆነውን የወንጌልን ቃል አያወቅም። ስለዚህ ዐጕል ቀረ፤ የሃይማኖት ዐርነት እስኪታወጅ ድረስም ዐጓጕል ይቀራል... ሃይማኖት የልብ ነገር ነው፤ ስለዚህ ሰማያዊው ንጉሥ እንጅ የዚህ ዓለም ንጉሥ አይቈጣጠረው። ወንጌል የቈማርን ለቈማር ስጡ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ያለውም በዚሁ ቢተረጐም ለመንግሥታችን ሳይበጅ አይቀርም። እነሆ ይህ ሁሉ ባጤ ምኒልክ ታስቦ ኖሮ ይሆናል፤ ነገር ግን አልተፈጸመም።

ገብረ ሕይወት አገር አፍቃሪ ብቻ ሳይሆኑ የአገር እድገት መሠረት ምን ሊሆን እንደሚገባው የመንግሥትም መኖር ድርሻው በሥራው እንዲገለጥ በተለይ «መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር» በተሰኘው መጽሐፋቸው አሳውቀዋል። ለዚህም የጀርመኑ ሊቅ አስቴር ሰሞሎ በልጅነት ዕድሜያቸው እንዲቀስሙ ያደረገውን ትምህርት እንዲህ በማለት ይጽፋሉ፡-

... እያንዳንዱ ሰው ሌላውን ሰው ሁሉ አጥቅቶ ለብቻው እንዲኖር ይወዳል፤ መንግሥት ግን በግዛቱ ውስጥ የሚኖሩትን ኀይለኞች ሁሉ እርስ በርሳቸው እንዲተፋፈሩ የግድ ይላቸዋል፤ የመንግሥት ጥረቱ ሕዝቡን ሁሉ አስማምቶ በመካከላቸው ሰላም ለማድረግ ነው...





በዚህም እምነታቸው የመንግሥት መኖር ለአንድ አገር አስፈላጊ ነው። ከዚህም የተነሣ እያንዳንዱ ዜጋ ኀላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ፣ መንግሥትም ሕዝቡን በሐቅ እንዲያገለግል ጽሑፋቸው ያመለክታል። ስለ አገር ብልጽግና መሠረቱ ታታሪነት መሆኑን ሲያብራሩ፣ ከነጕድጓድ ድምፅና ከገዘሆን ግዝፈት ይልቅ ለገብረ ጕንዳንና ለንብ ኀብረት ያደላሉ።

ዕውቀት የሌለው ሰው የገዘሆንን ቁመትና መብረቅ ሲያይ፣ የትልቅም ነጐድጓድ ጩኸት ሲሰማ የፈጣሪውን ሥራ ያደንቀዋል፤ አስተዋይ የሆነ ሃይማኖተኛው ግን የንብንና የጕንዳንን ትጋት፣ የሥራቸውንም ትክክልነት፣ የሥርዐታቸውን ማማር አይቶ በዚህ ዓለም ፍጥረት ይገረማል፤ ከመብረቅና ከነጐድጓድ ኀይልም ይልቅ የንብንና የጕንዳንን ተአምር ለፈጠረው የበለጠ ምስጋና ሁኖ ይታየዋል። እነዚህንም ሰሎሞን በመጽሐፈ ምሳሌ 6÷6፣ 30÷25 ላይ አብራርቶአቸዋል ... የአንድ አገር ሕዝብም ይበለጽግ ዘንድ እንዲህ ይሆን ዘንድ ይገባል።

ገብረ ሕይወት የሰው ታታሪነቱ ከሚገለጽበት አንዱና ዋንኛው ከመሬት ጋር ያለው መልካም ግንኙነት መሆኑን እንዲህ በማለት ያስረዳሉ፡-

መሬት ማናቸውንም ነገር ብትሰጥ በብድር ነው፣ ብድሩን ካልመለሱላት እንደ ባንኮች ሁሉ ታስቸግራለች በአይሁድና በክርስትና የሃይማኖት መጽሐፍ እንደምናየው ... ጥረህ ግረህ በግንባርህ ወዝ ብላም ሆነ መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ የተባለለት ሰው መሬትን ይንከባከባት ዘንድ ይገባል።

ገብረ ሕይወት የመሬትን አበዳሪነት ከባንክ ጋር ማነጻጸራቸው፡- ሰው እንጀራውን በመሬት ላይ በሥራ መጠን እንደሚያገኝ ሁሉ ኑሮውን ላደረጀባት መሬት ደግሞ በተራው ያላትን ንጥረ ነገር በመጠበቅ፣ በመተካት፣





www.ethiopianorthodox.org

በመንከባከብ ኀላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባው ያስረዳሉ። ነጋድራስ ገብረ ሕይወት የአካባቢ ጥበቃ ግንዛቤአቸው እጅግ የሚያስደንቅና በዘመኑ አውሮፓውያን ዘንድ እንኳ ይህ ለመታሰቡ የሚያጠያይቅ ነበር ማለት ይቻላል። በተለይም ማኅበራዊ አለመረጋጋት በሥነ ምኅዳር ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ በስፋት ያተቱትን ዐጠር ባለ መልኩ ቀጥሎ መመልከት ይቻላል።

በሕዝቦች በጐሣዎችና በአንባዎች መካከል አንዱ የአንደኛውን አገር መሬት ፍለጋ በሚፈጠረው ተደጋጋሚ ጦርነት አስቀድሞ እየተሻሻለ ያለው አካባቢ ከመጥፋቱም በተጨማሪ ሰዎች ይሞታሉ፤ የተረፉትም ይሰደዳሉ፤ በያሉበት ለብዙ ጒዳት ይዳረጋሉ። በዚህ ሁኔታ ረሀብ፣ ስደትና በሽታ እየተፈራረቀ፣ የተፈጥሮ ጥሪት እየጠፋ ሰውም ምድርን መግዛት ያቅተዋል። ሰላም ፈላጊውም ሕዝብ ተደጋጋሚ ጥቃት ሲደርስበት እያለማና እያሻሻለ ያለውን መሬት እየተወ ራሱን ለመከላከል የሚያመችውን ስፍራ ፍለጋ ወደየተረተሩ ይሰደዳል። ነጋድራስ ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ሕዝብም ቅጥልጥል የታሪክ ሂደት እውነት መሆኑን ከአክሱማዊው መንግሥት አንሥቶ የነበረውን ቁርቁስ ዋቢ በመጥቀስ ያትታሉ። አምልኮተ አሐዱ አምላክ (Monotheism) መሠረት የሆነው ይሁዲነት በአክሱማዊው መንግሥት ጊዜ ገባ፤ እያደገም መጥቶ ብዙ ተከታዮችን አፈራ፤ በነባሩ ብዙ አማልክት አምላኪና (Polytheism) አዲስ በመጣው ይሁዲነት አምላኪዎች መካከል ጦርነት ተካሔደ፤ ከዚህ የተነሣ ነባሩ የተፈጥሮ ሀብት ተደመሰሰ፤ የለማው መልሶ ምድረ በዳ ሆነ፤ ብዙ ሕዝብም ዐለቀ፤ መሬት ተበላሸ፤ ለረጅም ጊዜም ለኢትዮጵያ በዕውቀት ወደ ኋላ መቅረት ምክንያት ሆነ። እንደ ገናም «የግራኝ መሐመድ ወረራ» በመባል የሚታወቀው ጦርነት ዐሥራ አምስት ዓመት የፈጀ በሰው፣ በመኖሪያ ቤቶችና በተፈጥሮ ደን ላይ የእሳት ዝናብ አዘነበ። እንደ ገና ሕዝቡ ከምርታማ ስፍራ ወደ ገደሉና ወደ ተረተሩ መሸሸጉን ቀጠለ። ይህም ለረጅም ጊዜ



፻



የትውልድን ቅስም ሰባሪና ነዋሪ ጥሪትን ያጠፋ ሆኖ ቀረ። በሰሜን በደርቡሾችና በጣሊያኖች የደረሰው ጥፋት ኢትዮጵያ ትግራይና ጎንደር ቀላል የማይባል ጥፋት አስከትሏል። እንዲያ እያለ ሕዝባችን ከአንዱ ክልል ወደ ሌላ ክልል ምክንያቱ በበዛ ጎጠኝነት ዕረፍት አጥቶ በእርጋታና በቈይታ ለሚገኝ አገር ዐቀፋዊ እድገት ባእድ ሆኖ ቀረ በማለት ታሪክን የተንተራሰ የሰላ ሥነ ምኅዳራዊ (Ecological) ትንተና ገና ዓለም በሙያው መስክ ሳትነቃ ሰጥተዋል።

እኒህ ሰው ስለ አንድ አገር ኢኮኖሚ ማደግ መሠረት ጣይ ነው ብለው ስለሚያምኑበት የባንክ አልግሎት ሲጽፉም ዐይነተ ብዙ ባንኮች መኖራቸው ተገቢ ነው ይላሉ፤ ይህም በምኒልክ ጊዜ ሳይሆን በመቅረቱ ወራሲው መንግሥት ቢያርመው በማለት ተከታዩን አሰተያየት ጽፈው ነበር ፦

ዛሬ በኢትዮጵያ የቆመው .. ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ.. ካቆመበት ቀን ጀምሮ እስከ ኀምሳ ዓመት ድረስ በኢትዮጵያ ሌላ ባንክ እንዳይቆም ውል ተቀብሏል፤ ከዚህ ቀደም እንደ ተረዳነው ግን ማናቸውም ነገር በጥቂቶች ሰዎች እጅ ገብቶ ሞኖፖል ሲሆን ለሕዝቡም ለመንግሥቱም ጒዳት ነው። ለአፄ ምኒልክ አንድ ሰው መጥቶ በአገርዎ ከእኔ በቀር ሌላ ሰው እንዳያርስ... ወይም እኔን ሳይጠይቅ በየቤቱ ማንም ወጥ እየሠራ እንዳይበላ ፈቃድ ይስጡኝ ብሎ ለምኗቸው ቢሆን፣ የሚናገራቸው ቃል ምንም ቢያምር የሚሰጠው ተስፋ ምንም ትልቅ ቢሆን ያለ ጥርጥር ይቈጡት ነበር..

ይህን ሲሉ አፄ ምኒልክ ባንክን አስመልክቶ የዕወቀት ባሕርይ በሌላቸው ሰዎች ቃል ተታለው ይህንን እንደ ፈጸሙ በመናገር ሲሆን ለአንድ አገር ዕድገት የተለያዩ ባንኮች ተወዳዳሪዎች ሆነው ሕዝቡን ቢያገለግሉ የተሻለ ውጤት ሊኖር እንደሚችልም ያኔ ቀድመው አሳስበዋል።



ለኢትዮጵያችን ቀድመው ደርሰው ነበር፤ አንተ በመባያ ዕድሜአቸው አንቱ

፻፩



www.ethiopianorthodox.org

የሚያሰኝ ሥራ ሠሩ። ምሁር ኅሊናቸው የአገር ዕድገት ቅንአት ጫረባቸው፤ ለዚህች ምድር ሩቅ አሳቢ ሆነው የወጣትነት ትኩረታቸው ብዙ ዘመን እንደ ተጠራቀመ የሽምግልና ምክር ይኸው መቶ ዓመት ሲያስተጋባ ኖረ። የኒህ ሰው ዕድሜ 33 ዓመት ብቻ መሆኑ ይቆጫል! ይሁን እንጂ ትልቁ ጥያቄ ስንት ዓመት ኖርን ሳይሆን ረጅሙንም ሆነ ዐጭሩን ዕድሜ እንዴት ኖርነው የሚለው ነው። ነጋድራስ በ1912 ነሐሴ ወር ትልቁን እንቅልፍ አንቀላፉት፤ አምላክ አሁን ከመቶ ዓመት በኋላ የአፍታ ዳግም ትንሣኤ ዕድል ቢሰጣቸውና ኢትዮጵያን ቢያዩዋት ምን ትመስላቸው ይሆን?

## መወድስ

ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ምንኛ ተማረ
እሩቅ እያሰበ እርሱ ቅርብ ዐደረ
ያልታደሉ ሰዎች ቀድመው እየመጡ
የደነደነ አንጎል መክረው ላይለውጡ
ድንቁርናን ታግለው ሳያንደባልሉት
እንደተቃጠሉ እንዴት ይግቡ መሬት?





## ትምህርተ ውልብታ

ስህተት ነው ብለው ላመኑበት ነገር ምሑራዊ መልስ ለመስጠት መዘጋጀታቸው በትምህርት የገፉ ሁሉ ሊከተሉት የሚገባ ምሳሌ ነው።

አንድ ሰው በአገሩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ መልካም ተጽእኖ የማምጣት ኀላፊነት እንዳለበት ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት እንማራለን።

የሕይወት ቁም ነገር የሚለካው በዕድሜአችን ርዝመት ሳይሆን በዘመናችን የምንተገብረው ሥራ ፍሬአማ መሆን በመቻሉና ባለመቻሉ ነው።

ማኅበረ ፖለቲካዊ ለውጥ ከአንድ አገር ነባር ታሪክ ጋር መጣጣም የሚችልባቸው ሁኔታዎች ሲጎድሉ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ምንም ያህል በቅንአትና በዕውቀት ቢደገፉም ውጤቶቻቸው አስተማማኝ ላይሆን ይችላል።

የአንድ ሰው የሥራ ውጤት ለትውልድ የሚተላለፈው በራሱ ጥረት ብቻ ሳይሆን በእውነተኛ የሕይወት ጓደኞችም ጭምር ነው። ይህንን ከገብረ ሕይወት ባይከዳኝና ከጳውሎስ መናመኖ እውነተኛ ጓደኝነት እንማራለን።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የተሰማሩባቸው የቀለም ትምህርት ዘርፍና ለኅብረተሰብ ልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት መስክ ሊለያይ መቻሉን ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት ተመክሮ ማየት ይቻላል።





www.ethiopianorthodox.org

## የውልብታ ምንጭ


ጥ.ጋቤ አስረስ የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ዐጭር የሕይወት ታሪክ ፣ በቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርስቲ የድግሪ ማሟያ ጽሑፍ 1962 ዓ. ም.

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር 1916 ንግድ ማተሚያ ቤት

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ 1904 ዓ.ም.

አሸብር ገብረ ሕይወት የንግሥት አዜብ ታሪካዊ ጉዞ 1951ዓ.ም.

Bahiru Zewde *Pioneers of Change in Ethiopia:* the Reformist Intellectuals of the Early Twentieth Century, Eastern African Studies, Addis Ababa University Addis Ababa, 2005

Shiferaw Bekele, *Gabra Heywat Baykedagn and the Emergence of a Modern Intellectual Discourse*, Sociology, Ethnology Bulletine, Vol. 1, No 3 February 1994

ብርሃን መጽሔት 1994 ዓ.ም.

መስከረም ቅጽ 1፣ 3 ፣1973 ዓ.ም.

ሩህ ቅጽ 2 1985 ዓ.ም.

ሰንደቅ 2ኛ ዓመት ቁጥር 77 1999 ዓ.ም.



መዝናኛ 1ኛ ዓመት ቁጥር 043 መጋቢት 25 ቀን 1997 ዓ.ም.




## የአንባቢው የግል ማስታወሻ






www.ethiopianorthodox.org